## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ይስማማሉ። በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ስለመሲሑ ማንነት እንዲሁም ሥራ ያለውን ልዩነት ይግለጹ።
2. አንድ ሰው ሙስሊሞች ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ተግባር እንዴት እንደሚፈጽሙ መረዳት ይችላል። ነገር ግን የክርስቲያኖችን መረዳት ያዳግተዋል። ልዩነቱ ከምን እንደ መጣ ይግለጹ። (ማቴዎስ 5+48፣ ሱራ 33 +40)።
3. ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብለው ማመናቸው ምን ዐይነት ትርጒም እንዳለው ይግለጹ (ሱራ 33 +40)?
4. ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ ነው ብለው ማመናቸው ምን ትርጒም ያለው ይመስሉታል (ሉቃስ 4 +14-40)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ በቁርአን ውስጥ ምስጢራዊ ሰው ነው። ኢየሱስ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ ያለው ስፍራ እጅግ አነስተኛ ነው። ለብዙ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስን አስፈላጊ ወዳልሆነና ከእውነተኛ ሕይወት ተሞክሮ ውጪ በሆነ ሁኔታ ምስጢራዊ ሰው ስታደርገው ቆይታለች። ስለ ኢየሱስ እውነታ ከመሆኑ ይለቅ ምስጢር ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ይግለጹ።



## ምዕራፍ ስድስት

# ቅዱሳት መጻሕፍት

# ቁርአን—መጽሐፍ ቅዱስ

ኢብራሂም መሐመድ፣ "እባክህ መጽሐፍ ቅዱስህን አውሰኝ" ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልካሙ የምሥራች (Good News) የሚባለውንና አረንጓዴ እንዲሁም ጠንካራ ያልሆነ ጥራዝ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ እንሥቼ ሰጠሁት። ኢብራሂምም ሰዎች የመጽሐፉን ማንነት እንዳያውቁ በሚል በቡናማ ወረቀት ለበደው። መጽሐፉን በአክብሮትና በጥንቃቄ በመያዝ ከቤታችን ሹልክ ብሉ በመውጣት ወደ ቤቱ ሄደ።

በማግሥቱ ማታ ኢብራሂም ያንኑ መጽሐፍ ይዞ ወደ ቤታችን መጣ። በኢብራሂም ገጽ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሐዘን ድባብ በግልጽ ይነበብ ስለነበረ፣ በእያሌው እንዳዘነ ማወቅ አዳጋች አልነበረም። ቤት በመግባት ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ፣ መጽሐፉን ከቦርሳው ውስጥ በማውጣት ጠረጴዛው ላይ አነጠፈው።

"እኔ መቼም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መስሎኝ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ ሆኖ አላገኘሁትም። ሰዎች የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት አበላሽተዋል። እንዴት ዐይነት አሳዛኝ ጥፋት ነው! መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ከሆነ እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይደለም"።

ኢብራሂም በዚህ ዐይነቱ ታላቅ ሐዘን ውስጥ እያለ፣ ቡናማ መልክ ያለውን ባዶ ቦርሳውን አንከርፍፎ በዚያ ጨለማ ወደ ቤቱ ሄደ። "ተበላሽቶአል" የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ምስቅልቅል ባለው ጠረጴዛዬ ላይ ተዘርሮአል።

### ታሪክና መገለጥ

ኢብራሂም ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ነው። እስትንፋስ እግዚአብሔር ያለበት እንደ እርሱም ያለ የታሪክ መጽሐፍ የለም። በእኔ ግምት ኢብራሂም ንባቡን የጀመረው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ሲሆን፣ ንባቡን ከጀመረ ከጥቂት አንቀጾች በኋላ ቃየን ወንድሙ አቤልን የገደለበትን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የግድያ ታሪክ አንብቦአል። ከጥቂት ምዕራፎች በኋላም፣ የኖኅ ልጆች አባታቸው ሰክሮ እንዲሁም ራቁቱን ሆኖ

ስላገኙት፣ ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ፈጸሙ፣ ያዕቆብ በረከትን ለማግኘት ዐይነ ስውር የሆነውን አባቱን ይስሐቅን፣ ኤሳው ነኝ ብሎ እንዳታለለው እንዲሁም የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ለግብፅ ነጋዴዎች በሠላሳ ብር እንደ ሸጡት፣ በተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ አንብቦአል። እነዚህን ታሪኮች ያነበበ አንድ ሙስሊም እነዚህ ዘገቦች የእግዚአብሔር ቃል የመሆናቸውን ጉዳይ በጭራሽ ሊቀበል አይችልም። ኢብራሂምም ከላይ የተመለከትናቸው ታሪኮች የእግዚአብሔር ቃል አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ እንዳደረሱት እሙን ነው።

ሙስሊሞች ቁርአንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማነጻጸር፣ ቁርአን ከሰው ልጆች ታሪክ በላይ እንደ ሆነ ይናገራሉ። ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ከማንኛውም ሰብአዊና ታሪካዊ ገድፈቶች የነጻ ነው እንዲሁም ከሰማይ ከአላህ ዘንድ የተላከ መገለጥ ነው የሚል ግንዛቤ አለ።

የቁርአን ሥነ ጽሑፋዊ ውቅር ከሰብአዊና ከታሪካዊ ተጽእኖዎች ነጻ እንደ ሆነ ይታሰባል። አስተምህሮው የተዋቀረበትም መንገድ፣ ከመልእክቱ መገለጥ ቅደም ተከተል ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም። ከመጀመሪያው ምዕራፍ በስተቀር ሁሉም የቁርአን ምዕራፎች ከረጅም ምዕራፎች ወደ አጫጭር ምዕራፎች የተደረደሩ ናቸው። ረጃጅም ምዕራፎች በመጀመሪው ክፍል ላይ ሲጻፉ አጫጭሮቹ ደግሞ ከበስተ ኋላ ተሰትረዋል። ቁርአናዊ ምንባባት ነቢዩ መሐመድ በመካ ቆይታቸው ወይም በመዲና ቆይታቸው ጊዜ የተጻፉ የመሆናቸው ጉዳይ፣ ከግምት የሚገባ አይደለም። ሙስሊሞች የአላህ መገለጥ (ቁርአን) በታሪክ ክሥተቶች ላይ አልተመረኰዘም የሚል እምነት አላቸው።

በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ ቁርአን ታሪካዊ ክሥተቶችን አካቶ ይዞአል። ለምሳሌ ስለኖኅ የጥፋት ውሃ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሙሴ በቍጥቋጦ ውስጥ እንደ ተገለጠለት ተጽፎአል። እነዚህ ምንባባት እንደ ታሪክ ዘገባ የቀረቡ ሳይሆን፣ እውነትን ለማሳየት ከታሪክ ውስጥ እንደ ተወሰዱ ናሙናዎች ነው። እነዚህም ታሪኮች ምሉዕነት የሚጐድላቸው ሲሆን፣ በተለያየ ስፍራ ተበጣጥሰው ይገኛሉ። ሙስሊሞች መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚወረስ መመሪያ እንደ ሆነ ያምናሉ። ታሪካዊ ክሥተቶች የመገለጡን እውነተኛነት ሊያሳዩ ይችላሉ፤ ነገር ግን መገለጡ ሲመጣ ከተፈጸሙ ክሥተቶች በስተቀር፣ ሌሎች ታሪካዊ ክሥተቶች መገለጥ ሊሆኑ አይችሉም።

ይህም ሲባል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ)፣ ለታሪክ ግድ የለውም ማለት ግን አይደለም። ነቢዩ መሐመድና የጥንቱ የሙስሊም ማኅበረሰብ በቁርአን ውስጥ



አልተካተቱም። የነቢዩ መሐመድ ታሪክና አባባሎች ሐዲስ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። ሐዲስ ትልቅ ዋጋ እንዳለው ቢታሰብም በቁርአን ውስጥ ምንም ስፍራ የለውም። በሙስሊሞች እሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ የተምታታ የሐዲስና የእግዚአብሔር ቃል ቅይጥ ነው።

እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሠራው ሥራ ራሱን ገልጦአል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፣ የእስልምና ነገረ መለኮት የሚቃወመው ለምንድን ነው? እስልምና እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ እንደ ሆነ ያምናል። ስለዚህም እግዚአብሔር ራሱ ባሮቹ የሆኑትን የሰው ልጆች መልክ ይዞ ተገለጠ የሚለው ትምህርት፣ እግዚአብሔርን ዝቅ እንደማድረግ ይታሰባል። እግዚአብሔር እጅግ ትልቅ አምላክ ነው። ሙስሊሞች፦— " ይህ ትልቅ አምላክ በተፈጥሮ ውስጥ ራሱን እንዴት ይገልጣል?[1] ራሱስ እንዴት ሰው ሆኖ በሰዎች መካከል ይገለጣል? ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም" ብለው ያስባሉ።

ይሁንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ፣ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራውን ሥራ መሠረት ያደረገ ታሪክ ነው። ክርስቲያኖችና አይሁዶች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራቸው ሥራዎች የመጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ዋነኛ ክፍል እንደ ሆኑ ያምናሉ። የአይሁድ የነገረ መለኮት ምሁር ኢሚል ፋከንሀይም እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘገቡ የታሪክ ክሥተቶች ለዘመናት እያስደነቁን የሚኖሩ መሠረታዊ መረጃዎች ናቸው ብሎአል[2]። ለምሳሌ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር ዐርነት አውጥቶአቸዋል። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሲና ተራራ ተገናኛቸው (ዘፀአት 1-14: 19-20)። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት የተመሠረተው፣ በእነዚህ ሁለት ክሥተቶች ላይ ነው። በእርግጥ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከሠራቸው ሥራዎች፣ የመሲሑ የኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ቀዳማይ እንደ ሆነ ያምናሉ።

ሙስሊሞች በተደጋጋሚ የሚነግሩኝ፣ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስን በተመለከተ የቀረበው ዘገባ እንዲሁም አስተምህሮ ጳውሎስ ሆን ብሎ የፈጠረው ፈጠራ እንደ ሆነ ነው። በእርግጥ በዘመናችን ያሉ አንዳንድ የነገረ መለኮት ምሁራን ይህ ዐይነት አመለካከት አላቸው፤ ምናልባትም ሙስሊሞች ይህን አመለካከት

---

1 Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 134-135.

2 Emil Fackenheim, *The Presence of God in History: Jewish Affirmations and Philosophical Reflections* (New York: New York University Press, 1970), 8-14.

ስላነበቡ ይሆናል ይህን መሰል አስተያየት የሚሰነዝሩት። በእርግጥ ይህ አባባል ግን ትክክለኛ ነውን? ኢየሱስ ለዘመናት አማኞችን ሁሉ እንዳስደነቀ ጳውሎስም በክርስቶስ ተደንቆአል፤ ከዚህ በተረፈ ግን ጳውሎስ ከሌሎች የተለየ ነገር አላደረገም።

ጳውሎስ ወጣት በነበረ ጊዜ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ሁኔታ ይሰደዱ፣ እርሱም ክርስቲያኖችን ክፉኛ ያሳድድ ነበር። የትንሣኤው ጌታ በራእይ ከተገናኘው በኋላ ግን፣ ስለኢየሱስ ያለው አድናቆት መቼም ቢሆን ከልቡናው ሊጠፋ አልቻለም። የኢየሱስን ሕይወት አጥብቆ ይመረምር ነበር። የጳውሎስ ባልንጀራ የነበረውም ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር በመሆን የኢየሱስን ሕይወት መመርመር ጀመረ። ከዚህም የተነሣ የክርስቶስን ሕይወትና አገልግሎት የሚተርከውን ወንጌሉን ለመጻፍ እንዲዘጋጅ ምክንያት ሆነ። ሉቃስ ራሱ፣ የሉቃስ ወንጌልን ለመጻፍ ያደረገውን ጥረት እንዲህ ሲል ገልጾታል:—

> የተከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ከመጀመሪያው በዐይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፣ በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ፣ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ከመጀመሪያ ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ (ሉቃስ 1+1-4)።

ስለዚህ የጳውሎስ ነገረ መለኮት፣ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ለተፈጸመው ታሪካዊና መለኮታዊ ክሥተት ምላሽ ነው[3]። በጳውሎስ የተጻፉ መልእክቶች በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተካተዋል። መልእክቶቹም በክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ የተፈጸሙ አስደናቂ ክሥተቶች ናቸው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ እንዲሁም ሰዎች ለእርሱ የሰጡትን ምላሽ የሚተርክ መጽሐፍ ነው።

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ፣ የአጻጻፍ ሂደቱ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደ ተካሄደ ያምናሉ። ይህን እምነት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያብራራዋል:—

> ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል (2ጢሞ 3+15-17)

[3] N.T. Wright, *The Challenge of Jesus: Rediscovering Who Jesus Was and Is* (Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1999).



# ምሪትና ኅብረት

እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ከሰዎች ጋር ኅብረት ያደርጋል። በቁርአን ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን ወደ ሰው ልጆች እንደሚልክ ይታሰባል። የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ጸሎትም ይህንን ልዩነት የሚያንፀባርቅ ነው። ክርስቲያኖች "የአባታችን ጸሎት" ብለው በሚጠሩት ጸሎት በአንጻሩ በቁርአን የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ደግሞ፣ "በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ በኾነው" ተብሎ ተጽፎአል። "እግዚአብሔር አባታችን" በሚለውና "በእግዚአብሔር ስም" ተብሎ በሚቀርበው ስግደትና ጸሎት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር በግላችን እንደሚገናኘን ያስተምራል። እግዚአብሔር እኔን አግኝቶኛል፤ ራሱንም ገልጦልኛል። እርሱ እግዚአብሔር አባቴ ስለሆነ በሐዘኔና በደስታዬ ውስጥ እውነዊ ተሳትፎ ያደርጋል። እግዚአብሔር ትልቅ አምላክ ቢሆንም እንኳ እኛን ለመገናኘት ራሱን ዝቅ አደረገ። በሰማያት ያለው አባታችን ደስታችንን እንደሚጋራ ሁሉ በሐዘናችንም አብሮን ያዝናል[4]። ፍሥሓችንንና ሕማማችንን ይካፈላል።

ቁርአን እግዚአብሔር የቅርብ አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል። ሱራ 50+16 "ሰውንም ነፍሱ (በሐሳቡ) የምታጫውተውን የምናውቅ ስንሆን፣ በእርግጥ ፈጥረነው፤ እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን" ይላል። እግዚአብሔር በቅርበት የሚከታተለን የእርሱን ፈቃድ መፈጸም አለመፈጸማችንን ለማረጋገጥ ነው። ፈቃዱን የምንፈጽመውም ለእግዚአብሔር በመስገድ ነው። በእስልምና "እግዚአብሔር ቅርብ ነው" የሚለው አስተሳሰብ፣ ደስታችንንና ሐዘናችንን ለመጋራት ነው የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ አይደለም። ሩኅሩኅ ለሆነው አምላክ እንገዛለን፤ ነገር ግን አምላኬ በሚለው መረዳት እርሱን ማወቅ አንችልም[5]። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ ይመልሳል፤ ይሁንና በእኛ ልመና ከእኛ ጋር መስተጋብር አይፈጥርም። መቼም ቢሆን እርሱ የእኛን መከራ አይጋራም።
በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ በመከራ ውስጥ ባለንበት ጊዜ እንደሚገናኘን ተጽፎአል። አዳምና ሔዋን በገነት ዛፎች መካከል በተሸሸጉበት ስፍራ ተገናኛቸው። እግዚአብሔር ኖኅን እንዲሁም አብርሃምንና

[4] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 134-135.
[5] ዝኒ ከማሁ።

ሣራን ተገናኛቸው:: አምላካችን አጋርን በጭንቀትዋ ጊዜ ሲያገኛት ሙሴንም በቁጥቋጦ ውስጥ በእሳት አምሳል ተገለጠለት:: በተጨማሪም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሲና ተራራ ተገለጠላቸው:: እግዚአብሔር ለሰዎች በተገለጠባቸው በእያንዳንዱ አጋጣሚ ለተገለጠላቸው ሰዎች ሁሉ ትልቅ ቦታ እንዳለው አመላካች ሲሆን፣ ለሌሎችም በረከት የሚሆንበት ሁኔታ ነበር:: እግዚአብሔር ሲገለጥልን ጥሪውን እንሰማለን፣ ለሌሎችም በረከት እንሆናለን::

የእስልምና እምነት አማኙ ግለሰብ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳያደርግ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመራዋል:: ለምሳሌ እግዚአብሔር ለመሓመድ የእስልምናን አስተምህሮ እንዲገልጥላቸው መልአኩ ገብርኤልን ልኮአል:: ነገር ግን መገለጡ በመጣባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ፣ እግዚአብሔር መሐመድን በግል አልተገናኛቸውም:: ይሁንና እግዚአብሔር ሙሴን በቍጥቋጦ ውስጥ በእሳት አምሳል በተገናገኘው ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ቀጥተኛ መስተጋብር እንደ ነበረው አመላካች ነገሮች አሉ:: አንዳንድ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ግን ለሙሴ በቍጥቋጦ ውስጥ የተገለጠው መልአኩ ገብርኤል እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ይላሉ:: አብዛኛው ሙስሊም ይህንን አመለካከት ይቀበላል[6]::

በቁርአን መሓሪው አምላክ ፈቃዱን ለሰዎች እንደ ገለጠ ሲጻፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር ሰዎችን ባሉበት ሁኔታ በግል እንደሚገናኛቸው ተገልጾአል:: እነዚህ የተለያዩ አስተምህሮዎች በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፊው ተመዝግበዋል:: ቀጥለን በመጀመሪያ ቁርአንን በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እንሄዳለን::

## ቁርአን

በደቡባዊ ሶማሊያ በጀማማ ውስጥ በምትገኝ መንደር ግብዣ ላይ እንዳለን ሶማሊያዊ የሆነው እንግዳ፣ "ይህቺ ምሽት ከዐሥር ሺህ ምሽቶች ትበልጣለች" አለ:: ምሽቱ የረመዳን ጾም ፍቺ (ኢድ አልፈጥር) ቀን ነበር:: ተናጋሪው አስተናጋጃችንና ሌሎች ሶማሌያውያን ከአምስቱ የእስልምና የእምነት ተግባራት ውስጥ አንዱ የሆነውን የረመዳን ጾም፣ ለአንድ ወር በታማኝነት ጾመው ጾሙን የሚያሳርጉበት ቀን ነበር::
የተዘጋጀውን ምግብ በኅብረት ከመቋደሳችን በፊት፣ ጋባዣችን ስለበዓሉ ደስታ በተሞላ አነጋገር እንዲህ አለ:— "ይህ ምሽት ከዐሥር ሺህ ምሽቶች ይበልጣል! በዚህ ምሽት ቁርአን ከሰማይ መውረድ የጀመረበትን ቀን እናስባለን::

[6] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 67.



የሮመዳን ጾምም የእግዚአብሔር መልእክት መገለጥን ስጦታ ወደ ፊት እንድንመለከት ያደርገናል:: ዛሬ በዚህ ምሽት ቀኑን የምናከብረው መልእክቱ ከሰማይ ወደ ምድር በመምጣቱ ነው:: ስጦታውም አሁን በእጃችን አለ፤ እርሱም ለሰዎች ሁሉ መመሪያ የሆነው ቁርአን ነው":: ቁርአን በሱራ 2+185 እንዲህ በማለት ያውጃል:—

> (እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች አንቀጾች ሲሆን፣ ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፤ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፤ በሺተኛ ወይም በጉዞ ላይ የሆነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቍጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፤ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፤ በናንተም ችግሩን አይሻም፤ ቍጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህንን ደነገግንላችሁ)":: (በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

እንዲሁም በሌላ ስፍራ:—

> እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛዪቱ ሌሊት አወረድነው:: መወሰኛዪቱም ሌሊት ምን እንደ ሆነች ምን አሳወቀህ? መወሰኛዪቱ ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት (ሱራ 97+1-3 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

የእግዚአብሔር መልእክት ከሰው ልጆች ግምት በላይ የሆነ እውነት እንደ ሆነ ቁርአን ያስተምራል:: ተራሮች የቁርአን መልእክት ቢያርፍባቸው እግዚአብሔርን ከመፍራታቸው የተነሣ ይሰነጠቃሉ (ሱራ 59+21):: እንደ እስልምና አስተምህሮ ይህ እውነት ነው አማኞችን ከማያምኑ ሰዎች የሚለያቸው እንዲሁም እውነተኛ አማኞች ቁርአን ሲነበብ ለእግዚአብሔር በፍርሓትና በመንቀጥቀጥ ይሰግዳሉ (ሱራ 84+20-22)::

ሙስሊሞች እግዚአብሔር በተለያየ ዘመናት በመላእክት አማካይነት ለሰው ልጆች መልእክት ልኮአል የሚል እምነት አላቸው:: መልአኩ ገብርኤል (ጅብሪል) የመጨረሻ መልእክት የሆነውን ቁርአን ለመሐመድ አምጥቶአል:: መልአኩ ገብርኤል በተገለጠ ጊዜ መሐመድ ፈርተው ነበር:: ገብርኤል በ610 ዓ.ም ለመሐመድ ሲገለጥላቸው፣ መሐመድ በሒራ ዋሻ ውስጥ ነበሩ:: መልአኩም ወደ እርሳቸው ቀርቦ እንዲህ ሲል አዘዛቸው:—

> አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታ ስም:: ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም):: አንብብ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ ያ በብዕር ያስተማረ፤ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን (ሱራ 96+1-5 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሐመድ የተገለጠላቸው ቃል፣ "አንብብ" የሚል ነበር። ቁርአን የሚለውም ቃል ትርጉም "አንብብ" ማለት ነው። ሙስሊሞች፣ ቁርአን በሰማይ የመጻሕፍት ሁሉ እናት (ኡም አል-ኪታብ) ከተባለው መጽሐፍ የተወሰደ ንባብ እንደ ሆነ ያምናሉ (ሱራ 13÷39)። ለመጀመሪያ ጊዜ ከመጣው መልእክት በኋላ፣ መልአኩ ገብርኤል ወደ መሐመድ በየጊዜው እየመጣ የቀሩትን የሰማያዊውን መጽሐፍ ክፍሎች ያስተምራቸው ነበር። በቁርአን ውስጥ ያሉ መገለጦች ከመልአኩ ገብርኤል በስተቀር በሌላ እንዳልመጡ ቁርአን ያስተምራል[7]።

መሐመድ ከመልአኩ ገብርኤል የመጣላቸውን መልእክት በታማኝነት ምንም ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ ለተከታዮቻቸው ያነቡላቸው እንደ ነበር ሙስሊሞች ያምናሉ። ተከታዮቻቸውም የመልእክቱን አብዛኛ ክፍል በአእምሮአቸው የያዙት ሲሆን፣ የተወሰነውን ክፍል ደግሞ ጽፈው አስቀምጠውታል። ይህንንም ተግባር በታማኝነት መፈጸም ትልቅ ኀላፊነት ነበር። የመሐመድ ተከታዮች እያንዳንዱ ጥቅስ (አያህ) መሓሪ ከሆነው ፈጣሪ ወደ ምድር የተላከ መልእክት እንደ ሆነ ያምናሉ። የቁርአን አጠቃላይ መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ መሐመድ የመጣው፣ መሐመድ ለሃያ ሁለት ዓመት በምድር ላይ በነበራቸው በአገልግሎት ዘመን ጊዜ ነበር። እያንዳንዱ የቁርአን ምዕራፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነበበው ደግሞ በመሐመድ ነው።

የቁርአን ምዕራፎች ተሰብስበው የተጻፉት፣ እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ653 ዓ.ም በካሊፍ ኡስማን ዘመን ነው። ይህም ነቢዩ መሐመድ ከሞቱ ከሃያ ዓመት በኋላ ማለት ነው። በዚያን ጊዜ የነበሩ ሌሎች አማራጭ የእጅ ጽሑፎች ተቃጥለዋል። ከዚህም የተነሣ ጥንታዊ አማራጭ የቁርአን እጅ ጽሑፎችን በንጽጽር ለማጥናት አልተቻለም።

ቁርአን ከ1.2 ቢሊዮን ለሚበልጡ የዓለማችን ሙስሊሞች የሕይወት መመሪያ ነው። ሙስሊሞች ለቁርአን እጅግ ትልቅ ክብሬታ አላቸው። በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሙስሊሞች፣ የቁርአንን መልእክት ቃል በቃል በአእምሮአቸው ይይዛሉ። ሁሉም የሶማሌ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከመጀመራቸው በፊት የተወሰኑትን የቁርአን ምዕራፎች በቃላቸው ያጠናሉ።

[7] Nahl (The Bee) 16:103. Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge: Harvard University Press, 2001), 20-21. Najm (The Star) 16:19-23; Haff (The Pilgrimage) 22:52-53. George W. Baswell Jr., *Islam: Its Prophet, Peoples, Politics, and Power* (Nahville: Broadman & Holman Publishers, 1996), 45.



በሌላ ስፍራ የሚገኙ ሙስሊሞችም ተመሳሳይ ልማድ አላቸው። እያንዳንዱ የቁርአን ጥቅስ (አያህ) የተቀደሰ ነው። በዐረብኛው ቋንቋ "አያህ" ማለት ምልክት ማለት ነው። እንደ እስልምና አስተምህሮ ፍጥረት ለእግዚአብሔር አልሆት ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቁርአንም የእግዚአብሔር የተከበረ ምልክት ነው። ሕፃናት የቁርአንን ጥቅሶች (አያህዎች) በቃላቸው ባጠኑ መጠን፣ የአላህ የምልክቶቹ ምስጢርና ተአምራቶች በአእምሮአቸው ውስጥ ይቀረጻል የሚልም አስተሳሰብ አለ።

ቁርአን ቤት ውስጥ ካሉ ዕቃዎች በተለየ ሁኔታ ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል። ማንኛውም ሰው ቁርአንን ለመያዝ ሃይማኖታዊ ዕጥበት ማካሄድ አለበት። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳችም ጽሑፍ እንዲሁም ምልክት መጻፍ የተከለከለ ነው። ቁርአንን ከእናት ቋንቋው ከዐረብኛ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጐም የተከለከለ ሲሆን፣ ቢተረጐም እንኳ የተተረጐመው የቍርአን ቅጅ እንደ ቅዱስ ቁርአን አይታይም። የቁርአን ምዕራፎች በየቀኑ በዓለም ዙሪያ በሚደረጉ የአምልኮተ ስግደት (የሰላት) ሥርዐቶች ወቅት ይነበባሉ። ቁርአን የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሠረት ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ተጽፈው የተጠናቀቁት በአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። የመጻፉ ሥራ የተጀመረው በሙሴ ሲሆን፣ የተፈጸመው ደግሞ በዮሐንስ ዘመን ነው። ከአብርሃምና ከእስራኤል ታሪክ ጅማሬ እስከ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ያለው ዘመን ደግሞ፣ ሁለት ሺህ ዓመት ያህል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲረዱና እግዚአብሔር በመካከላቸው ስላደረገው ታሪክ የሚተርክ እንዲሁም የነገረ መለኮት አስተምህሮ መጽሐፍ ነው። በውስጡ ያሉ ታሪኮች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራቸውን ሥራዎች የሚያስተዋውቁ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል ታሪክ በሕዝቦች ታሪክ ላይ የሚያጠነጥን ነው (ዘፍጥረት 1-11)። ታሪኩም ዓለም ዐቀፋዊ የሆነ ታሪክ ነው። ለምሳሌ የአዳምና የሔዋን ታሪክ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ታሪክ እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ያምናሉ። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረናል። እኛ ሁላችንም የተገኘነው ከአዳምና ከሔዋን ነው። ስለዚህ ሁላችንም ሰብአዊ ፍጡሮች ነን። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የሰው ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፆአል፤ ኀጢአትም በሰዎች ሕይወትና ኑሮ እንዲሁም በሚኖሩባት ዓለም ላይ ነግሠ።

ሁለተኛው ዐይነት ታሪክ እግዚአብሔር ሰውን ሲጠራና ተስፋ ሲሰጥ የሚያሳይ ነው (ዘፍጥረት 12-50)። በእነዚህ ምዕራፎች እግዚአብሔር አብርሃምን ከሕዝቡ ተለይቶ እንዲወጣ እንዳዘዘው፣ የአሕዛብ ሁሉ አባት እንደሚሆን እንዲሁም አሕዛብ ሁሉ በእርሱ በኩል እንደሚባረኩ የሚገልጹ ታሪኮች ተዘግበዋል። በዘፍጥረት 12-50 ያለው ክፍል ደግሞ ከአብርሃም የተገኙት ሦስት ተከታታይ ትውልዶች፣ ለእግዚአብሔር ጥሪ በመታዘዝ ያለፉበትን የሕይወት ጉዞና የሚዳስስ ነው። ይህ የሕይወት ጉዞም ለሕዝበ እስራኤል ማንነት መሠረት የጣለ ነበር።

ሦስተኛው ታሪክ እግዚአብሔር እስራኤልን መርጦ ለዓለም ሕዝብ ብርሃን በማድረግ፣ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣ ከዘፀአት እስከ ዘዳግም ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚተርክ ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ የፈርዖን ቀንበር ዐርነት በማውጣት፣ በሲና ተራራ ላይ ተገናኛቸው። ስለዚህ የሙሴ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት መጻሕፍት እግዚአብሔር አብርሃምንና ቤተሰቡን እንዴት እንደ ጠራቸውና እንዴትስ እንደ መራቸው እንዲሁም እስራኤልን በምድረ በዳ በመምራት ከእርሷ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን የሚተርክ መጽሐፍ ነው።

አራተኛው ታሪክ ከኢያሱ እስከ ግዞት ዘመን ያለውን የታሪክ ጊዜ የሚያጠቃልል ሲሆን፣ እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር እንዴት እንደ ወረሱ እንዲሁም እንደ አገር ራሳቸውን መምራት እንደ ጀመሩ የሚያሳይ ነው። ስምንት መቶ ዓመት የሚሆነው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ራሱንና ሥራውን ይፋ ያደረገበት የታሪክ ጊዜ ነው። በእነዚህ ዘመናት እስራኤላውያን እንደ ቃል ኪዳን ሕዝብ በተለያዩ ጦርነቶችና ወረራዎች ውስጥ እንዴት እግዚአብሔርን አክብረውና አስከብረው መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር አስተምሯቸዋል። በተጨማሪም እስራኤል እንደ አገር እንዴት መመሥረት እንዳለባት፣ ስለ አስተዳደር፣ ስለሌሎች አማልክት፣ ስለምጣኔ ሀብት፣ ስለሃይማኖታዊ ሥርዐቶች፣ ስለፍትሕ፣ ስለድኾችና፣ ስለመጻተኞች የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ የተገለጠበት ጊዜ ነው። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተማሩት ያለኀጢአት ሆነው አልነበረም። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዲሁም ጸጋ እንዲቀበሉ ምክንያት ሆኖአል።

አምስተኛው ታሪክ ስለምርኮና ከምርኮ መልስ ያለውን የእስራኤላውያንን ሕይወት የሚዳስስ ነው። ይህ ወቅት ብዙ ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች የተነሡበት ጊዜ ነበር። ብዙ የነቢያት መጻሕፍትም የተጻፉት በዚህ የታሪክ ጊዜ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ በሌሎች ሕዝቦች ተሸንፈው፤ ቤተ



መቅደሳቸውም ፈርሶ ወደ ግዞት አገር እንዴት ሊወሰዱ ቻሉ? ክርስቲያኖች ለወንጌል ያላቸው የመከራ ነገረ መለኮት መሠረት ያገኘው በዚህ የታሪክ ጊዜ ከተፈጸሙት ታሪኮች ነው።

እነዚህ አምስት የታሪክ ዘመናት የተጻፉት እንዲሁም ነገረ መለኮታዊ ትርጓሜ የተሰጣቸው ብሉይ ኪዳን ተብሎ በሚጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ አጋማሽ ክፍል ነው። ከዚህ በመቀጠል ስድስተኛውን ታሪክ የምናገኘው አዲስ ኪዳን ተብሎ በሚጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ አጋማሽ ክፍል ውስጥ ነው።

ስድስተኛው ዘመን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና አገልግሎት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ የተካሄደበት ዘመን ነው። በክርስቶስ ሕይወት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሆኑ የነበሩት ነገሮች፣ እግዚአብሔር አብርሃምን ከጠራበት ጊዜ አንሥቶ ለነበሩት ጊዜያት ቀጣይ ክፍል ነው። ከመሲሑ ምጽአት በፊት የነበሩት ትንቢቶች፣ ስለመሲሑ መምጣት የተነገሩትን ተስፋዎች በዋነኛነት የያዙ ናቸው:— "ሠረገላውንም ከኤፍሬም ፈረሱንም ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ፤ የሰልፍም ቀስት ይሰባል፤ ለአሕዛብም ሰላምን ይናገራል፤ ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፤ ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይሆናል" (ዘካርያስ 9+10)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች በርካታ ገጽታ አላቸው። ከሠላሳ ያላነሡ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን የተወሰኑ ክፍሎች ጽፈዋል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን፣ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት የተለያየ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ያላቸው ናቸው። ከእነዚህም ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች መኻል ታሪክ፣ ቅኔ፣ ግጥም፣ ትንቢት፣ አቡቀለምሲሳዊ፣ የማጽናናትና የግሣጼ ደብዳቤዎች ዋነኛውን ቦታ ይይዛሉ።

ብዙ ሰዎች ታሪካዊ ጽሑፎች ተአማኒ ናቸውን? በሚለው ጉዳይ ላይ፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሣሉ። የብሉይ ኪዳን ታሪኮች የተጻፉት በዚያን ዘመን ከእስራኤል ውጪ የነበሩት ሕዝቦች ትክክለኛ ታሪክ ለመዘገብ ምንም ዐይነት ትኩረት በማይሰጡበት ጊዜ ነው። አንዳንድ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለታሪክ ትኩረት የማይሰጡበት ዐቢይ ምክንያትም ታሪክ ትርጒመ ቢስ ድግግሞሽ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ታሳቢ ስለሚያደርጉ ነው። የቻይና ነገሥታትን የመሰሉ ጥቂት ሰዎች፣ ስለአገራቸውና ስለሕዝባቸው ታሪክ በመጻፍ ትክክለኛውን ታሪክ ለማሳየት ሞክረዋል። ቻይናውያን የአገራቸውን ታሪክ በመጻፍ በአገሪቱ ጥሩ መሪዎች በተነሡበት ወቅት ለአገሪቱ የስኬት ዘመን

እንደ ነበር፤ በእንጻሩ ደግሞ ክፉ መሪዎች በተነሡበት የታሪክ ዘመን መከራ ወደ ሕዝቡ እንደ መጣ አሳይተዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች የተለያየ ይዘት አላቸው። ታሪኮቹም በእያንዳንዱ ትውልድ የተፈጸሙትን ክሥተቶች ይዘግባሉ። ዘገባዎቹ እውነተኛ ታሪኮች ሲሆኑ፣ የሰዎችን ሠናይና እኩይ ምግባራት የሚይዙ ናቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔር እንደ ልቡ ብሎ የጠራው ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት መፈጸሙን እንዲሁም የቤርሳቤህን ባል እንዳስገደለ ተጽፎአል። የሃያኛው ምዕተ ዓመት የከርሰ ምድር ጥናት ተመራማሪዎች፣ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን እውነተኛነት በጥናታቸው ለማረጋገጥ ችለዋል። ዊሊያም አልብራይት የተሰኘው የሃያኛው ክፍለ ዘመን ዕውቅ የከርሰ ምድር ተመራማሪ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች፣ ስለጥንታዊው ዘመን ከሚናገሩ ታሪኮች ሁሉ ይልቅ እጅግ ተአማኒ የሆኑ ታሪኮች እንደ ሆኑ ተናግርአል[8]።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍያን፣ የታሪክ ክሥተቶችን እውነተኛነት ለመጠበቅ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡበት ዐቢይ ምክንያት ምንድን ነው? ጸሐፍያኑ እግዚአብሔር በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ እያደረገ እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት እየተቈጣጠረ እንዳለ ፈጽመውና ጨልጠው በማመናቸው ነው። በዚህ ዐይነቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ውስጥ የተጻፈ መጽሐፍ ለሰው ልጆች ሁሉ ትልቅ ትርጕም ያለው መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የነበሩት እስራኤላውያን ይህን እምነት በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ይፋ ያደርጉ ነበር። ከዚህም የተነሣ የእስራኤል ታሪክ በጥንቃቄ ተዘግቦአል።

በጥንት ዘመን የነበረው ይህ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ፣ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ያለ ስሕተትና ብልሽት የጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ቅጆች መሆናቸውን የሚያረጋግጡልን ናቸው። በሌላ አንጻር ግን ቁርአን ነቢዩ መሐመድ ከሞቱ ከ20 ዓመታት በኋላ በካሊፍ ኡስማን ዘመን ዘይድ ካዘጋጀው ቁርአን በስተቀር ሌሎች ሰዎች ያዘጋጅዋቸው ቁርአኖች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል። ነገር ግን በሺዎች የሚቈጠሩ ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን አባቶች ተአማኒነት የላቸውም ብለው ያወገዟቸውን መጻሕፍትንም የሚጨምር ነው።

[8] W. F. Albright, *From the Stone Age to Christianity* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 45.



የብሉይ ኪዳንን ተአማኒነት በተመለከተ የሙት ባህር ጥቅሎች ዐይነተኛ መረጃ ይሰጣሉ። የሙት ባህርን ጥቅል ያገኙት እረኞች ሲሆኑ፣ እንደ ጐርጐርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1947 ዓ.ም በሙት ባህር አካባቢ ባለ ዋሻ ውስጥ ከሁለት ሺህ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተገኝተዋል።

በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በርካታ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ከተለያዩ ቦታዎች አግኝተዋል። በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ አምስት ሺህ የሚሆኑ እጅግ ጥንታዊ የሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅጆች በእጃችን አሉ። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀምጠው የተገኙበት ሁኔታ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ለምሳሌ ሰባ አምስት የሚሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች የተገኙት፣ እንደ ጐርጐርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1897 ዓ.ም በግብፅ አገር ኦክሲርንቾስ በተባለው ቦታ፣ መጻሕፍቱ እንዳይበላሹ በዐዞ ቈዳ ተጠቅልለው በክብር ከተቀመጡበት ስፍራ ነው። ከእነዚህም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ አንዱ የዮሐንስ ወንጌል ሲሆን፣ ይህም መጽሐፍ እንደ ጐርጐርሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ135 ዓ.ም የተጻፈ እንደ ሆነ ይገመታል። እነዚህ ጥንታዊ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ትክክለኛና ተአማኒነት ያለውን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለንባብ እንዲያቀርቡ ረድቶአቸዋል። ኤፍ. ጂ. ኤ. ሆርት የተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር በእጃችን ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት፣ ቀደምት/አንጋፋ (ኦርጅናል) ከሆነው መጽሐፍ ጋር ሲነጻጸሩ፣ ከአንድ ሺህ ንጽጽሮች ውስጥ ምናልባት አንድ ልዩነት ቢገኝባቸው እንጂ፣ ከዚያ ያለፈ ልዩነት ሊገኝባቸው በፍጹም አይችልም የሚል አስተያየት ሰጥተዋል[9]።

እነዚህ ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች፣ ቀደምት/አንጋፋ የሚባሉት ጽሑፎች አሁን በእጃችን ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ጋር ሲነጻጸሩ የተለየ ይዘት እንደሌላቸው የሚያረጋግጡ ናቸው። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች አሁን የምንጠቀምባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች፣ ከጥንታዊ ጽሑፎች ጋር ልዩነት ቢፈጥሩ እንኳ ጥንታውያኑ መጻሕፍት በእጃችን እስካሉ ድረስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህን ችግር ለማስወገድ የክለሳ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ። ያልተዛባና ያልተዛነፈ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የነገረ መለኮት ምሁራን ቀዳማይ ዐላማ ነውና።

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። መሲሑ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው ያምናሉ። ይህ

[9] Sean Kealy, *The Changing Bible* (Nairobi: KUC, n.d.). 87.

ማለት ምን ማለት ነው? የድነት ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ርእሰ ጉዳዮች መኻል ዋነኛው ርእስ ነው። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር በመሲሑ በኢየሱስ በኩል ሰዎችን እንዳዳነ ያስተምራሉ። በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ለዘላለም ሕያው ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ማለትም ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ኅብረት እንድናደርግ ምሪት ይሰጠናል።

መሲሑ ኢየሱስ እንዲህ ብሉአል:—

> እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም (ዮሐንስ 5+39-40)።

## ሙስሊሞችና የቀደሙት መጻሕፍት

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ግራ ይጋባሉ። ይሁን እንጂ ቁርአን ሙስሊሞች ሁሉ በቀደምቶቹ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲያምኑ ያዛል። ቁርአን ቀደምቶቹን መጻሕፍት በአራት ይከፍላቸዋል።

1. ሱሐፍ (የተወሰኑ ገጾች):— ለአብርሃም የተሰጠው መገለጥ ሲሆን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጠፍቶአል።
2. ተውራት (ቶራህ):— ለነቢዩ ሙሴ የተሰጠ መገለጥ ነው።
3. ዘቡር (መዝሙራት):— ለንጉሥ ዳዊት የተሰጠ መገለጥ ነው።
4. ኢንጂል (ወንጌል):— ለመሲሑ ኢየሱስ የተሰጠ መገለጥ ነው።

ሙስሊሞች ሁሉ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት መልእክቶች፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች የተሰጡ መገለጦች እንደ ሆኑ ያምናሉ። በተጨማሪም እነዚህን መጻሕፍት ማንኛውም ሰው እንብቦ ይጠቀምባቸው ዘንድ ክርስቲያኖች ለሰው ልጆች ሁሉ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው ቁርአን ያዛል[10]።

[10] በኬንያና በሶማሊያ የሚገኙ ክርስቲያኖች ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ናቸው የሚላቸውን መጻሕፍት ማለትም አምስቱ የሙሴ መጻሕፍትን፣ መጽሐፈ መዝሙርንና ወንጌላትን ለሙስሊሞች እያዘጋጁ ያቀርባሉ። በዚህም ጥናት ውስጥ በርካታ ሙስሊሞች መሲሑ ማን ነው? እንዲሁም ተልእኮውስ ምን ነበር? የሚሉትን መሠረታዊ ነጥቦች በውል እንዲገነዘቡ ያደረገ ሲሆን፣ ይህም ጥናት አርባ በሚበልጡ ቋንቋዎች እንዲተረጉም ተደርጎአል። በየዓመቱም በሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች



እንደ ሙስሊሞች እምነት፣ ከእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በኋላ እግዚአብሔር የመጨረሻው መልእክት የሆነውን ቁርአንን፣ በነቢዩ መሐመድ በኩል ይፋ አድርጎአል፤ እንዲሁም ቁርአን ከእርሱ በፊት ለነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ማጠቃለያ እንዲሁም እነዚህን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳ ሙስሊሞች ለአብርሃም የተሰጠው መገለጥ (ሱሐፍ) ጠፍቶአል የሚል እምነት ቢኖራቸውም፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች (የመጽሐፉ ሰዎች) እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይጠፉ እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቀው አቆይተዋል። ቁርአን የመጨረሻው መልእክት እንዲሁም የቀድሞዎቹን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ ነው የሚል እምነት ቢኖርም እንኳ፣ ለቀድሞዎቹ መጻሕፍት ትልቅ አክብሮት እንዳለው ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ቁርአን እነዚህ መጻሕፍት የክርስቲያኖችም ሆነ የአይሁዶች እምነትና ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያስተምሩ እንዲሁም ለሰው ዘር ሁሉ፣ "መመሪያና ብርሃን" የሚፈነጥቁ መጻሕፍት መሆናቸውን በግልጽ ያስተምራል (ሱራ 5+44-47)።

ቁርአን ሙስሊሞችንም ሆነ ነቢዩ መሐመድን እንዲህ ሲል ያዛቸዋል:—

> ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፤ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል፤ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን (ሱራ 10+94)።

በሌላ ስፍራም ቁርአን ለሙስሊሞች:—

> እላህ የነዚያን መጽሐፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ፣ አትደብቁትምም በማለት የያዘባቸውን (አስታውሱ) (ሱራ 3+187 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ነገር ግን ቁርአን ለሙስሊሞችና ለመሐመድ እነዚያ የመጽሐፉ ሰዎች (ክርስቲያኖችና አይሁዶች):—

> "አላህም ወደ አንተ ካወረደው ከከፊሉ እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቃቸው" (ሱራ 5+49 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ትምህርቱን እንዲከታተሉ ዕድል ሰጥቶአቸዋል። ለትምህርቱም ያላቸው ፍላጎትና አቀባበል እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ክርስቲያኖች ደግሞ፣ ይህን የሙስሊሞችን የቃለ እግዚአብሔር ፍላጎት ለማርካት፣ ለሕፃናት በየቀኑ የሚጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በሥዕል እያስደገፉ ማቅረብ በመቻላቸው፣ በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ታትመው በክልሉ እንዲሠራጩ ተደርጎአል።

በማለት ያስጠነቅቃል። ቁርአን ከመጽሐፉ ሰዎች (ክርስቲያኖችና አይሁዶች) ውስጥ የአንዳንዶቹን ሥራ ቢቃወምም፣ ለመጽሐፉ ሰዎች አክብሮት አለው። የመጽሐፉ ሰዎችም መጻሕፍቶቻቸውን በጥንቃቄ እንዲጠብቁ እንዲሁም ማንኛውም ሰው የመጻሕፍቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ በሮችን መክፈት እንዳለባቸው ያዛል[11]።

## ተበላሽቶአልን?

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መገለጥ እንደ ሆነ ቢያምኑም፣ ቁርአንንና መጽሐፍ ቅዱስን ማስታረቅ በእያሌው ይቸግራቸዋል። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ኢብራሂም የተባለው ሰው በክርስትና ውስጥ ካሉ ዋና ዋና ችግሮች መካከል አንዱ፣ መጽሐፍ ቅዱስ "የመበላሸቱ" ጉዳይ እንደ ሆነ ተናግሮ ነበር። ኢብራሂም መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ከሚለው አስተሳሰቡ በተጨማሪ፣ ሌሎች ጥያቄዎችም ነበሩት። ኢብራሂምን ካስጨነቁ ነገሮች መኻል አንዱ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋንኛ ክፍል ታሪክ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ታሪክ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለው ጉዳይ ደግሞ የበርካታ ሙስሊሞች ጥያቄ ነው።

የኢብራሂም ሁለተኛው ጥያቄ፣ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ሊታረቁ የማይችሉ እጅግ ብዙ ልዩነቶች አሉ የሚለው ነጥብ ነው። በኬንያ በሚገኘው ኬንያታ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሙስሊሞች ጋር ያደረግነው ውይይት ይህን ችግር የሚያስረዳ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ እኔና ጃማ ሑሴይን የዓለም ሃይማኖቶች የሚል ትምህርት በዚሁ ዩኒቨርስቲ ስናስተምር፣ አንድ ተማሪ ጃማ ሑሴይንን እንዲህ ሲል ጥያቄ ጠየቃቸው:—

> ሁሉም ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ማመን አለባቸው ብለሃል። ነገር ግን በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ አራቱ ወንጌላት የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ቁርአን ኢየሱስ እንደ ሞተና ሞትንም ድል አድርጎ እንደ ተነሣ ይክዳል።

ጃማ ሑሴይን ለተማሪው እንዲህ ሲል መለሱለት:—

> በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ልዩነት የመጣው መጽሐፍ ቅዱስ በመበላሸቱ ምክንያት ነው። ሙስሊሞች በአንጋፋው (በኦርጅናሉ) መጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን፤ ነገር ግን አሁን በተበላሸውና በክርስቲያኖችም እጅ በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ አናምንም።

[11] ከዚህ በላይ ያለውን የግርጌ ማስታወሻ ይመለከቷል።



እኔም ለጃማ ሑሴይን የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብሁ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ብለው የሚናገሩት ከምን መረጃ ተነሥተው ነው?"። ጃማ ሑሴንም፣ "ከቁርአን መረጃ ተነሥቼ ነው፤ ቁርአን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳበላሹት ያስተምራል" ሲሉ መለሱልኝ። እኔም፣ "ቁርአን ይህ ዐይነቱን ነገር የሚያስተምረው በየትኛው ክፍል ነው?" ስል ጠየቅሁ። ጃማ ሑሴይንም፣ "የየትኛው የቁርአን ክፍል ይህ ዐይነቱን ትምህርት እንደሚያስተምር ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በኋላ በትክክል አመላክትሃለሁ" አሉኝ።

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ከተጠናቀቀ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቢሮአቸው ወስደውኝ፣ በስፋት የሚታወቀውን የሚከተለውን የቁርአን ክፍል ለትምህርታቸው ማጠናከሪያነት አሳዩኝ:—

> ከእነርሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን፣ ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልሆነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ። እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ (ሱራ 3+78)።

እኔም ለጃማ ሑሴይን እንዲህ ስል ጥያቄ አቀረብሁ:— "እስካሁን ድረስ እኔም ሆንሁ እርስዎ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በምላሳችን ጠቅሰነው አናውቅምን? ታዲያ ይህ የቁርአን ክፍል ይህ ዐይነቱ ስሕተት እንዳይፈጠር የሚያስጠነቅቅ አይደለምን? እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ይህን ክፍል በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ማለት ትክክል አይመስለኝም፤ ክፍሉ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ቅንጣት ታህል ፍንጭ የለውም"።

በእርግጥ ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር ይናገራሉ። ቁርአን፣ "የአላህም ንግግሮች ለዋጭ የለም" (ሱራ 6+34) ሲል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ "አቤቱ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል" (መዝ 119+89) ይላል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ በዓለም ዙሪያ የሚገኘው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ፣ አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት የጐደለው መጽሐፍ ነው

የሚል አመለካከት አለው:: ጃማ ሑሴይን የተናገሩትም ንግግር በየመስጊዱ ከሚነገረው ንግግር ቅንጣት ታህል የተለየ አይደለም::

## ክርስቲያኖችና ቁርአን—ሙስሊሞችና መጽሐፍ ቅዱስ

ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አመኔታ ማጣታቸውና ማንቋሸሻቸው ክርስቲያኖችን በእያሌው ያሳዝናቸዋል:: በክርስቲያኖች እይታ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ላለማመናቸውና ለማንቋሸሻቸው በቂ የሆነ ቁርአናዊ መረጃ የለም የሚል ጽኑ አቋም አላቸው:: ይሁንና ቁርአንን የማብራራቱና የመተርጎሙ ሥራ የሙስሊሞች ኀላፊነት ነው:: ክርስቲያኖች ስለቀድሞዎቹ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ስለሌሎች ርእሰ ጉዳዮች የራሳቸውን አመለካከት በቁርአን ላይ መጫን ያለባቸው አይመስለኝም::

ይሁን እንጂ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ቁርአን ስለቀድሞዎቹ መጻሕፍት የሚያስተምረውን ትምህርት በሚገባ ማወቅ አለባቸው:: ቁርአን ስለቀድሞዎቹ መጻሕፍት ሁለት ትልልቅ ትምህርቶች አሉት::

1. የቀድሞዎቹ መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መለኮታዊ መገለጦች ናቸው::
   "ከርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን (ቁርአንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ:: ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል" (ሱራ 3+3 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

   > ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን (ሱራ 5+48)::
   >
   > እላንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው (ሱራ 5+68 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::
   >
   > ለሙሳንና ለሃሩንም እውነትንና ውሸትን የሚለይን ብርሃንንም ለጥንቁቆችም መገሠጫን በእርግጥ ሰጠናቸው (ሱራ 21+48፤ 10+64)::
   >
   > የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፤ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው፣ እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው (ሱራ 5+47፤ 11+17፤ 21+48)::



"የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም" (ሱራ 10+64)::

ወንጌልን በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> በፍላጉታቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፤ እንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው (ሱራ 5+46 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

እንዲሁም ቁርአን ነቢዩ መሐመድን እንዲህ ሲል ይመክራል:—

> ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ (ሱራ 10+94)::

አንዳንዴ ቁርአን የእግዚአብሔርን ቃል ማንም ሊያበላሸው እንደማይችል ያስተምራል:: ቀጥሎ ያለው የቁርአን ክፍል ይህንን እውነት ያረጋግጣል:—

> ከበፊትህም መልእክተኞች በእርግጥ ተስተባበሉ፣ በተስተባበሉብትም ነገርና በተሠቃዩት ላይ እርዳታችን እስከመጣላቸው ድረስ ታገሡ፤ የአላህም ንግግሮች ለዋጭ የለም፤ ከመልእክተኞቹም ወሬ (የምታረጋጋበት) በእርግጥ መጣልህ (ሱራ 6+34 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

2. የመጽሐፉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ማክበርና በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው::

ቁርአን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያበላሹት፣ እንዳይደብቁት፣ ለጥቅም ብለው እንዳይለውጡት እንዲሁም ከዐውደ ምንባቡ ውጪ እንዳያብራሩት ይመክራል:—

> አላህ የነዚያ መጽሐፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ አትደብቁትምም፣ በማለት የያዘባቸውን (አስታውሱ) (ሱራ 3+187 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

እንዲሁም:—

> ከነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መሆኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ:: እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልሆነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ:: እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ (ሱራ 3+78)::

> የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሸት ለምን ትቀላቅላላችሁ? እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ ለምን ትደብቃላችሁ (ሱራ 3፥71)።

> ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ወዮላቸው፤ ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው፤ ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኀጢአት) ወዮላቸው (ሱራ 2፥79 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

በእርግጥ ቁርአን ስለራሱ የመጨረሻ መልእክት እንዲሁም የቀድሞዎቹን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ሙስሊሞች ወደ መጽሐፉ ሰዎች ሄደው ለሕይወታቸው የሚጠቅማቸውን ምክር እንዲጠይቁአቸው ያዛል።

በአንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ከሙስሊሞች ጋር በነበረኝ ውይይት ለሙስሊም ወዳጆቼ፣ "ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን አበላሽተዋል እያላችሁ አትክሰሱ። ይልቁንም ከእኛ ጋር ቁጭ ብላችሁ የመጽሐፍ ቅዱሱን ትምህርት ከእኛ ልትሰሙ ይገባል። ቁርአን የሚያስተምራችሁ ይህን እንድታደርጉ ነው" በማለት ቃለ እግዚአብሔርን በኅብረት እንድናጠና ጥሪ አደረግሁላቸው።

በተቃራኒው ሙስሊም ባልንጀራዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ:— "እኛ እናንተን መስማት እንዳለብን ይገባናል፤ ነገር ግን እናንተ የምትመክሩንን ምክር ሁሉ እንዳንቀበል ቁርአን ያስተምረናል። ምክንያቱም እናንተ ሙስሊሞችን ልታሳስቱ ትችላላችሁና"።

ሙስሊም ጓደኛዬ እንደ ተናገረው ሙስሊሞች ወደ ክርስቲያኖች እንዲሄዱ እንዲሁም ክርስቲያኖች ስለመጽሐፋቸው ማብራሪያ እንዲሰጥዋቸው ታዟል። እንዲሁም ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ምክር ከእውነተኛው የእስልምና እምነት እንዳይስቱ ቁርአን ያስተምራል። ይህ እንዳለ ሆኖ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር በሚያደርጉት ውይይት የታዘብነው ቀዋም ነገር ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ያላቸው መረጃ ፍጹም የተዛባ መሆኑን ነው።

በጀርመን አገር ዳግም መጥምቃውያን ከሙስሊሞች ጋር በነበረን ውይይት ላይ ከሙስሊሞች በኩል የእስልምናን አመለካከት ያቀረበው ምሁር፣ "የእስልምና ነገረ መለኮት ምሁር እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ የሆነ ሙስሊም ሰው



ታውቃለህ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። እርሱም፣ "እንደዚህ ዐይነት ሙስሊም መኖሩን ሰምቼ አላውቅም" ሲል ነበር መልስ የሰጠው።

እስካሁን ድረስ በየትኛውም የሙስሊም ዩኒቨርስቲ የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የክርስትናን አስተምህሮ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ አልተከፈተም። በተቃራኒው ግን ብዙ የክርስቲያን ዩኒቨርስቲዎች እስልምናንና ቁርአንን የሚያጠና የጥናት ዘርፍ አላቸው። እንዲሁም በቁርአን ትምህርት በጣም የተካኑና የተከበሩ በርካታ ክርስቲያን ሊቃውንት አሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ስለእስልምና ማብራሪያ እንዲሰጡ በሙስሊሞች እንኳ ሳይቀር በርካታ ግብዣዎች ይቀርብላቸዋል።

በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ይህ ዐይነቱ ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የምናገኘው በሚቀጥለው ምዕራፍ ሲሆን፣ ስለ "ታንዚል" (ከሰማይ የወረደ መልእክት) እና ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ (ተሰግዎ) በስፋት እንዳስሳለን።

## ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ አመለካከቶች

በለንደን ከተማ ደቡባዊ ክፍል በሚገኘው መስጊድ ውስጥ፣ ለነበረው በመቶ ለሚቈጠር ሕዝብ የሙስሊሞቹ ተወካይ፣ "ዳዊት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልሆነ ገልጾአል" ሲል ተናገረ። እኔም ጸሐፍያኑ የተከተሉት የሥነ ጽሑፍ፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንዲሁም የጸሐፍያኑ ተሞክሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት አካል ናቸው አልሁት። የሙስሊሞቹ ተወካይ ዳግም ስለቁርአን ሲያብራራ፣ "ቁርአን የባህል ወይም የሰዎች ልምምድ ተጽእኖ ያለበት መጽሐፍ ሳይሆን፣ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደ ንጹሕ መልእክት ነው" ሲል ተናገረ።

በዚያን ሌሊት የምንነጋገረው፣ "የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ" በሚለው ርእሰ ጕዳይ ላይ ነበር። በርእሰ ጕዳዩም ላይ ለሦስት ሰዓት ያህልም ተወያይተናል። በመጨረሻም እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉን ለቅዱሳን ሰዎች ገልጦአል በሚለው ነጥብ ላይ ተስማማን። ምንም እንኳ በዚህ ነጥብ ዙሪያ መግባባት ላይ ብንደርስም፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የማይስማሙባቸው በርካታ ርእሰ ጕዳዮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ:—

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለው መልእክት ቀጥታ ከሰማይ የወረደ (ታንዚል) ነው።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ በማድረግ ራሱን ገልጦአል።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ፈቃዱን ይፋ አድርጎአል።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የሰብአውያንን ታሪክ ያገናዘቡ ናቸው። ይህም ማለት የሰብአውያን አካሄድ እግዚአብሔርን ግድ የሚለው ጉዳይ ስለሆነ፣ በሰዎች የአካሄድ ዐይነት የእግዚአብሔር ምላሽ ይወሰናል።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የሰብአውያንን ታሪክ ያገናዘቡ አይደሉም። የሰዎችም አካሄድ የእግዚአብሔርን ምላሽ አይወስነውም።
*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መልእክት፣ እግዚአብሔር የሰዎች ልጆችን ታሪክ በመጋራት፣ ሰብአውያንን ለመታደግ የከፈለውን ዋጋና የሄደበትን መንገድ መተረክ ነው።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* የቅዱሳት መጻሕፍት መልእክት ከታሪክ ክሥተት ውጪ ነው። በቁርአን ውስጥ የሚገኙት ታሪካዊ ዘገባዎች ተምሳሌታዊ ንግግሮች ብቻ ናቸው።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ነቢያትም ሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፍያን እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ምን ትርጒም አለው የሚለውን ጒዳይ ማብራራት የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው። ስለዚህ መለኮታዊው መገለጥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተደረገ ማብራሪያም ጭምር ነው። አንዳንድ ጊዜም ጸሐፍያኑ የእግዚአብሔርን ቃል "ሰሙ" ወይም "አዩ" እንዲሁም "የእግዚአብሔር ቃል በአፋቸው ነበር" ተብሎ ተገልጾአል።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፉት ነቢያት በእግዚአብሔር መለኮታዊ መልእክት መገለጥ ሂደት የእግዚአብሔር አፍ ብቻ በመሆን አገልግለዋል።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጆችን ታሪክ ያካተቱ ናቸው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሰጡትን ምላሽ



እንዲሁም ትንቢታዊ መልእክቶችን ይዘዋል። ሰዎች ለእግዚአብሔር ትእዛዝ የነበራቸው ተቃውሞ የታሪኩ ሌላኛው ገጽታ ነው።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መለኮታዊ መልእክቶች ናቸው። የሰዎችን ታሪክ ወይም ሰዎች ለእግዚአብሔር የሰጡትን ምላሽ የሚዘግቡ መጻሕፍት ቅዱሳት መጻሕፍት ሊሆኑ አይችሉም። ለምሳሌ ሱና (የነቢዩ መሐመድ ታሪክ) መለኮታዊ መገለጥ አይደለም።

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጐም ይቻላል።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* ቁርአን ተብሎ የሚጠራው በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈው ቁርአን ብቻ ነው። የቁርአንን መልእክት በተለያዩ ቋንቋዎች ማብራራት ቢቻልም፣ ቁርአን የሚለውን ስያሜ ማግኘት የሚችለው ዐረብኛው ቁርአን ብቻ ነው።
*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የሁለት ወገንን (የእግዚአብሔርንና የሰው ልጆችን) ግንኙነት ማዕከል ያደረጉ መጻሕፍት ናቸው።
*ቁርአናዊው ትምህርት፡—* ቅዱሳት መጻሕፍት የአንድ ወገን ንግግር ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር የሰው ልጆች የሚመሩበትን ምሪት አወረደ፤ የሰው ልጆችም በተሰጠን ምሪት መሠረት እንድንኳዝ ታዘናል።

*ወንጌል፡—* የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታዊ ትምህርት ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ይፋ ማድረግ ነው። እርሱም ሥጋ የሆነ አምላክ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ትርጒም ማወቅ የሚቻለው ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ተያይዞ ሲብራራ ነው።
*እስልምና፡—* ቁርአን ለሰዎች ሁሉ መመሪያ እንዲሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ የመጨረሻው መገለጥ ነው። ቁርአን የቀድሞዎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጠቀልል እንዲሁም የሚያብራራ ነው።

*ወንጌል፡—* የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት እጅግ በጣም አስደናቂ መልእክት ሲሆን፣ አንድ ሰው ይህንን የምሥራች ወንጌል በእምነት ሊቀበል የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ሲረዳው ብቻ ነው።
*እስልምና፡—* የቁርአን መልእክት ቀጥተኛ እንዲሁም ምክንያታዊ ስለሆነ ሰዎች በሚያነቡት ጊዜ ያላንዳች ዕርዳታ ትምህርቱን ሊያስተውሉ ይችላሉ። ሰው ሁሉ ሲወለድ ሙስሊም ሆኖ ስለሚወለድ እንዲሁም የእስልምና

አስተምህሮ ከሰብአዊ ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ስለሆነ ሰዎች የቁርአንን ትምህርት ያላንዳች ጥያቄ ሊቀበሉት ይችላሉ።

*መሲሑ*— ትስብእት (ሥጋ) የሆነ አምላክ እንዲሁም የአምላክ ቃል ነው።
*ቁርአን*— ቁርአን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከሰማይ ወደ ሰው የመጣ የእግዚአብሔር ምሪት ነው።

መለኮታዊ መገለጥን በተመለከተ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ይሁን እንጂ እንስማማበታለን በሚሏቸውም ነጥቦች ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች አሏቸው። ነገር ግን ይህ ልዩነት ከሙስሊሞች ጋር ላለው ግንኙነት እንቅፋት ሊሆን አይገባም። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ያደረገ ምስክርነት ሊለዋወጡ እንዲሁም ውይይት ሊያካሂዱ ይገባል።
መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን በአያሌው የተለየ በመሆኑ ምክንያት በርካታ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ለመወያየት በሚፈልጉበት ጊዜ ከሙስሊሞች አዎንታዊ ምላሽ አያገኙም። ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚለየውም ታሪካዊ ዘገባዎችን በማቅረቡ እንዲሁም በመሲሑ በኢየሱስ ላይ ባሉ ነጥቦች ዙሪያ ነው። እንደ አብርሃም ታሪክ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ብዙ ሙስሊሞችን ግራ የሚያጋቡ ቢሆንም፣ አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በርካታ ሙስሊሞችን የሚመስጥና ልቡናቸውን የሚማርክ ነው።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*
ዘፍጥረት 3፥1-20
*የቁርአን ምንባብ*
ሱራ 20፥9-24

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለሙሴ በሚቃጠለው ቊጥቋጦ ውስጥ መገለጡን የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ በቁርአን ውስጥ ካለው ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ክሥተት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ከሙስሊሞች ጋር ላለን ውይይት እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን (ዘፍጥረት 3፥1-20፤ ሱራ 20፥9-24)?
2. ኢብራሂምን ግራ ሊያጋባው የቻለው የመጽሐፍ ቅዱስ አብዛኛው ክፍል ታሪክ የመሆኑ ጕዳይ ነው። ቁርአን ግን እንደዚህ ዐይነት ታሪኮችን



አልዘገበም። በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ያሉ እነዚህ ልዩነቶች ስለ መለኮታዊ መገለጥና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስላለው ግንኙነት በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን የአመለካከት ልዩነት እንዴት ሊያሳዩ ይችላሉ (ዘፍጥረት 3፥8-10:15፤ ሱራ 2፥38)?
3. ማንኛውም ሙስሊም "አምላኬ" ብሎ ሳይሆን "በእግዚአብሔር ስም" ብሎ ነው የሚጸልየው። ክርስቲያኖች ደግሞ "አምላኬ ሆይ" ወይም "አባታችን ሆይ" ብለው ይጸልያሉ። ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች እንዲህ ብለው የሚጸልዩበትን ምክንያት ይግለጹ (ሱራ 1፥1-7፤ ማቴዎስ 6፥9-13)።
4. "መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል" ለሚለው የሙስሊሞች ተቃውሞ ክርስቲያኖች ምን ዐይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እንዲሁም ምላሻቸውን በምን ዐይነት መልክ ማቅረብ እንዳለባቸው አስተያየቶትን ይስጡ።
5. ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ይናገራል (ሱራ 3፥3፤ ሱራ 5፥47-49)። እነዚህ ቁርአናዊ ምንባባት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እምነትን አስመልክቶ ለሚያካሂዱት የጋራ ውይይት ምን ዐይነት ዕገዛ ሊኖራቸው ይችላል?

ምዕራፍ ሰባት

# መገለጥ

## ታንዚል—ተሰግዎ

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖር አንድ ክርስቲያን፣ "በእኔ አገር የሚኖሩ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ጥሩ ግንኙነት አላቸው:: በንግግራችን መኻል የሃይማኖት ጉዳይ ከተነሣ ግን ውይይቱን አቋርጠን እንለያያለን" ሲል ነግሮኛል:: ይህ ለምን ሊሆን ቻለ? አንደኛው ሌላኛውን ማዳመጥ አስቸጋሪ ለምን ሆነበት? እኛ እምነታችንን ለሌሎች ለመናገር ምን አስፈራን? ሙስሊሞች አለን ብለው የሚናገሩት እውነት ክርስቲያኖችን ስለሚረብሽ ነውን? ወይስ የክርስትና እምነት ሙስሊሞችን ስለሚረብሻቸው ነው?

አንድ ሙስሊም ፕሮፌሰር በሙስሊሙ ኡማና በክርስቲያኖች መካከል እውነትን አስመልክቶ ያሉትን የተለያዩ መረዳቶች በሚከተለው መንገድ ገልጾአል:: ፕሮፌሰሩ በመጀመሪያ እጁን ጨብጦ ቁርአንን በእጁ ላይ አኖረው:: ይህንን ድርጊት ሲያብራራ "የተጨበጠው እጄ መሐመድን ያመለክታል:: ለሙስሊሞች ቁርአን ከመሐመድ በላይ ነው:: ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደ መልእክት ስለሆነ፣ ከማንኛውም ታሪክና ከየትኛውም ነቢይ በላይ ነው:: ሁሉም እውነት በቁርአን ውስጥ ተብራርቶአል" አለ::

በመቀጠልም የተጨበጠ እጁን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ በማሳረፍ፣ "የተጨበጠ እጄ የሚያመለክተው መሲሑ ኢየሱስን ነው አለ:: ለክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ የሚያመለክተው ወደ ክርስቶስ ነው:: እርሱ እውነትና የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው:: እንዲሁም እርሱ ለሰዎች የተገለጠ እውነትና ሥጋ ለብሶ የተገለጠ አምላክ ነው:: እውነት ሁሉ ፍጻሜ የሚያገኘው በመሲሑ ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ ስለ እርሱ ይመሰክራል" አለ::

በአንድ መስጊድ ውስጥ በነበረን የምሽት ውይይት ላይ እንዲህ ስል ተናገርሁ "ውይይታችን ያተኰረው የእውነት መሠረቱ ምንድን ነው" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ነው:: ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስ በአካል የተገለጠ እውነት ነው ብለን እናምናለን:: ሙስሊሞች ደግሞ በዚሁ ምሽት፣ ቁርአን የሰው ልጆች እውነቶችን ሁሉ እንዲመዝኑበት ከሰማይ የወረደ መልእክት ነው ብለዋል:: ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተገናኘን ቁጥር ሁሉ እነዚህ ጥያቄዎች ዘወትር

ከእኛ ጋር ናቸው:: ስለሕይወትና ስለእግዚአብሔር ያለን ምልከታ የሚወሰነው ቀጥሎ ባሉት ሁለት ጥያቄዎች በምንሰጠው ምላሽ ነው:— መሲሑ ማን ነው? ቁርአን ምንድን ነው?

## መገለጥ እንደ ታንዚል

ሙስሊሞች፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመጨረሻ ጊዜ የወረደ መለኮታዊ መልእክት ነው የሚል እምነት አላቸው:: ታንዚል የሚለውም የዐረብኛ ቃል "ከሰማይ የወረደ" የሚል ትርጉም አለው:: በሰው ልጆች ታሪክ ሁሉ እግዚአብሔር ለሰብአውያን የሚሆነውን መልእክቱን ይፋ ያደረገው በነቢያት በኩል ቃሉን በመላክ ነው:: እንደ ቀድሞዎቹ መገለጦች ሁሉ ቁርአንም ከእርሱ በፊት የነበሩትን መገለጦች ለማብራራት እንዲሁም ለመጨረሻ ጊዜ ከሰማይ የወረደ (ታንዚል) መልእክት ነው:: ይህ ሙስሊሞች ሁሉ የሚቀበሉት መሠረታዊ አስተምህሮ ነው::

ይህ አስተምህሮ ከሚከተለው የሙስሊሞች ትምህርት ጋር የሚዛመድ ነው:: ሙስሊሞች በሰማያዊ ስፍራ በወርቃማ ጽሑፍ የተጻፈ ሰሌዳና የመጻሕፍት እናት ተብሎ የሚጠራ መዝገብ እንዳለ ያምናሉ:: ይህም መጽሐፍ የእግዚአብሔር ዘላለማዊና የማይለወጥ ፈቃድ የተጻፈበት መጽሐፍ ነው:: አዳም የእግዚአብሔር ምሪት ከመጣላቸው ነቢያት መካከል የመጀመሪያው ሰው ነው:: ይህም ምሪት አዳም በምድር ላይ በትክክል የአላህ ወኪል ሆኖ እንዲኖር ረድቶታል:: ኋላም ይህ የመጻሕፍት ሁሉ እናት የሆነው መጽሐፍ ቀሪ ክፍል በአራቱ መጻሕፍት ማለትም በተውራት፣ በዘቡር፣ በኢንጂልና በቁርአን ውስጥ ተገልጦአል::

ሙስሊሞች ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መገለጥ የመሆኑ ጉዳይ ማረጋገጫ አለው የሚል አቋም ስላላቸው ትልቅ ደስታ ይሰማቸዋል:: ማረጋገጫውም ቁርአንን የመሰለ መጽሐፍ ሌላ ሰው ማዘጋጀት አለመቻሉ (ኢጃዝ) ነው[1]:: ይህም ማለት የቁርአንን ተአምራዊነት አመሳስሎ መድገም ማንም ያለመቻሉ ነው:: ቁርአንና ሙስሊሞች ይህንን ሐሳብ ደጋግመው ያውጃሉ (ሱራ 2÷23):: የመሐመድ ተቃዋሚዎች መሐመድ የቁርአንን መልእክት ያገኘው ከጥንት አፈ ታሪክ ነው ብለው በሚቃወሙት ጊዜ፣ የመሐመድ መልስ ቁርአንን የመሰለ ትንሽ መጽሐፍ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ የሚል እንደ ነበረና ተቃዋሚዎቹም ይህን ማድረግ እንዳልቻሉ ይታመናል:: በዘመናችንም ሙስሊሞች፣ የዐረብኛው ቁርአን የቋንቋና የግጥም ሁኔታ በጣም

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 33-34.



አስገራሚ እንዲሁም ማንም ተመሳሳዩን ሊያዘጋጅ አይችልም ብለው ይናገራሉ::

ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ ቁርአን ስለሳይንስ ያለውን አመለካከት ይናገራሉ:: ቁርአን በዘመናችን በሳይንስ ስለተገኙት ግኝቶች ቅድመ ትንበያ ይሰጣል ይላሉ:: ሙስሊሞች እነዚህን ሁሉ መረጃዎች ለማቅረብ የሚሞክሩት፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መለኮታዊ መገለጥ፣ እጅግ ተአምራዊ የሆነ እንዲሁም ስለ ዘመናዊው ሳይንስ አስቀድሞ ትንቢት የተናገረና ከሳይንስም ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ መጽሐፍ መሆኑን ለማሳየት ነው::

የታንዚል (የቁርአን መገለጥ) አስተምህሮ ሙስሊሞች ቁርአንን ከብልሽት ጠብቀው እንዳቆዩ ያስተምራል:: የቁርአን ብልሽት ማለት ምን ማለት ነው? ቁርአን ተበላሽቶአል ስንል ውጫዊ ሰብአዊ ተጽእኖ አለበት ማለታችን ነውን? ምንም እንኳ መሐመድ የሌሎችን ሰዎች ምክር ይጠይቅ የነበረ ቢሆንም፣ ቁርአንን የመሰለ መጽሐፍ ማዘጋጀት አይቻልም የሚለው አስተምህሮ ቁርአን ከሰብአዊ ተጽእኖ ነጻ እንደ ሆነ ይገልጻል:: ቁርአን በምንም መልኩ አልተበላሸም፤ ከማንኛውም የሰዎች ተጽእኖ ነጻ ነው (ሱራ 10÷37-38):: ቁርአን ለሰው ልጆች ተገለጠ እንጂ በሰው ልጆች ተጽእኖ ውስጥ የወደቀ መጽሐፍ አይደለም::

በድሩ ዲ. ቀትራጋ የተባለው በናይሮቢ የእስልምና ፕሮፌሰር እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> በመለኮታዊ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት መገለጦች ከእግዚአብሔር ዘንድ በቀጥታ የወረዱ (ታንዚል) እውነተኛ ምሪቶች ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል የተገለጠው ለተመረጡ ነቢያት ነው:: የነቢያቱ ማንነት፣ ወይም ሕይወታቸው ወይም ደግሞ ታሪካቸው ለመለኮታዊ መልእክቱ መሠረት አልሆነም[2]::

## መገለጥ እንደ ተሰግዎ

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ተሰግዎ መገለጥ ነው:: ይህም ታንዚል ከሚለው የእስልምና አስተምህሮ ጋር ልዩነት አለው:: ተሰግዎ ማለት "በሥጋ መገለጥ" ማለት ነው:: ይህም የሚያመለክተው መለኮታዊው ቃል ሥጋ መሆኑን ነው::

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 150.

በምዕራፍ ስድስት ላይ እንደ ተመለከትነው፣ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የሠራውን ሥራና የሰብአውያንን ምላሽ የያዘ መጽሐፍ የመሆኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል እንዲሉ አድርጓቸዋል:: ከሰው ልጆች ሕይወት ጋር ተያያዥ የመሆኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ ከሆነ በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ማለት ይቻል ይሆናል:: ሁሉም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሰው ልጆች የታሪክ ሂደት ውስጥ የተገለጡ ናቸው:: ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት የሰዎችን ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ የሰዎችን ማንነት፣ ባህል እንዲሁም የአስተሳሰብ ዘይቤዎችን በግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መጽሐፍ ነው:: በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ በታሪክ ውስጥ የተገለጠ መለኮታዊ መልእክት ነው::

በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ መሠረት፣ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪ ውስጥ ራሱን በሙላት የገለጠው መሲሑ ክርስቶስ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚ ምድር በመጣ ጊዜ ነው:: እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮአ (ዮሐንስ 3+16):: ይህም ብቸኛው የእግዚአብሔር ልጅ አናጢ የነበረው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ሰው ሆነ::

በዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር ቃል፣ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር እውነት ተብሎ ተጠርቶአል:: እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረበት በቃሉ በኩል ራሱን ገለጠ:: የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መሲሑ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥጋ ሆኖ/ለብ እንደ ተገለጠ የዮሐንስ ወንጌል እንዲህ ሲል ይገልጻል:—

> በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ::. . . ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፤ አንድ ልጅ ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐንስ 1+1-2:14)::

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠሩ ያስተምራል:: ከሰዎች ኀጢአትና ዐመፅ የተነሣም በሰዎች ላይ ያለው የእግዚአብሔ መልክ/አምሳል ተበላሽቶአል:: አዳምና ሔዋን ኀጢአት በሠሩ ጊዜ የተበላሸው በሰዎች ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ምስል፣ እግዚአብሔር በመሲሑ በኩ አድሶታል:: ወላጆቻችን የሆኑት አዳምና ሔዋን በሠሩት ኀጢአት ምክንያት በሁላችን ላይ ሞት ተፈረደብን:: ይሁንና ሥጋ ለብሶ የተገለጠው እግዚአብሔ (መሲሑ) ተበላሽቶ የነበረውን በሰው ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ምስል ሙ በሙሉ አድሶታል::



እኛ ሁላችን ከኀጢአታችን የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ኅብረት ተበላሽቶአል:: ነገር ግን እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ወደ እኛ በመምጣት ከወደቀው ማንነታችን አነሣን:: በአዳም ምክንያት ኀጢአትና ሞት ወደ ሰው ልጆች ሁሉ ደረሰ:: ነገር ግን በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች መጣ:: ለእግዚአብሔር ጥሪ በእምነት አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጡ ማለትም ንስሐ ለሚገቡና ራሳቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው የሚሰጡ ሁሉ፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ ጽድቅንና አዲስ ሕይወትን ያገኛሉ:: ይህን እውነት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:—

> በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ (ሮሜ 5+19)::

እንዲሁም:—

> ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና:: ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ (1ቆሮ 15+21-22)::

## የውይይቱ አስቸጋሪነት

በእስልምና እምነት እግዚአብሔር ፈቃዱን በነቢያት በኩል አስታወቀን የሚል እምነት ሲኖር፣ በወንጌል ውስጥ ግን እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ራሱን መሥዋዕት በማድረግ ፍቅሩን እንደ ገለጠልን ተጽፎአል:: እነዚህ ሁለቱ አመለካከቶች በታንዚልና በተሰግዎ በተገለጠ መልእክት መካከል ላለው ልዩነት መሠረቶች ናቸው::

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ለውይይት በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ ልዩነቶቹ መንፀባረቃቸው የግድ ነው:: በክርስቲያኖች አመለካከት የእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ የተፈጸመው በሰዎች ታሪክ ውስጥ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ታሪካዊ ክሥተቶችንና ባህላዊ ዐውዶች ማወቅ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በትክክል ለመረዳት ታላቅ ዕገዛ አለው:: በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱሱ መገለጥ በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረገው ዐይነት መስተጋብር/ውይይት ነው:: እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ ውስጥ ሲገለጥ፣ ክፉ ሥራችንን ሲቃወም እንዲሁም የእኛን ጥያቄ ሲመልስና በቀናው ጎዳና ሲመራን እንመለከታለን::

በኢሳይያስ 1+18 ላይ "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር":: ስለዚህ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያስታውቅ ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ጋር የሚዋቀስ አምላክ ነው:: ብዙ ሙስሊሞች ይህንን አባባል ለቁርአን አይሠራም ይላሉ፤ ምክንያቱም የቁርአን መልእክት ከሰብአውያን ጋር አንዳች ትስስር የሌለው የአምላክ መልእክት ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ሰዎችን ለውይይት አይጠራም፤

ይልቁንም ከምሕረቱና ከርኅራኄው የተነሣ ፍጹም የሆነውን ፈቃዱን ለእኛ ገልጦልናል፡፡ ስለዚህ ሙስሊሞች ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መወያየት አንችልም ይላሉ፡፡

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ተገናኝተው በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ያላቸውን አመለካከት በሚወያዩበት ወቅት፣ የማያግባቧቸው ርእሰ ጉዳዮች ያጋጥሟቸዋል፡፡ ከእነዚህም ርእሰ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:—

## የክርስቶስ ሞት

በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ባለው ልዩነት ዋንኛው ርእሰ ጉዳይ ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደ ሞተ ሲያስተምር ቁርአን በተቃራኒው "አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም" (ሱራ 4+157) ይላል፡፡

እኔ በርካታ ጊዜ ከሙስሊሞች ጋር ስለክርቶስ ሞትና ትንሣኤ ተወያይቼአለሁ፡፡ ከእኔ ጋር የተወያዩት ሙስሊሞች፣ ከተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል የመጡና የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ማናቸውም ቢሆኑ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶአል የሚለውን ነጥብ ለማስተናገድ ፈቃደኞች አይደሉም፡፡

ብዙ መቶ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተገኙበት ከሙስሊም ምሁራን ጋር ባደረግኋቸው ውይይቶች በተደጋጋሚ፣ "ከእያንዳንዱ ወንጌል ውስጥ አንድ ሦስተኛው እጅ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር የተያያዘ ነው" እንዲሁም ክርስቶስ ኢየሱስ ለመሞቱና ከሙታንም ለመነሣቱ "እጅግ በርካታ እንዲሁም ተአማኒ የሆኑ የዐይን ምስክሮች የዘገቧቸው ዘገባዎች ዛሬም ድረስ አሉ" እላለሁ፡፡ ከእነዚህ ዘገባዎች መካከል አንዳንዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ደግሞ ይህን እውነት የሚያስረግጡ በርካታ የታሪክ ድርሳናት አሉ፡፡ የወንጌል ዐቢይ ትምህርትም የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ድርጊት ከተፈጸመ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ አንድ ሰው በጻፍዋት አንዲት ዐረፍተ ነገር ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስንና ተአማኒ የሆኑ የታሪክ ድርሳናትን ምስክርነት ዋጋ ማሳጣት ተገቢ ነውን?

ለዚህ ጥያቄ ከሙስሊሞች በኩል የሚሰጠኝ መልስ:— "ቁርአን ብሎአል፡፡ አል-መሲሕ ኢሳ አልተሰቀለም፤ አልሞተምም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባዎች የተበላሹ ናቸው" የሚል ነው፡፡



## ሰብአዊ ተጽእኖ

በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት ከሚፈጥሩ ነጥቦች መካል ሌላኛው፣ የሰዎች ማንነትና የሕይወት ዘይቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሱ የሆነ ቦታ ይዞ የመገኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ ከሙስሊም ባልንጀራዬ ጋር ስንወያይ እንዲህ አልሁት:— "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጸሓፊው ማንነትና ባህል ተካቶአል፡፡ ጳውሎስ ሲጽፍ ማንነቱን ሳይለቅ እንደ ጳውሎስ ሆኖ ጻፈ፤ ጴጥሮስም እንደ ጴጥሮስ ሆኖ ጻፈ"፡፡ ለዚህ ንግግሬ ይህ ጓደኛዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ:— "አንተ በግልጽነት እንደ ተናገርኸው የእግዚአብሔር ቃል ከሰዎች ባህልና የኑሮ ዘይቤ ጋር ስለተደባለቀ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል፡፡ ቁርአን ግን ከእንደዚህ ዐይነቱ ብልሽት የጸዳ ነው፡፡ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን"

## የእግዚአብሔር ምጡቅነትና ኀይል

ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰዎች ባህል፣ የኑሮ ዘይቤና ታሪክ ውስጥ ተገልጠዋል ብሎ መቀበል የእግዚአብሔርን ልዕልና፣ ልዕቀትና ኀይል እንዲሁም የቃሉን ክብር ያጉድፋል ይላሉ፡፡ የእስልምና ነገረ መለኮት የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ መውረዱ (ታንዚል) ከእግዚአብሔር ልዕልና፣ ልዕቀትና ኀይል ጋር በእጅጉ እንደሚስማማ ያስተምራል፡፡

ዳሩ ግን ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን "የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ መውረዱ የእግዚአብሔርን ኀይልና ክብር ለመጠበቅ ፍጹም ተመራጭ መንገድ ነውን?" ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ ሙስሊሞችም "አዎን" ሲሉ ይመልሳሉ፡፡

ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክ ውስጥ መገለጡ እንዲሁም ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ ደካማነት ነውን? የቤተ ክርስቲያንም ምስክርነት የሚያተኩረው እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ በመገለጥ መከራ መቀበሉ የእግዚአብሔርን ኀይልና ሰዎችን ሁሉ የሚለውጥ፣ የሚያድስና የሚያሳድግ የተትረፈረፈ አዲስ ሕይወት የሚሰጥ ነው በሚለው ርእስ ላይ ነው፡፡

ኬኔት ክራግ የተባሉ ጳጳስ ብዙውን የሕይወት ዘመናቸውን በአብዛኛው ያሳለፉት ከሙስሊሞች ጋር ከላይ በተመለከትናቸው ጥያቄዎች ዙሪያ በመወያየት ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክና ባህል የመገለጡን እውነት ሙስሊሞች እንዲያስተናግዱት ተማጽነዋል፡፡ ከሙስሊሞች ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ሁሉ ቁርአንና የመሐመድ ትንቢቶች የሰውን የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የሰብአውያንን ታሪኮች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው በማለት ይሞግቱ

ነበር። እንዲህ ሲሉም ይግጸናሉ፣ "እባካችሁ አስተውሉ ቁርአን የሰዎችን ማንነትና ታሪክ በውስጡ የያዘ መጽሐፍ እኮ ነው"[3]።

የክራግ ምኞት ይህንን እውነት በማሳየት ብዙ ሙስሊሞች የሰዎችን ባህልና ታሪክ የያዘውን መጽሐፍ ቅዱስን ይሰሙ ዘንድ ነው። ክራግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በራሳችን ዐውድ በተለይም በክርስቶስ በኩል ተገለጠልን የሚለውን እውነት ለሙስሊሞች ለመግለጥ ትልቅ ፍላጐት የነበራቸው ሲሆን፣ ይህን ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ብዙ ጥናቶችን አካሂደዋል። ይሁን እንጂ ከጽሑፎቻቸው የምንግረው ነገር ከሙስሊሞች ጋር በነበራቸው ውይይት ተስፋ መቍረጣቸውን ነው። ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የሰው ልጆችን ታሪክ፣ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የባህል አሻራ መቀበል በጣም ይከብዳቸዋል[4]።

## ታሪክና ታንዚል

ራሳቸው ሙስሊሞች ቁርአንን በሚያጠኑበት ጊዜ፣ የቁርአንን ታሪካዊና ባህላዊ ዐውድ በተከተለ መልኩ ስለሚያጠኑ ቁርአን ከታሪክ ውጪ ነው ማለት አይቻልም የሚለውን አቋም በመያዝ የሙስሊሞችን አቋም የሚተቹ ክርስቲያኖች አሉ። የተከበሩት የስዊዝ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁር የሆኑት ሐንስ ኩንግ ባካሄዱት ጥናት፣ ሙስሊሞች በቁርአን ውስጥ ያሉትን ታሪኮች እንደ ታሪክ በጥልቀት ለማየት ፈቃደኞች ካልሆኑ፣ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ውይይት ማድረግ አይችሉም በማለት ተናግረዋል። ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ቃል ለመነጋገር ብቸኛው መንገድ ሙስሊሞች ታሪክን ለማጥናት ፈቃደኛ መሆናቸው ዐቢይ ጉዳይ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል[5]።

ይሁንና የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ መገለጥ ነው የሚለውን አስተምህሮ፣ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ባህልና ታሪክ ውስጥ ተገልጦአል ከሚለው እምነት ጋር ማስማማት ይቻላልን? ሐንስ ኩንግ

[3] Kenneth Cragg, *The Event of the Qur'an: Islam in Its Scriptures* (Oxford: Oneworld Publications, 1994).

[4] ዝኒ ከማሁ፤ እንዲሁም Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Oxford: Oneworld Publications, 1999).

[5] Hans Kung, et al., *Christianity and World Religions: Paths to Dialogue with Islam, Hinduism, and Buddhism,* translated by Peter Heinegg (New York: Doubleday, 1986), 28-36.



ከሙስሊሞች ጋር ለመወያየት በቅድመ ሁኔታነት ያስቀመጡት መስፈርት የራሳቸውን አመለካከት በሙስሊሞች ላይ እየጫኑ ነው ወደሚለው ድምዳሜ አይወስድምን? ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያላቸው ይህ ዐይነቱ አተያይ እስካልተቀየረ ድረስ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር መወያየት አይችሉም የምንል ከሆነ ከሙስሊሞች ጋር መወያየት የምንችለው እንዴት ነው?

የእስልምና ምሁር የሆኑት አንድሪው ሪፒን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:— "ታሪክ የእውነት መለኪያ እንዲሁም ከቁርአን የሚበልጥ ነው የሚለው አስተሳሰብ ሙስሊሞች በፍጹም ሊቀበሉት የማይችሉት ጉዳይ ነው። በሰዎች ታሪክ ላይ ተመሥርቶ ያልተጻፈውን የቁርአን አስተምህሮ ወደ ሰዎች ታሪክ ዝቅ አድርጐ መቀበል ስለማይቻል እስልምና ትክክል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ይወስዳል የሚለው ጉዳይ ብዙ ሙስሊሞችን ያሳስባቸዋል"[6]።

ታንዚልና መጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ስለ እውነትና ስለ መገለጥ ያሉ ሁለት የተለያዩ መረዳቶች እንደ ሆኑ መቀበል የተሻለ ውጤት ያስገኛል። ቁርአን ስለ እግዚአብሔር ቃል መገለጥ ለሙስሊሙ ኡማ የሚያስተምረው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ከሚያስተምረው በጣም የተለየ ነው። ስለታንዚል ያለውን አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲቀበል ማስገደድ በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክ ውስጥ ተገልጦአል የሚለውን ትምህርት ቁርአን እንዲቀበለው ማስገደድ ውይይታችን ስኬታማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ፣ እስልምናና ወንጌል የሚያስተምሩትን ትምህርት ማበላሸት ነው። ሁለቱም የእምነት ቡድኖች ከራሳቸው እምነት አቋም በመነሣት የየራሳቸውን ምስክርነት ይሰጣሉ።

ሁለቱ የእምነት ክፍሎች ስለእግዚአብሔር ቃል ግልጠት የሚያስተምሩት ትምህርት፣ እምነቶቹን በማስፋፋት ረገድ ባላቸው ተልእኮ ላይ በሚገባ ተንጸባርቀዋል። ሁለቱም የእምነት ክፍሎች እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ቃል ለዓለም ሁሉ እንዲመሰክሩ ተልእኮ እንደ ሰጣቸው ያምናሉ። ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውም እስልምናን ወይም የምሥራቹን ወንጌል ይሰብካሉ። ቀጥለን እስልምናና ክርስትና ለዓለም ህዝብ ያላቸውን ተልእኮ እንመለከታለን።

## ታንዚል እና እስላማዊ ተልእኮ

ሙስሊሞች ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደው መልእክት የዐረብኛው ቁርአን እንደሆነ ያምናሉ። ስለዚህም ቁርአንን በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም

[6] Rippin, *Muslims,* 240-41.

አይቻልም። ወደ ሌላ ቋንቋ ከተተረጐመ ደግሞ ቁርአን መሆኑ ይቀራል። የቁርአንን ማብራሪያዎች በሌሎች ቋንቋዎች መጻፍ ይቻላል፤ ነገር ግን ማብራሪያዎቹ ቁርአን አይደሉም። የዐረብኛው ቁርአን ሙስሊሞች እምነታቸውን ለማስፋፋት ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ይጐዳዋል? ይህ ጉዳይ ለእምነቱ መስፋፋት ዐቢይ እንድምታ አለው።

በጣም ግልጽ ከሆኑት እንድምታዎች ውስጥ አንዱ የዐረብኛ ቋንቋ በሙስሊሞች ጸሎት (ሰላት) ውስጥ ያለው ሚና ነው። ለምሳሌ በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ በተለያየ ሁኔታ በርካታ ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት ይቀበላሉ። ባልቲሞር በተሰኘው ከተማ ባለ መስጊድ ውስጥ በአንድ ምሽት ብዙ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና ሃይማኖት ተቀብለዋል። የምሽት ጸሎቱ ሲጠናቀቅ አንድ ሽማግሌ ወደ ሙስሊሞቹ መሪ በመቅረብ "ሙስሊም መሆን እፈልጋለሁ" አለው። በመስጊዱ ውስጥ የተሰበሰቡ ሙስሊሞች "አልሐምዱሊላህ" (ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን) በማለት አስተጋቡ።

የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) አዲሱን አማኒ የእስልምና የእምነት አንቀጽ በዐረብኛ "ላ ኢላህ ኢለላህ ሙሐመዱን ረሱል አላህ" (ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው) እንዲያውጅ አደረገው። ከዚያም የሙስሊሞቹ መሪ፣ "ይህ ሰው ከዚህ በኋላ ሙስሊም ነው" በማለት ካስታወቀ በኋላ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ እንዲቀበለውም ጥሪ አቀረበ። ኢማሙ ለአዲሱ አማኝ በየምሽቱ በመስጊዱ ውስጥ የዐረብኛ ትምህርት እንደሚሰጥ ነገረው። የእስልምና መጽሐፍ የተጻፈው በዐረብኛ ቋንቋ ስለሆነ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ጸሎት ማድረስ የሚቻለውም በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ መሆኑን ከገለጠለት በኋላ፣ ዐረብኛ ቋንቋ መማሩ መሠረታዊ ጉዳይ እንደ ሆነ ለአዲሱ አማኒ ገለጠለት።

## የዐረብኛው ቁርአን

ላሚን ሳኔህ የተባሉት የነገረ መለኮት ምሁር፣ በዐረብኛ ቋንቋና በእስላማዊ ተልእኮ መካከል ስላለው ዝምድና በስፋት ጽፈዋል። የሳኔህ ዕድገት በምዕራብ አፍሪካ በሙስሊም ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን የክርስትናን እምነት የተቀበሉት ገና ወጣት ሳሉ ነበር። ኋላም ዬል በሚባለው ስመ ጥር የአሜሪካን ዩኒቨርስቲ ውስጥ "ሚስዮሎጂ" በሚባለው የጥናት ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት አስተምረዋል። የዶክትሬት ዲግሪ ጥናታቸው እስልምና በምዕራብ አፍሪካ በሚል ርእስ ላይ የሚያጠነጥን ነበር።



ሳኔህ በጥናታቸው ቁርአን ከሰማይ የወረደ መገለጥ (ታንዚል) ነው የሚለው አመለካከት በእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ውስጥ ያለውን ድርሻ በስፋት መርምረዋል። ይህም የሙስሊሞች አመለካከት ቁርአን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች እንዳይተረጐም ምክንያት ሆኖአል። እንደ እስልምና ትምህርት፣ ቁርአን በመባል የሚጠራው በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ብቻ ነው። በተለያዩ ቋንቋዎች የሚተረጐሙት መጻሕፍት ማብራሪያዎች እንጂ እውነተኛ ቁርአን ሊሆኑ አይችሉም። በዚህ ዐቢይ ምክንያት እስልምና በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ሁሉ ዐረባዊነት ከእምነቱ ጋር እየተስፋፋ ሄደ። የዐረብኛ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች ከእስላማዊ ሚስዮናዊ ተልእኮ ጋር የተቈራኘ ነው።

የሳኔህ ሐሳብ ቀጥተኛ የሆነ ሂስ ነው። ሳኔህ የዐረብኛው ቁርአን እስልምናን የሚቀበሉ ሰዎችን ባህል ክፉኛ እንደሚያዳክም ይገልጻሉ[7]። በትውልዳቸው ዐረብ የሆኑ ሚስዮናውያን የዐረብኛውን ቋንቋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ የእስልምናን ሃይማኖት ተቀብሎ የዐረብኛን ቋንቋ የተማረ ግለሰብ ቁርአንን በደንብ የተማረውንና ቋንቋውን ጠንቅቆ የሚያውቀውን ዐረባዊ ሙስሊም ቁርአናዊ አስተምህሮን በተመለከተ ሂስ እንዴት ማቅረብ ይችላል? በአንጻሩም የዐረብ ሙስሊም ሚስዮናውያን የሚያሳድሩት የባህል ተጽእኖም በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

በአንጻሩ ደግሞ እስልምና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ ነው። ዐረብኛው ቋንቋ አዲሱ አማኝ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሙስሊሞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው ያደርጋል። አዲስ የሆነ ማንኛውም ሙስሊም ሰላት ሲሰግድ በመቶ ሚሊዮኖች ከሚቈጠሩ ከዓለም ሙስሊሞች ጋር በመሆን አላህ ለገለጠው ፈቃድ እየተገዛ እንደ ሆነ ያምናል። በዐረብኛ ቋንቋ የሚፈጸመውን ጸሎት (ሰላት) ማወቅ፣ ዓለም ዐቀፋዊ ለሆነው ለአላህ ፈቃድ የመገዛት ምልክት እንደ ሆነ ይታመናል።

## የፖለቲካ ሥርዐት

የዐረብኛውን ቁርአን ማክበር በፖለቲካ ሥርዐት ውስጥ የራሱ የሆነ ተጽእኖ አለው። የሕንድ ሙስሊም ምሁር የሆነው ራፊቅ ዘካሪያ፣ በእስልምና ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ገጽታ በሦስት ዋና ዋና ርእሶች በመክፈል ጽፎአል። ይኸውም:—

---

[7] Lamin Sanneh, *Translating the Message: The Missionary Impact on Culture* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1989), 211-14.

1. በፖለቲካው ሥርዐት ያለው ሚና:— "በእስልምና እምነት ገዢው፣ መንግሥት ወይም አስተዳደር የእስልምናውን ርዕዮተ ዓለም በጥንቃቄ መከተል አለበት:: ነቢዩ መሐመድ የፖለቲካውን ሥርዐት በመጠቀም የእስልምናን እምነት ለማሳደግና ለማስፋፋት ተጠቅመውበታል"[8]::
2. ከፖለቲካ ሥርዐት በላይ የሆነው ሥልጣን:— እንደ ሙስሊሞች ትውፊት፣ በአንድ ወቅት ነቢዩ መሐመድ ሲናገሩ፣ "ዐረቦች በሌሎች ሕዝቦች ላይ አንዳችም የበላይነት እንደ ሌላቸው ሁሉ ሌሎች ሕዝቦችም በዐረቦች ላይ የበላይ አይደሉም"[9] ብለዋል:: የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፓኪስታን የተሐድሶ መሪ ማሁዱዲ ይህንን የነቢዩን መሐመድ ንግግር አዘውትሮ በመጥቀስ፣ ዐረብ ያልሆነውን የሙስሊም ማኅበረሰብ ከዐረብ ተጽእኖ ለማላቀቅ ከፍተኛ ትግል አድርጎአል:: ይሁን እንጂ ራፊቅ ዘካሪያ ደግሞ፣ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ የዐረብኛ ቋንቋ ለሚያውቁ እንዲሁም ለዐረቦች ከፍተኛ አክብሮት እንዳለው ገልጾአል[10]::
   በቀደምትነት እስልምናን የተቀበለው የዐረቡ ማኅበረሰብ በዙሪያው ከሚገኙት ማኅበረሰቦች በሥልጣኔ ወደ ኋላ የቀረ ነበር:: የዐረብኛው ቁርአን በሥልጣኔ ወደ ኋላ ለቀረው ለዐረብ ሕዝብ ትልቅ ኀይል ሰጥቶአል:: ነገር ግን እየቆየ ሲሄድ በዐረብኛ ቋንቋ የተገለጠው መልእክት ዐረብ ያልሆነውን የሙስሊም ማኅበረሰብ ማግለያ መሣሪያ መሆን ጀመረ:: እስልምና ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እየተስፋፋ ሲመጣ፣ የዐረብኛ ተናጋሪ ከሆኑት በተጨማሪ የነቢዩ መሐመድ ዘመዶች (ቁሬይሾች) የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የበላይ ሆኑ፤ የዐረብ ዝርያ የሌለው ሙስሊም በእነርሱ ቍጥጥር ሥር ወደቀ[11]:: ለብዙ ዓመታት መሐመድ የዐረቦችን የበላይነት ለማስቀረት የተናገሩት ንግግር በፍጹም በተግባር ሊተረጐም አልቻለም[12]::
3. የፖለቲካ ሥርዐት መቀየር:— የፖለቲካ ሥርዐትን ስለመቀየር ራፊቅ ዘካሪያ እንዲህ ይላል:— "የሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሪ መቼና እንዴት ይቀየር? የሚለው ጥያቄ በመጀመሪያዎቹ የእስልምና ዘመናት ላይ የነበሩትን የሸሪአ ሕግ ምሁራንን ግራ አጋብቶ ነበረ:: መሪዎች ሰነፍ ሲሆኑ፣ ዓለማዊነት ሲያጠቃቸው፣ ታማኝነት ሲጐድላቸው፣ አምባገነን

[8] Rafiq Zakaria, *The Struggle within Islam: The Conflict Between Religion and Politics* (New York: Penguin, 1989), 284.

[9] ዝኒ ከማሁ፤ 285::

[10] ዝኒ ከማሁ::

[11] ዝኒ ከማሁ::

[12] ዝኒ ከማሁ::



ሲሆኑ ወይም ደግሞ ዐላማቸውን ሲስቱ ሙስሊም የነገረ መለኮትና የሕግ ምሁራን መሪዎች ከሥልጣናቸው እንዲነሡ የሚጠይቅ አንዳችም አስተያየት አልሰጡም:: እነዚህ ምሁራን በተቃራኒው ነቢዩ መሐመድ "ለባለሥልጣናት ተገዙ" ያሉትን ንግግር በመጥቀስ ሕዝቡ ለእነዚህ መሪዎች እንዲታዘዝ አስተምረዋል"[13]::

እነዚህ ሦስት ነጥቦች ዲሞክራሲያዊ ሥርዐት የተመሠረተባቸውን መሠረታዊ ፋይዳዎች የሚያንፀባርቁ አይደሉም:: ነገር ግን በዚህ ርእስ ጕዳይ ዙሪያ፣ በኡላማዎች (በእስልምና ሕገ ምሁራን) መካከል ምክክሮች (ሹራ) ይካሄዳሉ:: ሹራ በኡላማዎች መካከል የሚካሄደውን ዲሞክራሲያዊ ውይይት አመልካች ቢሆንም፣ ኡላማዎች የሚያስተላልፉት ውሳኔ የእስልምናን ሕግ (የሸሪአን ሕግ) መሠረት ባደረገ መልኩ ብቻ ነው:: ይህ አሠራር ሌሎች ማኅበረሰቦች ከሚከተሉት አስተዳደር ፍጹም የተለየ ነው:: በእስልምና ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ የዲሞክራሲያዊ ሥርዐት አራማጆች፣ የዲሞክራሲን መሠረታዊ ፋይዳዎች በትክክል ለመረዳት ከእስልምና ውጪ መመልከት የግድ ይሆንባቸዋል[14]::

በቴምፕል ዩኒቨርስቲ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ያበረታታል ብዬ ስናገር በዚሁ ዩኒቨርስቲ የሚማር ሙስሊም ተማሪ "እስልምና ዲሞክራሲ አይደለም" ሲል ተናገረ::
ከሰማይ የወረደው መልእክት (ቁርአን) የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በሌሎች "ሰዎች ላይ መስካሪዎች" እንዲሆን ነው (ሱራ 2+143) የሚለው ቁርአናዊ ትምህርት አንዳንዶ ሙስሊሞች በሌሎች ሕዝቦች ላይ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ዘመቻ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ነው:: አፍሪካዊው የታሪክ ምሁር ጆን አለምቢላህ አዙማህ የአፍሪካውን ተሞክሮ በመጥቀስ ይህ የሙስሊሙ አስተሳሰብ ሙስሊሞች በአፍሪካውያን ላይ ጦርነት ለመክፈት እንዴት እንዳነሣሣቸው ጽፎአል:: አዙማህ በምዕራብ አፍሪካ አገሮች እስልምና የተስፋፋው በጂሐድ ጦርነት አማካይነት እንደ ሆነም በሰፋት አብራርቶአል[15]:: በሱዳን ለሩብ ምዕተ ዓመት የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት ያባባሰው፣ ሙስሊም ሱዳናውያን ለጂሐድ ጦርነት የነበራቸው አመለካከት ነው:: ይህ ሁኔታ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል መተማመን እንዳይፈጠር ትልቅ የሆነ እክል

[13] ዝኒ ከማሁ፤ 290::

[14] ዝኒ ከማሁ፤ 288-89::

[15] John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab-Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 63-108.

ፈጥሮአል:: በጦርነት መኻል ዕርቀ ሰላም ማውረድ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል አስቸጋሪ ጉዳይ ነው::

በሌላ አንጻር ደግሞ እስልምናን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት የሚፈልጉ ሙስሊም ሚስዮናውያን ተልእኮዋቸው መሠረት ያደረገው፣ ስለሰላም በቁርአን ውስጥ የተገለጹትን ምንባባት ነው:: በምሥራቅ አፍሪካና በኢንዶኔዥያ እስልምና የተስፋፋው በጦርነት ሳይሆን በንግድና በስደት ሲሆን፣ የእስልምናን ሃይማኖት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች በተለይም በሱፊ ሙስሊሞች አማካይነት ነው:: በጂሐድ ጦርነትም ሆነ በሰላማዊ መንገድ እልምናን ያስፋፉ ሙስሊሞች፣ "አላህ ለሰው ልጆች መለኮታዊ መልእክት ልኮአል፤ ሰዎች ሁሉ ለዚህ መልእክት ሊገዙ ይገባል" የሚል ተመሳሳይ ዐላማ ያነገቡ ናቸው::

## ሂሳዊ አስተሳሰብ

ሰዎች ታንዚልን መሠረት ስላደረገው መገለጥ ያላቸው ምልከታ፣ እውነትን ለማወቅ ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ይወስነዋል? በምዕራፍ ሦስት ላይ አዳም "ለእንስሳት ስም እንዲያወጣ ታዘዘ" በሚለው ርእስ ሥር ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጥተን ነበር:: የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ ወረደ (ታንዚል) የሚለው አስተሳሰብ፣ እግዚአብሔር ለአዳም የእንስሳትን ስም ሁሉ አስተማረው ከሚለው ቁርአናዊ ትምህርት ጋር ይስማማል:: አንድ ሰው ከሰማይ ተገለጠ ስለተባለው እውነትና ነጻ በሆነ መንገድ አእምሮውን በመጠቀም ከሚደርስበት እውነት ጋር እንዴት ይዛመዳል የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ይህ ጥያቄ ሙስሊሞችም ሆነ ክርስቲያኖች ሊመልሱት የሚገባ ዐቢይ ጥያቄ ነው:: ነገር ግን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለ መለኮታዊ መገለጥ ያላቸው አመለካከት የተለያየ መሆኑ ይህንን ጥያቄ በተለያየ መንገድ እንዲመልሱ ያደርጋቸዋልን?

ሻቢር አህታር የተባለው ዘመናዊ ሙስሊም ፈላስፋ በግሊዥያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎቹ እውነትን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና በጥያቄውም ላይ በግልጽነት መወያየት እንደሚያስፈልግ አስተያየቱን ሰጥቶአል:: የአህታር ባልንጀሮች ግን፣ "ሙስሊሞች...ሊማሩት የሚችሉት አንዳችም አዲስ ነገር የለም:: የምዕራባውያን ነጻ ምርመራ ዐላማ ቢስ ነው:: እግዚአብሔር እውነትን ሁሉ ስለገለጠልን ነጻ በሆነ መንገድ አእምሮአችንን



በመጠቀም ነገሮችን እንመርምር የሚለው ጥያቄ አስፈላጊ አይደለም" ሲሉ ይከራከራሉ[16]::

አህታር አብረውት ያሉትን የዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ፣ "እውነትን መፈለግና እውነትን መመዘን ያስችለናል በሚል ዘመናዊ ዩኒቨርስቲ አቋቁመን እውነት ሁሉ ተገልጦልኛል በሚል ጭፍን አመለካከት ውስጥ እንኖራለን...በማለት ይሞግታል"[17] አህታር ሙስሊሞች እውነትን በተመለከተ ማናቸውንም ዐይነት ጥያቄዎች እየጠየቁ እንዲወያዩ ያበረታታል:: አንዳንዴ ይህ ዐይነቱን አቋም ይዞ መኖሣት ብቸኛ ሊያደርግ ይችላል:: እውነትን ሁሉ እግዚአብሔር ገልጦልናል በአንጻሩ ደግሞ እውነትን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሣን በመወያየት እውነትን ማፈላለግ አለብን የሚሉት አመለካከቶች እርስ በርሳቸው ይስማሙ ይሆን?

# ተሰግዎና የክርስቲያኖች ተልእኮ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውን የሆነው የክርስቲያኖች ተልእኮ ምን እንደሚመስል በአጭሩ እንመለከታለን:: በጴንጤቆስጤ (በበዓለ ኀምሳ) ቀን በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች ሁሉ፣ ሐዋርያት ወንጌልን በእነርሱ ቋንቋ በመስበካቸው ምክንያት ተደንቀው ነበር:: ይህ ሕዝብ፣ "የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን" ሲሉ ተናግረዋል (ሐዋርያት ሥራ 2÷11):: ሐዋርያት በልሳን የተናገሩት ከዐሥራ ሁለት በሚበልጡ ቋንቋዎች ነው:: ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሰዎች ሁሉ በራሳቸው ቋንቋና ባህል ውስጥ የእግዚአብሔርን መልእክት መቀበል እንደሚችሉ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው::

## መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም

ከጴንጤቈስጤ (ከበዓለ ኀምሳ) ቀን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች በመተርጐም፣ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በራሳቸው ቋንቋ እንዲያነቡ/እንዲሰሙ ታላቅ ጥረት አድርጋለች:: ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲደርሳቸው ያደረገችበት ዐቢይ ምክንያት ምንድን ነው? ለዚህ መሠረታዊ

---

[16] Rippin, Muslims, 288.

[17] ዝኒ ከማሁ::

ምክንያቱ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ መገለጡ ነው። የወንጌልም መሠረታዊ ትምህርት አምላክ በመሲሑ በክርስቶስ አማካይነት ከእኛ ጋር ሆነ (አማኑኤል) የሚል ነው። እግዚአብሔር በአካል በመሲሑ በኩል በእስራኤል ባህል፣ ቋንቋ እንዲሁም ማኅበረሰብ ውስጥ ተገለጠ። በእርግጥ ከላይ እንደ ተመለከትነው ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ ተገልጦአል። እግዚአብሔር ቃሉን በሰዎች ቋንቋ አማካይነት ገለጠ። እርሱ እኛ ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ወደ እኛ በመምጣት በሙላት፣ በታላቅ ክብር እንዲሁም በማያሻማ ሁኔታ በክርስቶስ በኩል ተገናኘን።

ይህም ወንጌል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ ስለተገለጠ፣ ማንኛውም ዐይነት ባህልና ቋንቋ ሳይገድበው ይሠራል የሚለውን እንድምታ ታሳቢ ያደረገ ነው። ለምሳሌ አዲስ ኪዳን የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ቢሆንም፣ ወደ ግብፃውያን ቋንቋ ሲተረጐም እግዚአብሔር ለግሪኮች በግሪክ ቋንቋ የተናገረውን መልእክት ለግብፃውያን በግብፅ ቋንቋ ያንኑ መልእክት እንዲያውቁት አድርጓል። የግሪክ ክርስቲያኖችም በግብፅ ክርስቲያኖች ላይ አንዳችም ተጽእኖ ማድረግ በፍጹም አይችሉም። (የሚያሳዝነው ግን አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያናት በሌሎች አገሮች ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ተጽእኖ ሲደረግባቸው ይስተዋላል። ይህ ዐይነቱ ድርጊት የወንጌልን መልእክት ክፉኛ የሚጻረር ነው)።

ለብዙ ዓመታት በአውሮፓ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከወንጌሉ ባሕርይና ትምህርት ጋር የሚጻረሩ ተግባራትን ሲፈጽሙ ቆይተዋል። በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሌሎች ሕዝቦችን ትጨቁን የነበረው በላቲን ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በመጠቀም ነበር። በግብርና የሚተዳደረው የኅብረተሰብ ክፍል በላቲን የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብም ሆነ መረዳት አይችልም ነበር[18]።

በዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የማተሚያ መሣሪያ መፈልሰፉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያየ የአውሮፓውያን ቋንቋዎች እንዲተረጐም እንዲሁም የነጻነት እንቅስቃሴዎች በመላው አውሮፓ እንዲስፋፉ አስተዋጽኦ

[18] ይህ ዐይነቱ ችግር በኢትዮጵያ በምትገኘውም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት የሚስተዋል ዘመን የፈጀ ችግር ነው። ሥርዐተ አምልኮ በሚፈጸምበትም ጊዜ ሆነ፣ ስብከተ ወንጌልና ትምህርተ ወንጌል በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ የግእዝን ቋንቋ መጠቀሟ፣ በርካታ ምዕመናን የወንጌልን ትምህርት በትክክል እንዳይረዱ እክል ፈጥሮባቸው ይገኛል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ምሁራንና መሪዎች በጉዳዩ ላይ ሊመክሩ ለችግሩም ሁነኛ መፍትሔ ሊያፈላልጉ እንደሚገባ እናምናለን።



አድርጐአል። ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች በኋላ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ተቋቋሙ። በአውሮፓ በአጠቃላይ አዲስ በተፈጠሩ የክርስቲያን ኅብረቶች ውስጥ የወንጌል መልእክት ሥር እየሰደደ መጣ። የፕሮቴስታንት ተሐድሶና የዳግም መጥምቃውያን (የአናባፕቲስት) እንቅስቃሴ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረት ውጤቶች ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጕሞአል። የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ክፍሎች ሦስት ሺህ በሚሆኑ ቋንቋዎች የተተረጐሙ ሲሆን፣ ዘጠና አምስት ከመቶ ለሚሆነው የዓለማችን ነዋሪ በራሱ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ (ቢያንስ የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ክፍል) ተተርጕሞ ቀርቦለታል።

## መጽሐፍ ቅዱስን በተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጐም ጥቅም

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም፣ ሰዎች የቃለ እግዚአብሔርን ትምህርት እፍ በፈቱበት ቋንቋ አንብበው እንዲረዱ፣ መሲሑን እንዲቀበሉና የወንጌልን ትምህርት በራሳቸው ዐውድ ውስጥ እንዲያጣጥሙ ታላቅ ዕገዛ ያደርግላቸዋል። ያልተማሩ ሰዎች እንኳ አምልኮተ እግዚአብሔር በሚካሄድበት ወቅት የሚነበበውን የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት በትክክል እንዲረዱ እንዲሁም ጸሎታቸውን በራሳቸው ቋንቋ ወደ አምላካቸው እንዲያደርሱ ይረዳቸዋል። ወንጌል በራሳቸው ባህልና ቋንቋ ውስጥ ተጣጥሞ መገለጡ፣ ለእምነታቸው ጥንካሬ ይሰጣል። ይህ ዐይነት ሥራ፣ የኅብረተሰቡን ባህልና ቋንቋ ማዕከል ያደረገ ወንጌል የሚሰበክበት ስለሆነ ጠንካራ የሆነች ዐውዳዊ ቤተ ክርስቲያን ትመሠረታለች።
ላሚን ሳኔህ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐሙ ሁለት ዐይነት ችግሮችን ያስወግዳል ብለዋል። አንደኛው፣ አዲስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ከሚሲዮናውያን የባህል ተጽእኖ ነጻ እንድትወጣ ያደርጋታል። ሁለተኛው ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ በተመሠረተችበት አካባቢ ባለው ባህል ውስጥ ያለውን ክፉ ልምምድ አጥርታ እንድታይ ዕገዛ ያደርግላታል። በየትኛውም መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም፣ ወንጌል በኅብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ የሚያደርግ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም ለማኅበረሰቡ ጨውና ብርሃን በመሆን እኩይ የሆነውን ባህል የመለወጥ ዐቅም ታገኛለች[19]።

[19] Sanneh, *Translating the Message*, 157-209.

## ተሰግዎና ባህል

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም ስለዚያ ማኅበረሰብና ባህል ጥናት እንዲደረግ የሰዎችን ፍላጐት ከመቀስቀሱም ባሻገር የማኅበረሰቡ ባህል ተጠብቆ እንዲኖር ታላቅ ዕገዛ ያደርጋል። በዓለማችን በመቶዎች ለሚቈጠሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በቋንቋቸው የተጻፈው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በሚያደርጉትም ጥረት ውስጥ ከትምህርት ጋር እንዲተዋወቁ ትምህርት ቤቶችንም እንዲቈረቍሩ ምክንያት የሆነባቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ። ሰዎች በቋንቋቸውና በባህላቸው መኩራት ሲጀምሩ ባህላቸውና ቋንቋቸው ይታደሳል። እነርሱም "እግዚአብሔር በራሳችን ቋንቋ ውስጥ እየተናገረን ነው፤ ይህም አስደሳች ጕዳይ ነው" ይላሉ።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልእኮ መጽሐፍ ቅዱስን በኅብረተሰቡ ቋንቋ ማቅረብ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ በአሁኑ ዘመን በአፍሪካ አህጉር የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልእኮ የአፍሪካውያንን ባህል በመለወጥ በማቆየትና ሰዎች ለባህል ጥናት ፍላጐት እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የቀለም ትምህርት፣ የኅብረተሰብ ልማት፣ ሳይንሳዊ አብዮት፣ የሕክምና አገልግሎት እንዲሁም የማኅበረሰብ ጤና አጠባበቅ ትምህርት በአፍሪካ አህጉር ከቤተ ክርስቲያን የወንጌል አገልግሎት ጋር ተያይዘው የተከሠቱ ነገሮች ናቸው። በተጨማሪም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል፤ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ይወዳል፤ ያከብራል፤ እግዚአብሔር የሰዎችን ነጻነት ያከብራል፤ ክፉ መሪዎች በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት ስለሚቀርቡ እኩይ የሆነውን አስተዳደራዊ አካሄዳቸውን መቀየር አለባቸው የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትንና መንግሥታትን ለመመሥረት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል[20]።

በ1834 ዓ.ም የሞተውና የፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ ሆኖ ከእንግሊዝ ወደ ሕንድ የሄደው ዊሊያም ኬሪ "የሕንድ ቋንቋዎች አባት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ዊሊያም ኬሪና የእርሱ ሚስዮናዊ ቡድን የሕንድ ቋንቋዎችን ለማስተማር በሕንድ የቋንቋ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ስለነበር ነው። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ የተለያዩ መጻሕፍትን ለምሳሌ ስለባዮሎጂ፣ ስለሥነ እፅ፣ ስለግብርና፣ ስለታሪክ የሚያስተምሩ እንዲሁም

---

[20] Kwame Bediako, *Christianity in Africa: The Renewal of Non-Western Religion* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1995), 39-58, 172-188.



የሂንዱ ሃይማኖት መጻሕፍትን በአገሬው ቋንቋ አሳትመው ማቅረባቸው ነው ይህን ክብር እንዲጐናጸፉ ያደረጋቸው[21]።

ሕንዳውያን፣ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ወደ ህንድ አገር ከመግባታቸው በፊት ትምህርት ለመማር የሚመቸው ብቸኛው ቋንቋ የሂንዱ ሃይማኖት መጻሕፍት የተጻፉበት የሳንስክሪት ቋንቋ፣ ቁርአን የተጻፈበት የዐረብኛ ቋንቋ፣ የእንግሊዞቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው የሚል እምነት ነበራቸው። በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ስለቋንቋ የነበራቸው እምነት ከዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ፍጹም የተለየ ነበር። ዊሊያም ኬሪና የእርሱ ሚስዮናዊ ቡድን "ሴራምፖር ክርስቲያን ኮሌጅ" የተባለ፣ በእስያ የመጀመሪያው የሊበራል አርት ዩኒቨርስቲ ከፈቱ። የኮሌጁ ቀዳማይ ዐላማ ከሆኑት መኻል አንዱ በሕንድ በሚገኙ አካባቢዎች በሙሉ፣ በአገሬ ሰብ ቋንቋ ትምህርት ቤቶችን የሚጀምሩ መምህራንን ማሠልጠን ነበር። እያንዳንዱ ቋንቋ ክቡር ነው! እያንዳንዱ ሰው በአፍ መፍቻ ቋንቋው የማንበብ ዕድል ሊያገኝ ይገባዋል[22]።

## ስጦታት መጋስጥ

በተሰግዎ የተገለጠው ወንጌል ዘወትር ለጥቃት የተጋለጠ ነው። በማናቸውም ምክንያት ሰዎችን የማስገደድ ባሕርይ የለውም። ወንጌል እርስ በርስ የመከባበርን፣ የፍቅርንና የነጻነትን ዘር ይዘራል እንዲሁም ፍትሓዊ ያልሆኑና ሰዎችን የሚያዋርዱ ተግባሮችን አጥብቆ ይቃወማል። ለእምላክዋ ታማኝ የሆነች ቤተ ክርስቲያን የጌታ ጸጋና ተሰግዎን ያማከለ አገልግሎት የሚታይባት ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህ የመሲሑ አገልግሎት በተመሳሳይ መንገድ በክርስቶስ ሕይወት ጸጋና በአገልግሎት ለእኛ ተገለጠልን። የመሲሑ የፍቅር አገልግሎትና ምስክርነት እንዲሁም ይህ ዐይነቱ እውነት ዘወትር ለጥቃት የተጋለጠ ነው። መሲሑ ኢየሱስ የሞተበትም ዐቢይ ምክንያት ይኸው ነው። ከእርሱም ሞት የምንማረው ይህንኑ እውነት ነው።

እውነት ምንድን ነው? ሰዎች እውነትን ሊቈጣጠሩ እንዲሁም እውነትን ባሻቸው መንገድ ሊጠመዝዙ ይችላሉን? ምንም እንኳ ከላይ እንደ ተመለከትነው የፕሮፌሰር ሻቢር አህታር ተማሪ በዚህ ጕዳይ መረበሹን ቢናገርም ብሩሕ አመለካከት ላለው ምሁር ወንጌል ለዚህ ዐይነቱ ጕዳይ የሚሰጠው መልስ ምንድን ነው? የሚለውን በአንክሮ ሊመለከተው የሚገባው

---

[21] J. T. K. Daniel and R. E. Hedlund, *Carey's Obligation and India's Renaissance* (Serampore: Council of Serampore College, 1993), 153-298.

[22] ዝኒ ከማሁ፤ 153-175።

ጥያቄ ነው። ይህ እንዲያውም እንደዘበት እናንቀነው የምናልፈው ጥያቄ አይደለም። ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች የተገለጠውን መልእክት በመቀበልና ሌላ እውነት አለ ብሎ እውነታውን ለማወቅና እውነታውን ለመቀበል በሚደረገው ጥረት መካከል ያለውን ልዩነት ለማስታረቅ ይቸገራሉ። እውነት ለጥቃት የተጋለጠች በአንጻሩ ደግሞ ድል ነሺ ናት ወይስ እውነትን ሊያበላሹ ከሚነሡ ሰዎች መጠበቅ አለባት?

ዊሊያም ኬሪ ወንጌል ነጻ ያደርጋል፤ ኀይልም ይሰጣል። ስለ እውነት መመስከር እንጂ ስለ እውነት ጠበቃ መሆን አያስፈልግም ብሎ ስለሚያምን ሴራምፖር በሚገኘው የሊበራል አርት ኮሌጅ ተማሪዎች የተለያዩ ዐይነት ትምህርቶችን እንዲያጠኑ ይበረታቱ ነበር። ሳንስክሪትና የሂንዱ ሃይማኖት እንኳ የኮሌጁ ዋና የትምህርት ዘርፎች ነበሩ። የወንጌልም ትምህርት አብሮ ይሰጥ ነበር። ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ፣ እንዲመራመሩ እንዲሁም በወንጌል ውስጥ ስላለው እውነት በነጻነት የራሳቸው ውሳኔ እንዲወስኑ ተደርገዋል።

ዊሊያም ኬሪ ይህን መንገድ መከተሉ ትክክል ነውን? ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች የትኛውን መንገድ እንከተል በሚሉት ጉዳዮች ይቸገራሉ። አንድ ሰው ለተገለጠው እውነት ታማኝ እየሆነ በአንጻሩ ደግሞ ስለ እውነት ግልጽና ጥልቅ የሆኑ ጥያቄዎችን እየጠየቀና ለጥያቄዎቹም መልስ እያፈላለገ መኖር እንዴት ይችላል? የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች የእምነት ጉዞ የሚመራው ስለመለኮታዊ መገለጥ ባላቸው የተለያየ መረዳት ነው። ሙስሊሞች በታንዚል ክርስቲያኖች ደግሞ በተሰግዎ። እነዚህ የተለያዩ ምልከታዎች የሚያመጡት ልዩነት ምንድን ነው?

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ዮሐንስ 1+1-5:14

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 96+1-5

## <u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሰዎች እምነታቸውን እውነትን ሊያጠፉ በሚችል መንገድ ሲጠቀሙበት ያዩባቸው አጋጣሚዎች ካሉ በምሳሌነት ያቅርቧቸው።
2. የሙስሊሙ ኡማና ቤተ ክርስቲያን ለተገለጠላቸው እውነት ታማኞች ናቸው። የተገለጠውን እውነት አስመልክቶ በሙስሊሞችና



በክርስቲያኖች መካከል የሚደረጉ ውይይቶችን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች ምን ምን እንደ ሆኑ ይግለጹ።
3. ሙስሊሞች ስለታንዚል ያላቸው መረዳት ስለተለያዩ ባህሎች ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ወሰኖታል? ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ያላቸው እምነት ስለሌሎች ባህሎች ባላቸው አመለካከት ላይ ምን ዐይነት ተጽእኖ አስከትሎአል (ሐዋርያት ሥራ 2+5-12፣ ሱራ 12+2)?
4. ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ክፍሎች በሺዎች በሚቈጠሩ ቋንቋዎች ተርጉማለች። የሙስሊሙ ኡማ ግን ዐረብኛውን ቁርአን ይጠቀማል። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የራስዎትን አስተያየት ይስጡ (ማቴዎስ 1+23፤ ሱራ 16+103፤ 85+21-22)።
5. ጥልቅ ምርምርና ግልጽ የሆነ ጥናት የምዕራባውያን ዩኒቨርስቲዎች ቀዳማይ ተግባር ነው። እነዚህ ዩኒቨርስቲዎች ለቁርአንና ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ታማኝ ሆኖ ለሚኖረው የማኅበረሰብ ክፍል ያላቸው ተግዳሮት ምንድን ነው?

## ምዕራፍ ስምንት

# ኀይል

# ሒጅራ—መስቀል

ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን፣ "የእግዚአብሔር ሕዝብ" የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማዘጋጀት ላይ ሳለን፣ አንድ ባልንጀራዬ፣ "ሙስሊም ጓደኞቻችን ይህንን መጽሐፍ አይቀበሉትም" አለኝ:: በዚያን ጊዜ ስለኖኅና ስለጥፋት ውሃ ታሪክ የመጀመሪያውን ዙር ጽሑፌን አጠናቅቄ ነበር:: እኔ ግን ቁርአን ስለ ኖኅ ታሪክ ስለሚናገር ሙስሊሞች ስለ ኖኅ ለመማር ደስተኛ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነበርሁ::

ግማሽ ደርዘን የሚሆኑና ከእስልምና ወደ ጌታ የመጡትን አማኞች በአባልነት የያዘው የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድን አንዱ የሆነው ሰው የሰጠው አስተያየት፣ ስለ መጽሐፉ ይዘት ራሴን እንድጠይቅ አደረገኝ:: እኔም፣ "ይህ መጽሐፍ ሙስሊሞችን ሊያበሳጭ የሚችለው በምን ምክንያት ነው?" ስል ጠየቅሁ:: የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድኑ ዘፍጥረት 6+6 ላይ፣ "እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተፀፀተ በልቡም አዘነ" የሚለውን ክፍል ጠቀሱልኝ:: እኔም በአግራሞት፣ "ይህ ክፍል ሙስሊሞችን እንዴት ያበሳጫል?" ስል ጠየቅሁ:: በእኔ ግንዛቤ ማነስ ግራ በመጋባት፣ "አሁንም አልገባህም እንዴ?" በማለት የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድኑ ጠየቀኝ:: እነርሱም "በእስልምና እምነት እግዚአብሔር ሰዎች በሚሠሩት ነገር አይታወክም:: እርሱ ልዑልና ሁሉን ቻይ ነው:: እግዚአብሔር እኛ በምንሠራው ሥራ መቼም ቢሆን አዝናለሁ አይልም" አሉኝ::

በእስልምናና በወንጌል መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ እንመለከታለን:: እስልምናና ወንጌል ስለ እግዚአብሔር ኀያልነት ያስተምራሉ:: እስልምና ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ለሰዎች ሲል መከራን አይቀበልም ይላል:: ነገር ግን ወንጌል፣ ሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ለእኛ ሲል መከራን መቀበል እንደ መረጠ ያስተምረናል::

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በእስልምናና በወንጌል መካከል ያለውን ይህን ልዩነት በሰፊው ለመመልከት እንሞክራለን:: በዚህ ጥናታችን በተቃራኒ አቅጣጫ ያሉትን ሁለት የተለያዩ ጉዞዎች ማለትም ሒጅራንና መስቀልን

እንመለከታለን:: ሒጅራ ማለት መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ጉዞ ነው:: መስቀል ግን ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ከተጓዘ በኋላ በመስቀል ላይ በመሞት ጉዞውን ያጠናቀቀበት ስፍራ ነው:: የሒጅራና የመስቀል ጉዞዎች ስለ እግዚአብሔር ያለንን መረዳት በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነት የሚፈጥሩ ናቸው:: እነዚህ ትምህርቶች ስለ እስልምናም ሆነ ስለ ወንጌል መልእክት ከፍተኛ ትርጒም አላቸው:: እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ከእኛ ጋር በመሆን መከራን ይቀበላልን? ይህን ጥያቄ በተመለከተ ከእስልምናና ከወንጌል አንጻር የሚሰጡ ትምህርቶች ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና ለቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ናቸው::

በመጀመሪያ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መስቀል ያደረገውን ጉዞ በአሰሳ መልክ የምንቃኝ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደጉትን ጉዞ (ሒጅራ) እንመለከታለን:: እነዚህ ጉዞዎች እኛ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያለንን መረዳት እምነት ምን ዐይነት መረጃዎች ይሰጣሉ?

## ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ

ኢየሱስ ገሊላ ተብሎ በሚጠራው በሰሜናዊ ኢየሩሳሌም ይኖር ነበረ:: ኢየሱስ በጣም ደስተኛ ነበር:: ሐዋርያው ጴጥሮስ እርሱና ሌሎች ሐዋርያት በኢየሱስ ላይ ያላቸው እምነት ምን እንደሚመስል እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ:— "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ"::

ኢየሱስ በጴጥሮስ ንግግር በመደሰት:— "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ:: እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ገሀነም ደጆችም አይችሉአትም" (ማቴዎስ 16+17-18) ሲል ተናገረ::

ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ የመሰከሩት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ መሲሕነቱ ከእርሱ ጋር በገሊላ በሚኖሩ ሰዎች መካከልም የታወቀ ጉዳይ ነበር:: በተለይም ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ አምስት ሺህ ወንዶችን ከመገበ በኋላ፣ የክርስቶስ ዝና በገሊላ ምድር ሁሉ ተሰማ:: ኢየሱስ ይህንን ሕዝብ የመገበው አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ በመባረክ ነበር:: በዚያ የነበሩ ሰዎች በሥራው በመደነቅ ንጉሣቸው እንዲሆን ጠየቁት::



በዚያን ጊዜ የተወሰኑ የገሊላ ሰዎች የሮማ መንግሥትን አገዛዝ በመቃወም በስውር ይዋጉ ነበር:: እነዚህ ቡድኖች፣ "ቀናተኞች" ("ቀናይያን") በሚል ስያሜ ይታወቁ ነበር:: ኢየሱስን ንጉሣቸው ቢያደርጉ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ጥቂቱን ምግብ በመባረክ ወታደሮቻችንን ይቀልብልናል የሚል ስሜት አድርባቸው ነበር:: የገሊላ ሰዎች በኀይልም እንኳ ቢሆን፣ ኢየሱስን ንጉሣቸው ለማድረግ ተዘጋጅተው ነበር (ዮሐንስ 6+15)::

ኢየሱስ ንጉሥ እንዲሆን የቀረበለትን ጥሪ በመቃወም፣ ከሕዝቡ ተለይቶ ወደ ተራራ በመውጣት ሌሊቱን ሙሉ ሲጸልይ ዐደረ:: ከዚያ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና (ሉቃስ 9+51):: የሚያስደንቀው ጉዳይ ግን ኢየሱስ በኢየሩሳሌም የመስቀል ሞት እንደሚጠብቀው ያውቅ ነበር:: ለደቀ መዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ሰዎች የሰው ልጅን "ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል በሦስተኛውም ቀን ይነሣል" (ሉቃስ 18+32-33) ብሎ ይናገራቸው ነበር:: ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ባለበት ሁኔታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ::

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እርሱ መሲሕ እንደ ሆነ ያምኑ ነበር፤ ሆኖም ግን ተሰቅሎ እንደሚሞት በጭራሽ አላወቁም:: እንዲያውም ይህን ሁኔታ ባወቁ ጊዜ እንኳ ጉዳዩን ለመቀበል በብዙ ተቸግረው ነበር:: መሲሑ ይሰቀላል ብሎ ማሰብ በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ነበር:: በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ ስለ ስቅለቱ ሲናገር ጴጥሮስ ወደ እርሱ ወስዶ ኢየሱስን ይገስፀው ጀመር:: ነገር ግን ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና እንቅፋት ሆነህብኛል አለው" (ማቴዎስ 16+23)::

በኢየሩሳሌም ኢየሱስ ተይዞ ከታሰረ በኋላ፣ የመስቀል ላይ ሞት ፍርድ ተፈረደበት:: በዚያም ሰዓት እርሱ ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክትን መጥራት እንደሚችል ተናገረ (ማቴዎስ 26+53):: ይህ ማለት ሰባ ሁለት ሺህ የሚሆን የመላእክት ሰራዊት ማለት ነው:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀል ሞት ሊያድነው የሚያስችል የሰውም ሆነ የመላእክት ድጋፍ አልፈለገም::

ኢየሱስን የያዙ ሰዎች ለፍርድ ወደ ጲላጦስ ወሰዱት:: በዚያን ጊዜ ጲላጦስ የሮም አስተዳዳሪ ነበር:: ኢየሱስም በጲላጦስ የንጉሥ ችሎት ፊት እንዲህ ሲል ተናገረ፣ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው" (ዮሐንስ 18+36)::

ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት ገረፉት፤ አፌዙበትም፤ ምራቃቸውንም ፊቱ ላይ ተፉ። እንዲሁም የእሾኽ ጉንጉን ሠርተው በጭንቅላቱ ላይ አኖሩ። ጫፉ ከብረት በተሠራ ጅራፍም ገረፉት። ዐይኑንም አስረው ተሳለቁበት። ከዚህ በኋላ እጁንና እግሩን በምስማር ቸንከረው በሁለት ወንበዴዎች መካከል በመስቀል ላይ ሰቅለው ገደሉት። በሞት መካከል እያጣጣረ ሳለም በእርሱ ላይ መሣለቃቸውን አላቆሙም ነበር። ሞቱ ሲቃረብ በታላቅ ድምፅ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ" (ሉቃስ 23፥34)። ከዚያም "ተፈጸመ" ብሎ ነፍሱን ሰጠ (ዮሐንስ 19፥30)። ክርስቶስ በሞተበት ቅጽበት፣ "እነሆም የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተናወጠች፤ ዐለቶችም ተሰነጠቁ፤ መቃብሮችም ተከፈቱ፤ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ" (ማቴዎስ 27፥51-52)።

ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ መሞቱን ለማረጋገጥ ከሮማ ወታደሮች አንዱ ጐኑን በጦር ወጋው። ደምና ውሃ ከተወጋው ስፍራ ወጣ። የኢየሱስ ወዳጆች አስከሬኑን ወስደው ቅርብ በነበረ መቃብር ቀበሩት። የክርስቶስን አስከሬን ደቀ መዛሙርቱ እንዳይሰርቁት በሚል የሮማ መንግሥት የመቃብሩ በር በትልቅ ድንጋይ እንዲዘጋ ካደረገ በኋላ፣ ጠባቂ ወታደሮችን አስቀመጠ። ነገር ግን እግዚአብሔር ድንጋዩን ያንከባልሉ ዘንድ መላእክቶቹን ላከ። ይህም የሆነው ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ወይም ክርስቶስ ከተቀበረ በሦስተኛው ቀን ነው። ብዙ ሴቶች መቃብሩን ለማየት ሲመጡ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙ። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን አስነሥቶታልና!

ከዚያ በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተደጋጋሚ ሲታያቸው እንደቆየ ወንጌላት ያስተምራሉ። ቢያንስ ዐሥራ አንድ ጊዜ ያህል የታያቸው ሲሆን፣ በአንዱ አጋጣሚ ደግሞ አምስት መቶ ለሚሆኑ ሰዎች በአንድ ጊዜ ታይቶአል። ኢየሱስ፣ ከሙታን መነሣቱን ይጠራጠር ለነበረው ሐዋርያ (ቶማስ) በምስማር የተቸነከሩትን እጆቹንና እግሮቹን አሳይቶታል።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከታየባቸው አጋጣሚዎች አንዱ እንዲህ ተጽፎአል፡—

> ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡— ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንም ጐኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው። ኢየሱስም ዳግመኛ፡— ሰላም ለእናንተ ይሁን፣ አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡— መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (ዮሐንስ 20፥19-22)።



## የመሐመድ ወደ መዲና መሰደድ

ከክርስቶስ ልደት ከስድስት ምዕተ ዓመት በኋላ፣ መሐመድ የሳውዲት ዐረቢያ ምድር በሆነችው በመካ ከተማ የእስልምናን ሃይማኖት መስበክ ጀመሩ። የስብከታቸውን መልእክት የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ዘንድ በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት እንደ ሆነ ይናገሩ ነበር። ለዐሥራ ሁለት ዓመታት የተገለጠላቸውን የቁርአንን የተወሰኑ ክፍሎች እንደ ሰበኩ ይታመናል። የዐረቢያ ነዋሪዎች ከጣዖት አምልኮ እንዲመለሱ፣ ክፉ ተግባራትን እንዳይፈጽሙና ማኅበራዊ ፍትሕን እንዲያስጠብቁ ማስጠንቀቂያ ይሰጡ ነበር።

መሐመድ ከሕዝቡ ዘንድ የቀረበላቸው ምላሽ መዘባበቻ መሆን ነበር። ሕይወታቸውም አደጋ ውስጥ ነበር። ቢያንስ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግረዋል፤ ሰዎች ቆሻሻ ጥለውባቸዋል። እስልምናን ከተቀበሉ ሰዎችም መኻል አንዳንዶቹ ተደብድበዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ተገድለዋል። የተቀሩት ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዋል[1]። በወቅቱ ባመኑና ባላመኑ ሰዎች መካከል የነበረው ትግል ቀላል አልነበረም።

እግዚአብሔር ኀያል አምላክ ከሆነ ሙስሊም አማኞች ለምን ይሠቃያሉ? እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ከሆነ የመሐመድ ሕይወት አደጋ ላይ የወደቀው ለምንድን ነው? የእስልምና እምነት የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ለምን የሙስሊም ኡማ መመሥረት አልተቻለም? እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች በመካ የነበሩትን ሙስሊሞች ግራ ያጋቡና ጥርጣሬ ውስጥ የጣሉ ነበሩ። እነዚህ ጥያቄዎች ስለእግዚአብሔር ባሕርይና ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት ምርምር ውስጥ የሚከቱን ናቸው።

ምንም እንኳ ሙስሊሞች በመካ የነበራቸው ሕይወት በብዙ ችግሮችና ነገረ መለኮታዊ ግራ መጋባቶች የተሞላ ቢሆንም፣ የመሐመድ ሁለቱ ጉዞዎች (ሚዕራጅና ሒጅራ) ሙስሊሞችና መሐመድ እንዲበረታቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው።

---

[1] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 71-72.

ሚዕራጅ መሐመድ በአንድ ምሽት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ምሥጢራዊ ጉዞ ነው:: ጉዞው ሁለት ደረጃዎች አሉት:: አንደኛው ኢስራዕ የሚባለው ሲሆን፣ መሐመድ አል ባራቅ በምትባል ክንፍ ባላትና ፈረስ በምትመስል እንስሳ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ጉዞ ነው:: ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ መሐመድ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሱ ከፈረሰበት ስፍራ ወደ ሰባተኛው ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ነው:: ይህም ሚዕራጅ ተብሎ ይጠራል[2]::

የሚዕራጅ ጉዞ ኢየሳሌምና ቤተ መቅደሱ የፈረሰበት ስፍራ በእስልምና እምነት ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል:: የፈረሰው ቤተ መቅደስ በሙስሊሞች አል-አቅሳ ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፣ መሐመድ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረጉት ጉዞ ያረፉበት ቦታ ነው:: ምንም እንኳ ቁርአን ስለሚዕራጅ ጉዞ ግልጽ አድርጎ ባያስተምርም የሙስሊሙ የትውፊት መጽሐፍ ይህ ጉዞ ለመሐመድ ትልቅ ብርታት የሰጣቸው ተአምራዊ ጉዞ እንደ ነበር ዘግቦአል (ሱራ 17፥1)::

ሒጅራ የተሰኘው ሌላኛው ጉዞ በመሐመድ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ ተግባራዊ ገጽታ አለው:: መሐመድ በመካ በብዙ መከራ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ መልካም የምሥራች ከያትሪብ (መዲና) መጣላቸው:: የመዲና ከተማ ከመካ በስተሰሜን 250 ማይል ርቀት ላይ ይገኛል:: በዚያን ጊዜ በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሽማግሌዎች መሐመድንና ተከታዮቻቸውን ወደ መዲና እንዲመጡ ጋበዟቸው:: በመዲና የጐሣ ክፍፍልና ጦርነት ስለነበር መሐመድ ከተማዪቱን እንዲያስተዳድሩና ሰላምን እንዲያሰፍኑ ሥልጣን ሰጧቸው::

መሐመድና በመቶዎች የሚቈጠሩት የመካ ሙስሊሞች የመዲናውያንን የስደት ጥሪ በምሥጢር ተቀብለዋል:: እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ622 ዓ.ም ማለትም መሐመድ በመካ መስበክ ከጀመሩበት ከዐሥራ ሁለት ዓመት በኋላ፣ ሙስሊሞች ወደ መዲና ተሰደዱ:: ስደቱ በምሥጢር ለብዙ ወራት ቀጥሎ ነበር:: በዚሁ ዓመት በመስከረም 24 ቀን መሐመድ ወደ መዲና ሲደርሱ፣ በዚያ የነበሩ ሰዎች በታላቅ ደስታ ተቀበሏቸው:: የመዲና ከተማ ሁከት የነገሠባት ከተማ ስለነበረች የመዲና ነዋሪዎች መሐመድ ለከተማዪቱ ሰላም ያወርዳሉ የሚል ተስፋ ነበራቸው::

[2] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1968), 691-93.



መሐመድ በመዲና ከነቢይነት በተጨማሪ የአገር አስተዳዳሪና የጦር መሪ ሆኑ[3]:: ይህንን የፖለቲካ የበላይነት በመጠቀም መሐመድና ተከታዮቻቸው የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መሠረቱ:: ወደ ዓለም ሁሉ የተሠራጨው የሙስሊም ማኅበረሰብ መሠረቱን የጣለው በመዲና ነው::

መሐመድና ሙስሊሞች ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት የስደት ጉዞ ሒጅራ ተብሎ ይጠራል:: ይህ ክሥተት በእስልምና አዲስ ምዕራፍ ከፍቶአል:: የእስልምና ዘመን የተጀመረው በመሐመድ ልደት እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 570 ዓ.ም ወይም ለመሐመድ የመጀመሪያው መገለጥ በሒራ ዋሻ ውስጥ እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ610 ዓ.ም በመጣላቸው ጊዜ አይደለም:: የእስልምና ዘመን የጀመረው በመካ፣ በችግርና በመከራ ውስጥ የነበሩት መሐመድ ወደ መዲና በመሰደድ ባለሥልጣን እንዲሁም ባለብዙ ኀይል መሆን ሲጀምሩ ነው::

ሙስሊሞች ይህ ክሥተት መሐመድ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጥ ከሙሉ ልባቸው ይቀበላሉ:: መሐመድና ሙስሊሞች በተፈጠረላቸው የፖለቲካና የጦር የበላይነት ስኬታማ መሆን ችለዋል:: ሙስሊሞች ይህ ስኬት የመሐመድን ነቢይነትና የእስልምናን እውነት የሚያረጋግጥና ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው የሚል አቋም አላቸው:: ቁርአን ይህንን ሐሳብ ሲያብራራ:—

> እነዚህ የካዱት ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም (ከመካ) ሊያወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ (አስታውስ)፤ ይመክራሉም አላህም ተንኰላቸውን ይመልስባቸዋል፤ አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው (ሱራ 8፥30 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ይህ የቁርአን አንቀጽ አላህ ከፋዎችን ለመቅጣት መከራን እንደሚያመጣ የሚገልጽ ነው:: በመዲና የነበረው ሁኔታ በመካ የነበረውን ችግርና ስደት ያካክስ ነበር:: አሁንም ሙስሊሞች ማሸነፍ አለባቸው፤ እግዚአብሔርን የሚገዙ ሰዎች አሸናፊዎች ናቸውና የሚል አስተሳሰብ አለ::

## እርስ በርስ የሚቃረኑ ጉዞዎች

መሲሑ ኢየሱስና የእስልምናው ነቢይ መሐመድ በተቃራኒ አቅጣጫዎች ተጕዘዋል:: ኢየሱስ ከብዙ ሰራዊት ጋር ንጉሥ እንዲሆን ሲጠየቅ ጥሪውን ወደ

[3] W. Montgomery Watt, *Muhammad: Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1961), 82-228.

ጉን በመተው በመስቀል ላይ ለመሞት ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቀና። ነገር ግን መሐመድ ከመዲና መሪ እንዲሆኑ ለመጣላቸው ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት በመካ የነበረውን አገልግሎት በመተው ወደ መዲና ተጓዙ። እነዚህ የኢየሱስና የመሐመድ የተለያዩ የሕይወት ጉዞዎች ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና ለቤተ ክርስቲያን ሥነ ምግባራዊ ሕይወት መሠረቶች ናቸው። የክርስቲያን ሥነ ምግባር የመስቀሉን መንገድ መከተል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ያሳየውን የሕይወት ጉዞ እንዲከተሉ ጥሪ ያደርጋል:—

> የተጠራችሁ ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኀጢአት አላደረገም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ (1ጴጥሮስ 2፥21-23)።

የሒጅራ ጉዞና እንዲሁም ከዚያ በኋላ የነበረው የመዲና ሁኔታ፣ ሙስሊሞች ስለ ሥነ ምግባር ያላቸውን አመለካከት በእጅጉ ቀርጾታል። ቁርአን ሙስሊሞች አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ ያስተምራል:—

> እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሐዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፤ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት...ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሐዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው...እውከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው፤ ቢከለከሉም ወሰንን ማለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው) (ሱራ 2፥190-193 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

የእግዚአብሔር ልዕልናና ኀይል በእነዚህ ሁለት ጉዞዎች ውስጥ ትልቅ ስፍራ አላቸው። በወንጌላት መሲሑ የመከራንና የድካምን መንገድ እንደ መረጠ እናነባለን። እርሱ አምላክ ነው፤ ነገር ግን ወደ ምድር መምጣትን መረጠ። የሰውንም ሥጋ ለበሰ፤ ራሱን አዋረደ። የባሪያን መልክ ያዘ። እርሱ በመስቀል ላይ እንኳ ለመሞት የታዘዘ ሆነ። "በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው" (ፊልጵስዩስ 2፥9-11)።



በእስልምና እምነት መሐመድ በሒጅራ ጉዞ ያገኙት ስኬት፣ በምድር ላይ የእግዚአብሔር አስተዳደር ባለበት ሁሉ ድል አለ ለሚለው የሙስሊም ኡማ አስተሳሰብ መሠረት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲሰፍን የፖለቲካና የኀይል የበላይነት አስፈላጊ ነው። ስደትና መከራ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚገዙ የተገባ አይደለም። ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች የመስቀልን ታሪክ ይቃወማሉ፤ መሲሑ በመስቀል ላይ ሊሞት ከቶ አይችልም ይላሉ።

## ስለ መሲሑ የሙስሊሞች ሙግት

በመዲና የነበሩ አይሁዶች መሲሑ በመስቀል ላይ እንደማይሞት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተጻፈ ይናገሩ ነበር። ከዚህም የተነሣ ነበር ኢየሱስ መሲሕ ነው የሚለውን እውነታ የተቃወሙት። አይሁዶች መሲሑ በመስቀል ሊሞት አይችልም የሚለውን አቋም መሠረት ስለሚያደርጉ፣ ኢየሱስ መሲሕ ነው የሚለውን የሙስሊሞችን እምነት ይቃወሙ ነበር። አይሁዶች ኢየሱስ በፍጹም መሲሕ ሊሆን አይችልም ሲሉ ተከራክረዋል፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶአልና።

ከዚህ ምዕራፍ በፊት ሙስሊሞች ስለክርስቶስ ሞት ያላቸውን ተቃውሞ ተናግረን ነበር (ሱራ 4፥157)። ይህ የቁርአን ዐውድ በነቢዩ መሐመድ የተነገረው፣ በመዲና የሚኖሩ አይሁዶች ከሙስሊሞች ጋር ግጭት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ነው። መሐመድ ኢየሱስ መሲሕ ነው ነገር ግን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም ሲሉ አይሁዶችን ተቃወሙ።

እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንዲሁም ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ እግዚአብሔር መሲሑን ለመከራ አሳልፎ ሊሰጠው በጭራሽ አይችልም። እግዚአብሔር መሐመድን በመካ ከነበረው መከራ እንዳስመለጣቸው ሁሉ ኢየሱስንም በመስቀል ላይ ሊደርስበት ከነበረው መከራ አስመልጦታል። እግዚአብሔር ግራ መጋባትን በአይሁዶች ላይ ላከ፤ በኢየሱስም ፈንታ ሌላ ሰው ተሰቀለ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከሞት አስመልጦታል። ኢየሱስ ወደ ፊት ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ለማዘጋጀት ዳግም ወደዚህ ምድር ተመልሶ ይመጣል። እግዚአብሔር መሲሑ በመስቀል ተሰቅሎ እንዳይሞት ትድግናውን አሳይቶአል።

የሙስሊሙ ኡማ ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ለማስረገጥ የክርስቶስን ሞት አጥብቆ ተቃውሞአል። ይሁን እንጂ ኡማው ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ የተሄደበት መንገድ እግዚአብሔር በወንጌሉ ያስቀመጠውን እውነት

ያገናዘበ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የወንጌሉን እውነትና የተገለጠውን ተአምር ዳባ ልበስ እንዲል አድርጎታል። አሳዛኙ እውነት ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚለው ይህ አስተሳሰብ በሙስሊሞች ዘንድ ሁሉ ተቀባይነት ማግኘቱ ነው።

## የመስቀሉ መሰናክልነት

አንድ ቀን የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁር ለሆነ ሰው እንዲህ ስል ተናገርሁ:— "በእኔ ግንዛቤ፣ ስለ ኢየሱስ ስቅለት፣ ሞትና ትንሣኤ የሚያስተምሩ የቁርአን ጥቅሶች ግልጽነት የሚጐድላቸው እንዲያውም እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ይመስለኛል። ሁነኛ የሆነ ምርመራና ጥናት ሙስሊሞች የክርስቶስን ስቅለት ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በሮችን ሊከፍትላቸው አይችልምን?" እርሱም ሲመልስልኝ:— "ጥሩ ዐይነት ዕይታ ነው ያለህ። የቁርአንን ጥቅሶች በተመለከተ አንተ ያልኸው እውነት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ስለክርስቶስ ሞት የእኛ የሙስሊሞች ተቃውሞ በአንድ ወይም በሁለት ጥቅሶች ላይ የተወሰነ ብቻ ሳይሆን፣ ከእስልምና ነገረ መለኮት ጋር የተያያዘ ነው። እግዚአብሔር መከራን ሊቀበል አይችልም"።

ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ሲወያዩ ሙስሊሞች ስለ ክርስቶስ ስቅለትና ሞት በተደጋጋሚ ሲቃወሙ ይስተዋላል። ታሪፍ ኸሊድ የተባለው ሰው "የሙስሊሞቹ ኢየሱስ" በሚለው መጽሐፉ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ:— "ወንጌላት ስለ ክርስቶስ ሞት ትኩረት ሲሰጡ ቁርአን ግን ስለ ኢየሱስ መከራና ሞት ከማስተማር ይልቅ ተአምራዊ በሆነው ልደቱ ላይ ትኩረት ይሰጣል" ብሎአል[4]።

በዓለማችን ምሥራቅና ምዕራብ ጫፍ ባሉ ሁለት አገሮች ላይ የተደረጉ ውይይቶች ይህንን ርእሰ ጉዳይ በበለጠ የሚያብራሩ ናቸው። የመጀመሪያው ውይይት የተደረገው እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ በኒው ዮርክ ከተማ "የእግዚአብሔር ሣጥን" ተብሎ በሚጠራውና የሣጥን ቅርጽ ባለው ብሔራዊ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ፣ በሙስሊሞች የነገረ መለኮት ሰዎችና በክርስትና የነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ በተካሄደው ውይይት ተካፋይ ነበርሁ። የውይይቱ እንግዶች የሳሙኤል ዝዊመር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ቄስ ዶን ማክኩሪ እና

[4] Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge, Mass.: Harvard University Press, 2001), 14.



በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የእስልምና ማዕከል ዳይሬክተር የነበሩት ዶክተር አብድል ራውፍ ናቸው።

በውይይታችን ማጠቃለያ ላይ ዶክተር አብድል ራውፍ "በእውነቱ እናንተ መሲሑ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ ብላችሁ ታምናላችሁን?" ሲሉ ታዳሚውን ጠየቁ። እኛም "እንዴታ! በመሲሑ መስቀል እግዚአብሔር ለእኛ ሲል መከራን መቀበሉን እንዲሁም ለሰው ልጆች ራሱን አሳልፎ የሰጠበትን ፍቅር ለማየት ችለናል" አልናቸው። ዶክተር አብድል ራውፍ ቍጣ በተቀላቀለበት መንፈስ፣ "ይህ እንዴት ይሆናል? መሲሑ በመስቀል ላይ ሞተ ማለት እግዚአብሔር ደካማ ነው ማለት ነው። ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም" አሉ።

ሁለተኛውን ውይይት ያካሄድሁት፣ በኒው ዮርክ የተደረገው ውይይት ከተካሄደ ከስድስት ወር በኋላ፣ ራቅ ወዳለው የባንግላዴሽ የገጠር መንደር በሄድሁበት ወቅት ነበር። በአንድ ምሽት ፊደል ካልቈጠሩ ገበሬዎች ጋር ቁጭ ብለን በምንወያይበት ወቅት እንዲህ የሚል ጥያቄ ጠየቅኋቸው:— "እኔ ክርስቲያን እንግዳችሁ እንደ መሆኔ መጠን ልትጠይቁኝ የምትፈልጉት ጥያቄ አላችሁን?" እነርሱም፣ "አዎን" አሉኝ። "ክርስቲያኖች መሲሑ በመስቀል ላይ ተሰቅሎአል ብለው እንደሚያምኑ ሰምተናል። ምን ዐይነት እንግዳ ትምህርት ነው! አንተም እንደነርሱ ታምናለህን?" አሉኝ።

እኔም "አዎን እኔም እንደ እነርሱ አምናለሁ" አልኋቸው። ገበሬዎቹም "ይህ በፍጹም ሊሆን አይገባውም" ሲሉ መለሱልኝ። በመቀጠልም፣ "እግዚአብሔር ልዑል አምላክ ስለሆነ መሲሑ በእንዲህ ዐይነት አሳፋሪ ሁኔታ መከራን አይቀበልም" አሉ።

እነዚህ ሁለት ውይይቶች ተቃራኒ በሆኑ የዓለማችን ክፍሎች የተካሄዱ ውይይቶች ናቸው። አንደኛው ውይይት በነገረ መለኮት ሊቃውንት እንዲሁም በዶክተሮች መካከል የተደረገ ውይይት ሲሆን ሁለተኛው ባልተማሩ ገበሬዎችና በእኔ መካከል የተደረገ ነው። ነገር ግን በሁለቱም ውይይቶች ውስጥ የምንገነዘበው ጉዳይ መስቀሉ የማሰናከያ ዐለት መሆኑን ነው።

## ሰላምን መሻት

ምንም እንኳ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚል አቋም ቢያራምድም፣ አንዳንድ ሙስሊሞች ግን ስለ ክርስቶስ መስቀል ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጐት አድሮባቸዋል። መሐመድ ካሚል ሑሴይን የተባሉ ጸሓፊ፣

"የስሕተት ከተማ" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፍ፣ ኢየሱስ እንዲታሰርና መከራ እንዲቀበል ምክንያት የሆነው፣ መንፈሳዊ መሪዎችና የፖለቲካ መሪዎች ስለ እርሱ በነበራቸው ጥላቻ እንደ ሆነ አብራርተዋል:: ይሁን እንጂ በመጽሐፋቸው መጨረሻ ላይ፣ ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ በነበረው ግርግርና ሰዎች በጨለማው ምክንያት ግራ እየተጋቡ ሳሉ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት አስመልጦታል ብለዋል[5]::

በጀርመን አገር ለአራት ቀናት የሺአይት ሙስሊም ከሆነች ሴት ጋር በነበረኝ ውይይት፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶአል የሚለውን አስተምህሮ በጥልቀት ለማወቅ ፍላጐት እንዳደረባት ነገረችኝ:: ነገር ግን በመስቀል ላይ የሞተው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም የሚል የጸና አቋም እንዳላት ገልጻልኛለች::

አንዳንድ የእስልምና ቡድኖች ለእምነት ሲባል መከራን መቀበል የታማኝነት ምልክት ነው ይላሉ:: በምዕራብ አፍሪካ ካሉ የእስልምና እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ጦረኛ እንቅስቃሴን ይቃወማሉ[6]:: ብዙዎቹ የሱፊ እስልምና ቡድኖች ለእምነት መከራን መቀበልንም ሆነ ሰማዕት መሆንን ይደግፋሉ:: አንዳንድ የሺአ ሙስሊሞች እንደዚህ ዐይነት አመለካከት አላቸው:: በሙስሊም ኡማ እምነትና ሕይወት ውስጥ መልካምነት፣ ትኅትናና የአክብሮት መንፈስ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደሚንፀባረቅ መዘንጋት የለብንም::

ይሁንና ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን ላለው የመስቀል ትርጓሜ የሚሰጡት ምላሽ ስለክርስቶስ ባላቸው አመለካከት ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው:: በሶማሊያ በመምህርነት በሠራሁባቸው ጊዜያት አንዳንዴ ከሙስሊም ተማሪዎች ጋር በአቅራቢያችን በሚገኘው ሻይ ቤት አብረን ሻይ እንጠጣ ነበር:: አንድ ምሽት ሰላምን መፍጠር እንዴት ይቻላል በሚለው ርእስ ጉዳይ ላይ ተነጋገርን::

በውይይታችን መካከል አንድ ሙስሊም ተማሪ፣ "እስልምና የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ሃይማኖት ነው" አለኝ:: በመቀጠልም "አንተ አንድ ጉንጬን ብትመታኝ፣ ሁለተኛ እንዳትመታኝ ያንተን ጉንጭ አንተ ከመታኸኝ ምት በተሻለ ሁኔታ መምታት አለብኝ በእስልምና አስተምህሮ ሰላም የሚመጣው

[5] Muhammad Kamil Husain, *City of Wrong*, translated by Kenneth Cragg (Oxford: Oneworld Publications, 1995).

[6] Lamin Sanneh, *Piety and Power: Muslims and Christians in West Africa* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1996), 73, 123-24.



በዚህ መንገድ ነው:: ነገር ግን የመሲሑ የኢየሱስ አስተምህሮ ነባራዊውን ሁኔታን ያላገናዘበ ስለሆነ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም:: እርሱ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ አስተምሮአል:: እንዲያውም አንድ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውን አዙርለት ብሎአል:: ሰላምን በዚህ መልኩ ማስፈን በፍጹም አይቻልም"::

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት:— "አንተ በእኔ ላይ ስላደረግኸው ክፉ ነገር አጸፋውን ብመልስ፣ አንተ ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ በሌላ ጊዜ ጠብቀህ ትበቀለኛለህ:: ስለዚህ አንዱ በቀል ሌላ በቀል እየወለደ ይቀጥላል እንጂ ሰላም አይመጣም:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ የበደሉትን ሰዎች ከልብ በመነጨ ፍቅር ይቅር አላቸው:: እንዲህ ዐይነት አስደናቂ ይቅርታ በቀል እንዳይቀጥል ያደርጋል"::

በዚያች ምሽት ከእኔ ጋር ሻይ ሲጠጡ የነበሩ ተማሪዎች እኔ የነገርኋቸው ሰላምን የመከተል መንገድ ብዙም አልተዋጠላቸውም:: ከእስልምና በፊት በዐረብያ ባህላዊ እምነት ይከተሉ የነበሩ ዐረቦች፣ "ጠላቶቹን የማይበቀል ሰው ሌሎች ሰዎች ያጠቁታል"[7] ሲሉ የተናገሩትን ንግግር በሙስሊሞቹ አስተምህሮ ውስጥ አይቼዋለሁ:: በዚህ አባባልና ሙስሊሞች ሰላምን ለማምጣት በሚጠቀሙበት ዘዴ መካከል አንዳችም ልዩነት የለም::

ሶማሊያንና የሶማሊያን ሕዝብ እያጠፋ ያለውን ፍጅት ባሰብሁ ጊዜ ሁሉ፣ ከተማሪዎቼ ጋር ያደረግሁት ይህ ውይይት እፊቴ ላይ ድቅን ይላል:: በሶማሊያ ጐሣዎች መካከል እየተካሄደ ያለው የእርስ በርስ በቀል ለረጅም ዓመታት ሳይቋረጥ መካሄዱ፣ አገሪቱን ባድማ ከማድረጉ ማሻገር ሕዝቡን ለስደትና ለረሀብ ዳርጎታል::
የሒጅራ ነገረ መለኮት አንዳችም ዐይነት ሽንፈትን ወይም ለጥቃት የመጋለጥን መንገድ አይከፍትም:: መሐመድ ከመካ ወደ መዲና እንደ ተሰደዱት፣ በሃይማኖት ምክንያት የሚመጣ ጊዜያዊ ስደት ወይም መከራ ተገቢ እንደ ሆነ እስልምና ያስተምራል:: ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ማሸነፍ የግድ ይኖርበታል:: መሐመድ ከመዲና ወደ መካ በድል እንደ ተመለሱ ሁሉ፣ ሙስሊሞች ሁሉ ድል ማድረግ አለባቸው:: መሐመድና ተከታዮቻቸው የማታ ማታ በተቃወሙዋቸው የመካ ነዋሪዎች ላይ ድል እንደነሡ፣ በመጨረሻ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በጠላቶቹ ላይ ድልን ይጐናጸፋል::

[7] C. J. Lyall, *Translations of Ancient Arabian Poetry* (London: 1930), 5, in Kenneth Cragg, *Muhammed and the Christian* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 39.

በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ ጦርነትን የሚቃወሙና ችግሮችን በውይይት መፍታት ተገቢ እንደ ሆነ የሚያምኑ ሰዎች እንዳሉ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ንስሓ ለሚገቡና ከሙስሊሞች ጋር የሚደረገውን ጦርነት ለማቆም ለወሰኑ ሰዎች ምሕረት ማድረግ እንደሚገባ ቁርአን ያስተምራል። ይሁን እንጂ ዋና ዋና በሚባሉት የእስልምና ሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ፣ ከምሕረት ይልቅ ኀጢአትን የሠራ ወይም ደግሞ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ያጠቃ ሰው፣ ለሠራው ጥፋት ቢያንስ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊሰጠው እንደሚገባ በአጽንዖት ተገልጾአል[8]። የሚያሳዝነው ቅጣቱ ለሌላ በቀል እንደሚያነሣሣ ያለመገንዘቡ ነው።

በመካከለኛው ምሥራቅ በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል በሚደረገው የሰላም ድርድር የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት (ፒ. ኤል. ኦ) በሰላም ውይይቱ ውስጥ መሳተፉ አስደናቂ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም ፒ. ኤል. ኦ እስላማዊ ድርጅት ሳይሆን የተለያየ እምነትና አመለካከት ያላቸው ሰዎችን ያቀፈ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። በውስጡ የዐረብ ክርስቲያኖች መኖራቸው እስላማዊ ድርጅት እንዳይሆን አድርጉታል። እንደ ሐማስ ያሉ እስላማዊ ድርጅቶች ግን ጠላታችን ከሚሉት ከእስራኤል መንግሥትና ክርስቲያኖችን ካቀፈው ከፒ. ኤል. ኦ ጋር ለሰላም ድርድር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ መቀመጥን በጭራሽ አይፈልጉም።

እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ2002 ዓ.ም በአንድ ክርስቲያናዊ ኮሌጅ የተሰባሰቡ ተማሪዎች ለአንድ ሴሚስተር በእስራኤልና በዌስት ባንክ በመቆየት። ስለ እስራኤልና ፍልስጥኤም ሰላም ሦስት ስብሰባዎችን አድርገዋል። የመጀመሪያውን ስብሰባ ያደረጉት ከሐማስ መሪ ጋር ነው። የሐማሱ መሪ የጅሐድ ጦርነት በእስልምና ነገረ መለኮት ውስጥ ያለውን እንድምታ አብራርቶላቸዋል። በመቀጠልም አሁን ባለው ሁኔታ ከእስራኤል ጋር የጅሐድ ጦርነት ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደ ሆነ ተናግሮአል።

ሁለተኛ ስብሰባ ያደረጉት ከእስራኤል ሰፋሪዎች ጋር ነው። የሰፋሪዎቹ መሪ ለተማሪዎቹ፣ "እስራኤላውያን የሰፈሩት ድሮ የራሳችን በነበረው መሬት ላይ ነው። ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል ሰፋሪዎች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት

---

[8] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 39-42.



መከላከል ያለብን መልሶ በማጥቃት እንጂ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም" ሲል የሰፋሪዎቹን አቋም ገልጾአል።

የተማሪዎቹ ቡድን በሦስተኛነት ያነጋገረው በቤቶቻቸው ፍርስራሽ ላይ ተቀምጠው የነበሩትን የፍልስጥኤም ክርስቲያን ቤተሰቦችን ነው። ይህ ቤተሰብ እስራኤል አካባቢውን ባጠቃችበት ወቅት አለን የሚሉት ንብረት ሁሉ ወድሞባቸዋል። እነዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ ሆነው፣ የኢየሱስን ሕይወት በናሙናነት በመጥቀስ፣ እርሱ ጠላቶቹን ይቅር ብሎአል፤ እኛም ቤታችንን ባፈረሱ ሰዎች ላይ ቂም አንይዝም። የክርስቶስን ፍቅር ለዐመፅ ለሚነሣሡ ሰዎች ሁሉ ለመንገር ተዘጋጅተናል ብለዋል።

ምንም እንኳ የሙስሊም ነገረ መለኮት የመስቀሉን ሥራ ቢክድም የመሲሑ ጕዞ ወደ መስቀል ነበር። በዚህም መስቀሉ እንቈቅልሽ መሆኑ ቀጥሎአል። በፊላደልፊያ በሚገኝ መስጊድ ውስጥ በአንድ ምሽት በነበረን ውይይት፣ በቴምፕል ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪዋን የምትሠራ አንዲት ወጣት እንዲህ ስትል ጥያቄ ጠየቀችን፦— "በሶማሊያ ውስጥ ያለው የእርስ በርስ ግጭት ለምን አይቆምም? ሶማሊያ ሙስሊም አገር ሆና ሳለ እንደ ዳግም መጥምቃውያን (ሜኖናይት) ያሉ ክርስቲያኖች በዚህች አገር ሰላም በማምጣቱ ሂደት ውስጥ ብዙ የሚደክሙት በምን ምክንያት ነው?" ወጣቷ ጥያቄውን የጠየቀችን እኔ ሶማሊያ ውስጥ መቆየቴን ስለምታውቅ ነው።

እኔም፣ "ለእርስ በርስ ግጭቱ መቀጠል የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች በሰላም ሂደቱ ውስጥ የሚሟገቱት ሚና መሲሑ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰቀሉትን ጠላቶቹን ይቅር እንዳለ እኛም ይቅር ማለት አለብን በሚለው እምነት ላይ የተመሠረተ ነው። በጣም የሚያሳዝነው ነገር ላለፉት በርካታ ምዕተ ዓመታት የሶማሊያ ሕዝብ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደ ሞተና ጠላቶቹን ይቅር እንዳለ የሚሰብኩትን ክርስቲያኖች በሶማሊያ ኅብረተሰብ ውስጥ እንዳይኖሩ አግልሎአል። ክርስቶስ ለሰዎች የሰጠው የይቅርታ መንገድ ከዚህ ማኅበረሰብ ዐይን ተሰውሯል" አልኳት።

በዚያ ምሽት ከመስጊድ ውስጥ የሰማሁት ምላሽ፣ "ዋ! ብትጠነቀቁ ይሻላል። መሲሑ ኢየሱስ አልተሰቀለም" የሚል ነበር።

"በዚህ ምሽት በድጋሚ የክህደትን ንግግር እየሰማን ነው" አልሁ። በመቀጠልም "ሕዝብንም ሆነ እኛን በግላችን ሊፈውስ የሚችል ይቅርታ የሚያደርግ ፍቅር

በክርስቶስ መስቀል ተገልጦአል። እኛ ይህንን ፍቅር ስንቃወም እውነተኛ የሆነውን ዕርቅና ፈውስ እየተቃወምን እንደ ሆነ ልብ ልናደርግ ይገባል"።

በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ስለገለጠው አስደናቂ የማስታረቅ አገልግሎት ከተናገርሁ በኋላ አንዲት ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁር እንዲህ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡ፡— "እስከ ዛሬ ድረስ እኔ ቤተ ክርስቲያን የማስታረቅን አገልግሎት ስትፈጽም አላየሁም። ኢየሱስ ጠላቶቹን ከመበቀል ይልቅ ከጠላቶቹ ፊት መሸሽን መረጠ የሚለውን አነጋገርህን ስሰማ የመጀመሪያዬ ነው። እኛ ሙስሊሞች ቤተ ክርስቲያንን የምናውቃት ሁኔታዎች ፈታኝ ሲሆኑባት ወደ በቀልና ጦርነት እንደምትዞር ነው"።

እኔም በተራዬ፣ "በወንጌል ውስጥ የተገለጸውን ኢየሱስን ሳይሆን፣ በቀለኛውን ኢየሱስን የምትሰብክ ቤተ ክርስቲያን ካለች እግዚአብሔር ይቅር ይበላት። እናንተም ብትሆኑ በእግዚአብሔር ጸጋ እኛን ይቅር ማለት አለባችሁ። የእርስዎ አስተያየት እኛ ክርስቲያኖች የተቀበልነውን እምነት ያጐደፉትን ክርስቲያኖች ለንስሓ የሚጠራ ነው" ስል አስተያየቴን ሰጠሁ።

በመጨረሻም ወይዘሮዋ እኔን ካመሰገኑ በኋላ፣ በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆነው፣ "ስለቤተ ክርስቲያን ኀጢአት አንድ ክርስቲያን ከሙስሊሙ ይቅርታን ሲጠይቅ የሰማሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። በአንተ ንስሓ ውስጥ እኔ ከዚህ ቀደም ያላወቅሁትን የመሲሑን መልክ አይቻለሁ" አሉኝ።

## እውነተኛው ኀይል

መስቀል ኀይላችን ነው። ከላይ የተመለከትናቸው ውይይቶች የሚያሳዩን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነን የሚሉ ክርስቲያኖች ስለኀይል ያላቸው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆን ይልቅ እስላማዊ መሆኑን ነው። ከተለያዩ ጓደኞቼ ጋር በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ ያደረግናቸው ውይይቶች እውነተኛ ኀይል እንዴት ይገኛል የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ከሶማሊያ የመጡ ሦስት ሙስሊም ጓደኞቼ ለተወሰኑ ቀናት እቤታችን ዐርፈው ነበር። እሑድ ማለዳ ቁርስ እየበላን ሳለ፣ ከሁሉም በዕድሜ ገፋ ያለው ሰው፣ "በሶማሊያ የሰላም ሂደት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀኝ። በመቀጠልም፣ "አገራችን እየፈራረሰች ነው። የእናንተ የሜኖናይት



ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሰላም ሂደቱ በእግሩ እንዲቆም በርካታ ድጋፍ አድርጋችኋል ለዚህ ያነሣሣችሁ ምክንያት ምንድን ነው?"።

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት፡— "የእኛ ሰላምን የማምጣት አገልግሎት የክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ነፀብራቅ ነው። ኢየሱስ ታልፎ ከመሰጠቱና ከመከራው በፊት አሳልፎ የሚሰጠውን የአስቆሮቱ ይሁዳን እግር አጠበ። በዚህም አገልግሎቱ ክፉ ሊያደርግበት ለተዘጋጀው ሰው ርኅራኄ እንዲሁም እርሱን ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን አሳየ"።

"በተጨማሪም በመስቀል ላይ ተሰቅሉ ሳለ፣ ለሰቀሉት ሰዎች ይቅርታ አደረገላቸው። እንዲህ ዐይነት ፍቅር ደካማነት አይደለም። መሥዋዕት የሚያስከፍለው የእግዚአብሔር ፍቅር ከጠላቶቹ ጋር ዕርቅንና ይቅርታን የሚመሠርት ፍቅር ነው አልኋቸው"።

ይህንን እየተናገርሁ ሳለ ሙስሊማኑ ባልንጀሮቼ፣ "ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር መሲሑን በኀይል ቀብቶታል። ኀያሉ መሲሕ ደግሞ መከራ ሊቀበል አይገባውም። ደግሞም እግዚአብሔር ሰዎችን ይህን ያህል በፍጹም ሊወድ አይችልም" አሉ። እኔም፣ "ወንድሞቼ እባካችሁ፣ የእግዚአብሔርን ማንነቱን እኛ ልንወስንለት ሙከራ አናድርግ" ስል ምክሬን አጋራኋቸው።

በዚህ ውይይታችን ምክንያት በዚያ ማለዳ የነበረውን የመጀመሪያውን የእሑድ የአምልኮ ፕሮግራም ሳንካፈል ቀረን። ምክንያቱም በቤታችን ውስጥ ይደረግ የነበረው ውይይት ዐቢይ ጠቀሜታ ስለነበረው ነው።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ዮሐንስ 6፥1-15፤ ማቴዎስ 16፥21

*የቁርኣን ምንባብ*

ሱራ 9፥30፤ 58፥20-22

<u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. መሐመድና ኢየሱስ በተቃራኒ የሕይወት ጉዞዎች ውስጥ አልፈዋል ለሚለው ዐረፍተ ነገር ያልዎትን አስተያየት ይስጡ።

2. ኢየሱስ የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይልን መጠቀም አልፈለገም፤ ነገር ግን መሐመድ የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይልን መጠቀምን ወደደ (ዮሐንስ 18፥36፤ ሱራ 2፥190-193) የሚሉትን ዐረፍተ ነገሮች ያብራሩ::
3. የመሐመድ የሕይወት ጉዞ ሙስሊሞች ለጠላቶቻቸው ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽእኖ የሚያደርገው እንዴት ነው? ክርስቶስ ወደ መስቀል ያደረገው ጉዞ ክርስቲያኖች ለጠላቶቻቸው ያላቸውን አመለካከት ሊቀርጽ የሚችለው እንዴት ነው?
4. ሒጅራ በእስልምና አዲስ ምዕራፍ የተጀመረበት ነው:: ይህ ክሥተት ሙስሊሞች ስለራሳቸው ባላቸው አመለካከት እንዲሁም በእስልምና ነገረ መለኮት ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣበትን ምክንያት ይግለጹ::
5. በእግዚአብሔር ወይም በእግዚአብሔር ኀይል የተቀባ ሰው መከራ ይገጥመዋልን? በሒጅራ ጊዜ የተፈጠረው ሁኔታ ስለዚህ ጥያቄ ምን ምላሽ ይሰጣል? ለዚህ ጥያቄ ምን የእርስዎ መልስ ምንድን ነው? (ሱራ 8፥30፤ ሉቃስ 23፥34)::
6. ለራስዎትም ሆነ ለሌሎች ጥሩ ነው ብለው የሚያምኑትን ነገር የሚወስኑት እንዴት ነው? ይህን ለመፈጸም የሒጅራን ጉዞ ወይስ የመስቀሉን ጉዞ ይመርጣሉ?
7. ስለመስቀልና ስለ ሒጅራ ያለው ነገረ መለኮት ስለፍትሓዊ ጦርነት ምን ምላሽ ይሰጣል?



## ምዕራፍ ዘጠኝ

# ቅድስቲቱ ከተማ መዲና—ኢየሩሳሌም

መዲና በዐረብያ ምድር የእስልምና ኡማ የተጀመረባት ከተማ ናት:: በፍልስጥኤም—እስራኤል ውስጥ የምትገኘው ኢየሩሳሌም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተቈረቈረባት ከተማ ናች:: በእነዚህ ሁለት የታሪክ ወቅቶች ቤተ ክርስቲያንና የሙስሊሙ ኡማ አብረው ነበሩ:: በዚህ ምዕራፍ የሙስሊሙ ኡማ በመዲና የመፈጠሩን ሁኔታና ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የመጀመሯን ጕዳይ እንመለከታለን::

## ቤተ ክርስቲያን—የሙስሊሙ ኡማ

የሙስሊማኑና የክርስቲያኑ እንቅስቃሴዎች ከእመሁ አልቦ የተጀመሩ (ከባዶ ነገር ውስጥ የበቀሉ) አይደሉም:: ከቤተ ክርስቲያንና ከሙስሊም ኡማ ብዙ መቶ ዓመታት አስቀድሞ፣ እግዚአብሔር እስራኤል ለሕዝብ ሁሉ ብርሃን እንድትሆን እንደ መረጣት ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ያምናሉ:: እግዚአብሔር እስራኤል የቃል ኪዳን ሕዝብና በአሕዛብ መካከል ምስክር እንድትሆን መረጣት:: ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሙስሊሙ ኡማ ከጅማሬያቸው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው ጥሪ ፍጻሜና የእስራኤልን ተልእኮ የማስፋፋት ሥራ እንደሚሠሩ ያምኑ ነበር:: (ምዕራፍ አራትን ይመልከቱ)::

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ቤተ ክርስቲያን እንደ ተመሠረተች ነበር:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አማኞች ኢየሱስ መሲሕ፣ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ ይመሰክሩ ነበር:: ከአይሁድ ወገን ያልሆኑት አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀሉ ነበር:: ይህም ቤተ ክርስቲያን የተለያየ ዐይነት ሕዝብ ያለባት የኅብረተሰብ ክፍል እንድትሆን አስቻላት:: ይህ ጕዳይ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ "አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ" ያለው የተስፋ ቃል ፍጻሜ እንደ ሆነ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች::

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ:—

> ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ (ሐዋርያት ሥራ 1፥8)።

ቁርአን የተጻፈው የመጀመሪያው የሙስሊም ኡማ ሲቋቋም ነበር። ሙስሊሞች የሙስሊሙ ኡማ ከእስራኤልና ከቤተ ክርስቲያን የሚልቅ እንዲሁም ዓለም ዐቀፋዊ እንደ ሆነ ያምናሉ። የእስራኤል አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ፣ የሙስሊሙ ኡማ ግን ይህንን አገልግሎት ወደ ዓለም ሁሉ የሚያደርስ እንደ ሆነ ይታመናል። ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ አስተምህሮአዊ ጥያቄዎች ስለተከፋፈለች የሙስሊሙ ኡማ ተልእኮ ለእነዚህ ጥያቄዎች መፍትሔን መስጠት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ።

ቁርአን በሱራ 14፥1 ላይ፣ "አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርአን)፤ ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አሸናፊ ምስጉን ወደ ኾነው ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው" ይላል።

ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሙስሊሙ ኡማ አብርሃም የእምነት አባታቸው እንደ ሆነ ያስተምራሉ። እነዚህ የእምነት ክፍሎች እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ "አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ" ካለው ቃል ጋር አብሮ የሚሄድ ተልእኮ እንዳላቸው ያምናሉ። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ዓለሙ ሁሉ ታስፋፊያለሽ ሲል የሰጣትን የተስፋ ቃል ፍጻሜ ላይ ማድረስ ነው። የሙስሊም ኡማ ደግሞ ከእስራኤልና ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሻለ አገልግሎት እንዳለው ያምናል። ስለዚህ በእነዚህ ሁለት የእምነት ቡድኖች መካከል ለዘመናት የቆየ ውጥረት መኖሩ አያስደንቅም።

ይህ ምዕራፍ በኢየሩሳሌም፣ ስለ ተካሄደው የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ እንዲሁም በመዲና ደግሞ የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ማብራሪያ ይሰጣል። የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ከሙስሊም ኡማ ስለሚቀድም፣ በቀዳሚነት ስለቤተ ክርስቲያን አጀማመር ከተመለከትን በኋላ፣ ስለኡማ ደግሞ በቀጣይነት እንመለከታለን።

## ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተመሠረተች

ኢየሱስ ከሦስት ዓመት አገልግሎቱ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም አቀና። በዚያን ጊዜ ከተማዋ በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ነበረች። ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ከሚገኘው የደብረ ዘይት ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የገባው በአማረ አጀብና እልልታ እንዲሁም በታላቅ ሆታና ፍሥሐ ነበር።



## ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ

ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፣ ዙሪያውን ከበውት የነበሩ ሰዎች፦

> ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፤
> በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤
> ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር (ማቴዎስ 21፥9)።

የአይሁድ ባለሥልጣናት በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ክፉኛ ተቈጡ። ኢየሱስ ውርንጫ በሆነች አህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱ፣ እነርሱ አጥብቀው የሚቃወሙትን ነገር ስለ ራሱ እያወጀ መሆኑን ተረድተዋል። ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ እንደሚመጣ ስለመሲሑ በነቢዩ በዘካሪያስ የተነገረ ትንቢት ነው። ይህ ድርጊት ከመከሠቱ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት፣ ነቢዩ ዘካርያስ ስለመሲሑ እንዲህ ሲል ጽፎአል፦

> አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በዪ፤ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፣ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል። ሠረገላውንም ከኤፍሬም ፈረሱንም ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ፤ የሰልፉንም ቀስት ይሰብራል፤ ለአሕዛብም ሰላምን ይናገራል፤ ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይሆናል (ዘካርያስ 9፥9-10)።

ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት፣ መሲሕ እንደ ሆነ እንዲሁም ለዓለም ሁሉ የሚሆን የሰላም መንግሥት ጅማሬ መሆኑን አብሥሮአል። ይሁንና የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ድርጊት ክፉኛ ተበሳጩ። ለዚህ ዐቢይ ምክንያት ኢየሱስ እነርሱ የጠበቁት ዐይነት ንጉሥና መሲሕ ስላልነበረ ነው።

እነርሱ የሚጠብቁት ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባው በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ፣ ጋሻና ጦር በታጠቁ በብዙ መቶ የሚቈጠሩ ሰዎች ታጅቦ ነው። ይህ ንጉሥ ጣዖት አምላኪ የሆነውን የሮማን መንግሥት ገልብጦ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በከተማዪቱ፣ ከተማዪቱ በምትገኝባቸው አካባቢዎች እንዲያውም በዓለም ሁሉ እንደሚመሠርት ይታመን ነበር።

በሕዝቡ ጩኸት ታጅቦ በውርንጫ አህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው ኢየሱስ፣ በከተማዪቱ ላይ ንጉሥ መሆን አልቻለም። ፈሪሳውያን የሚጮኹውን ሕዝብ ኢየሱስ እንዲገሥጻቸው ቢጠይቁትም ኢየሱስ ሕዝቡን

አልገሠጻም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው፣ "እነርሱ ዝም ቢሉ፣ ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው" (ሉቃስ 19፥40)፡፡

የእንግሊዝ የነገረ መለኮት ምሁር ኤን. ቲ. ራይት ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ መምጣቱ እርሱ ከምሥራቅ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባ የእግዚአብሔር ክብር እንደ ሆነ መግለጽ ነው ሲል ያስተምራል[1]፡፡ ይህ ዐይነት መረዳት በትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ ከሰፈረው ትንቢት ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል በአህያ ላይ ስለሚቀመጠው ንጉሥ ሲጽፍ የእግዚአብሔር ክብር ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከምሥራቅ በኩል እየመጣ እንደ ሆነ ጽፎአል፦

> እነሆም የእስራኤል አምላክ ክብር ከምሥራቅ መንገድ መጣ፤ ድምፁም እንደ ብዙ ውሆች ይተምም ነበር፤ ከክብሩም የተነሣ ምድር ታበራ ነበር... የእግዚአብሔርም ክብር ወደ ምሥራቅ በሚመለከት በር ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ...በመቅደሱም ሆኖ የሚነግረኝን ሰማሁ በአጠገቤም ሰው ቆሞ ነበር፡፡ እንዲህም አለኝ፦ የሰው ልጅ ሆይ በእስራኤል ልጆች መካከል ለዘላለም የምቀመጥበት የዙፋኔ ስፍራና የእግሬ ጫማ መረገጫ ይህ ነው፡፡ ዳግመኛም የእስራኤል ቤትና ነገሥታቶቻቸው በግልሙትናቸው በከፍታቸው ባለው በነገሥታቶቻቸው ሬሳ ቅዱስ ስሜን አያረክሱም (ሕዝቅኤል 43፥2፡4፡6-7)

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ላይ ተቀምጦ ሲገባ፣ የእርሱ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት የነቢዩ ዘካሪያስ ትንቢት ብቻ ሳይሆን የነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢትም ፍጻሜ እንደ ሆነ ማወጁ ነበር፡፡ መሲሑ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ላይ ተቀምጦ መግባቱ፣ በእርሱ ማንነት አማካይነት የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱንና ለዓለም ሁሉ የሚደርስ የጽድቅ፣ የፍትሕና የሰላም መንግሥት መጀመሩን ያመለክታል፡፡

## ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አነጻ

ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደ ተነበየው፣ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት የተገለጠበት ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ፡፡ ነገር ግን ቤተ መቅደሱ በነጋዴዎች ተጨናንቆ ነበር፡፡ ነጋዴዎቹም መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ሰዎች እንስሳትና ምግብ በመሸጥ ላይ ነበሩ፡፡ ኢየሱስ ይህን ባየ ጊዜ የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛዎች ገለበጠባቸው፤ ለሽያጭ የቀረቡትንም እንስሳት ከቤተ መቅደሱ አስወጣቸው፡፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለሕዝብ ሁሉ የጸሎት

[1] N. T. Wright, *The Challenge of Jesus: Redisscovering Who Jesus Was and Is* (Downers Grove, Ill.: InterVarsitv. 1999), 123.



ቤት ይሆናል እንጂ፣ የዘራፊዎች ዋሻ አይሆንም አለ (ማቴዎስ 21፥13)፡፡ የቤተ መቅደሱ ባለሥልጣናት ኢየሱስን በምን ሥልጣን ነው ይህን ሁሉ የምታደርገው ሲሉ ጠየቁት፡፡ ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ" ብሎ መለሰላቸው (ዮሐንስ 2፥19)፡፡

ኢየሱስ ይህን የተናገረው ከሞተ ከሦስት ቀን በኋላ ከመቃብር እንደሚነሣ ማመልከቱ ነበር፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ክሥተት ሌላ ተጨማሪም መልእክት የያዘ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህን ሲል በድንጋይ የተሠራው ቤተ መቅደስ ከዚህ በኋላ አስፈላጊ አይደለም ማለቱ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ክብርና የመለኮት ሁሉ ሙላት በመሲሑ በኢየሱስ በኩል ተገልጦአልና ነው[2]፡፡ የቤተ መቅደስ ባለሥልጣናት ኢየሱስ በድፍረት እኔ በአካል ስለመጣሁ በድንጋይና በእንጨት የተሠራው ቤተ መቅደስ አያስፈልግም ማለቱ እንደ ሆነ ተረድተዋል፡፡

ኢየሱስ የተናገረው የቤተ መቅደሱን አላስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን፣ የኢየሩሳሌምን መፍረስም ጭምር ነው፡፡ ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፣ ስለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ፡፡ ምክንያቱም ኢየሩሳሌም የታነጸችው የሰላም ከተማ እንድትሆን ቢሆንም፣ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ለሰላሟ የሚሆናትን ንጉሥ ባለ መቀበልዋ እንዲሁም ወደ ፊት በእርስዋ ላይ ስለሚደርሰው ከፍተኛ መከራና ጥፋት ከሩቅ ተመልክቶ አለቀሰ፡፡ እውነታው አሐዱ ተብሎ በኢየሱስ የተጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ቤተ መቅደስም ሆነ ኢየሩሳሌም አያስፈልገውም፡፡

## ኢየሱስ ተሰቀለ

የቤተ መቅደስ መሪዎች ቍጣ በፍጹም በቀላሉ ሊበርድ አልቻለም፡፡ ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንደ ተመለከትነው፣ ኢየሱስን ይዘው አሰሩት፤ ከዚያም በኋላ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት ፈረዱበት፡፡ ቅጣቱን ለማክበድ በኢየሱስ ላይ የተለያዩ ዐይነት ክሶችን አቀረቡ፤ በዋነኛ የቅጣት ማክበጃነት የቀረበው ነጥብ ስለቤተ መቅደስ የተናገረው ንግግር ነበር፡፡ ሌላኛው ክስ ደግሞ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለው አነጋገሩ ነው፡፡
ከዚህ በፊት በነበረው ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል፣ ደቀ መዛሙርቱ ከፍተኛ ሐዘንና ፍርሐት ስለወደቀባቸው በተለያየ አቅጣጫ ተበታተኑ፡፡ ሆኖም ከሦስት ቀን በኋላ፣ ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ወደ መቃብሩ የሄዱ ሴቶች መቃብሩ ባዶ እንደ ሆነ አዩ፡፡ ይህም ኢየሱስ ከሞት የመነሣቱ እውነታ ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ድርጊት እጅግ

[2] ዝኒ ከማሁ፤ 110፡፡

በጣም ተገረሙ:: ከዚያ በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ውስጥ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከዐሥራ አንድ ጊዜ በላይ ታይቶአቸዋል::

## ኢየሱስ ትእዛዝ ሰጠ

ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ የታያቸው የተቸነከሩትን እጆቹን እግሮቹንና ጐኑን እያሳየ ነበር:: ከዚያም በኋላ ባርኮአቸው:: "ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ" አላቸው:: (ዮሐንስ 20÷21)::

ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው:: ከዚያ በኋላ መቶ ሃያ የሚሆኑ ደቀ መዛሙርት ለዐሥር ቀን በጾምና በጸሎት ሆነው የመንፈስ ቅዱስን ምጽአት ይጠብቁ ነበር:: በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ላይ እያሉ፣ በበዓለ ኀምሳ (በጴንጤቈስጤ) ቀን መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ላይ ወረደባቸው::

## ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች

በአይሁድ ሥርዐት የጴንጤቈስጤ በዓል የአዝመራውን የበኵር ምርት በሚሰበስቡበት ጊዜ የሚከበር በዓል ነው:: በዚያች ቀን በኢየሩሳሌም ይህ በዓል ልዩ ትርጒም ነበረው:: ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነችው የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ቀን ነው:: መንፈስ ቅዱስ እንደሚነጥቅ ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ወረደ:: በእያንዳንዱም ላይ የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች ዐረፉባቸው:: በተለያዩ ልሳናትም እግዚአብሔርን አመሰገኑ::

በዚያ ቀን ከመካከለኛው ምሥራቅና ከሰሜን አፍሪካ የመጡ በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች እየሆነ ያለውን ነገር ለማየት ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቦታ ተሰበሰቡ:: የወንጌልን እውነትና ቤተ ክርስቲያን በተአምራዊ መንገድ መቈርቈሯን እንዲሁም ወንጌልን በራሳቸው ቋንቋ በመስማታቸው እጅግ በጣም ተገረሙ::
ጴጥሮስም በጉባኤው መካከል ቆሞ የመጀመሪያውን ስብከተ ወንጌል ለተሰበሰቡት ሰዎች አበሠረ:: የወንጌልን እውነት በተመለከተ ጴጥሮስ የሰበከው ስብከት በሐዋርያት ሥራ 2÷22-24:36 ላይ ይገኛል:—

> የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና



> በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ:: እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው ዕውቀቱ ተሰጥቶ በዐመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት:: እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና...እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ::

ይህን በሰሙ ጊዜ በዚያ የነበሩ ሰዎች "እንግዲህ ምን እናድርግ?" አሉ:: ጴጥሮስም "ንስሐ ግቡ:— ኀጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ፤ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (ሐዋርያት ሥራ 2÷37-38) አላቸው:: በሺህ የሚቈጠሩት እነዚህ ሰዎች የወንጌልን መልእክት በሰሙ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኀጢአትና ስለ እውነት ወቀሳቸው:: ሦስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ስለ ኀጢአታቸው ንስሐ ገቡ፤ መሲሑ ኢየሱስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነም አመኑ:: ሐዋርያትም ያመኑትን ሁሉ አጠመቁ:: ያመኑትም በታላቅ ደስታና ፍሥሐ ተሞሉ:: ሁሉም፣ ያላቸውን ነገር ሁሉ ለሌለው ያካፍሉ ነበር እንጂ፣ በመካከላቸው ድኻ አልነበረም:: "በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸው እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው:: ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (ሐዋርያት ሥራ 2÷46-47)::

## ቤተ ክርስቲያን ተሰደደች

በሐዋርያት እጅ ተአምራቶች ቢፈጸሙና ብዙ ሰዎች ቢያምኑም እንኳ ወዲያውኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስደት ተነሣ:: ክርስቶስ መከራን እንደ ተቀበለው ሁሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ተሰደደች:: ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተች በሳምንታቶች በሚቈጠር ጊዜ ውስጥ ንጉሥ ሔሮድስ ሐዋርያው ያዕቆብ ዐንገቱ ተቀልቶ እንዲሞት አስደረገ:: ቀጥሎም ዲያቆን የነበረው እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሞተ:: ሐዋርያው ዮሐንስና ጴጥሮስ ተይዘው ከተደበደቡ በኋላ፣ ወኅኒ ተወረወሩ:: ይህ ሁሉ የሆነው ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ማደግ በጀመረችበት ጊዜ ነው:: በማደግ ላይ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ወይም የጦር ኀይል አልነበራትም፤ ይልቁንም በባለሥልጣናት ክፉኛ ትሰደድ ነበር::

በኢየሩሳሌም የተቀሰቀሰው ስደት ክርስቲያኖች ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንዲበተኑ አደረጋቸው:: አማኞች ወደ ተለያዩ ቦታዎች ቢበተኑም በተበተኑባቸው ስፍራዎች ሁሉ የምሥራቹን ወንጌል ይዘው ሄዱ:: አማኞች

በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ አዳዲስ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት ተቋረቋሩ:: ቤተ ክርስቲያን ይህ ሁሉ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ እንደ ሆነ ከሙሉ ልብ ትቀበላለች::

## ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናት

የቤተ ክርስቲያን ማዕከል ኢየሩሳሌም ነው የሚለው አስተሳሰብ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ መጣ:: ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች ከአንድ ትውልድ በኋላ ማለትም በሰባ ዓመተ ምሕረት የሮም ባለ ሥልጣናት በኢየሩሳሌም የነበረውን ቤተ መቅደስ አፈረሱ:: ኢየሩሳሌምም በሮም ቍጥጥር ሥር ወደቀች፤ ሌሎች ከተሞችም ፈራረሱ:: በመሠረቱ ኢየሩሳሌምም ሆነች ቤተ መቅደሱ፣ የክርስትና ማዕከል አልነበሩም:: ማንኛውም ክርስቲያኖች በመሲሑ በክርስቶስ ስም የሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ የክርስትና ማዕከል ነው:: ክርስቲያኖችም በታላቅ መደነቅና በከፍተኛ ሐሴት፣ "እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና ይላሉ" (2ቆሮንቶስ 6+16)::

## ቤተ ክርስቲያን ተበተነች ተስፋፋችም

ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ቢበተኑም፣ መከራን ግን ማምለጥ አልቻሉም:: በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕተ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን አንዳችም ዐቅም ስላልነበራት በእጅጉ ትሰደድ ነበር:: ይሁንና ቤተ ክርስቲያን ከተጀመረች በኋላ ባሉት ሁለት መቶ ዓመታት ውስጥ፣ በግብፅ ይኖር የነበረው አርጌንስ (Origen) እንዲህ ሲል ጽፎአል:— "ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመምጣቱ ምክንያት የእንግሊዝ ሕዝብ በአንድ አምላክ አምኖአል:: በአፍሪካ የሚገኙት የሙር ሕዝቦችም የወንጌልን እውነት ተቀብለዋል:: ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ ደርሶአል:: ቤተ ክርስቲያናት አሁን በዓለም ዋና ዋና በሚባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተተክለዋል፤ ምድር ሁሉ በደስታ እልል ትበል"[3]::
ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ኀይል ባይኖራትም፣ ትንሽ እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው፣ ወንጌል የባለሥልጣናት ቤት እንኳ ሳይቀር ገባ:: ለምሳሌ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ፣ ወንጌል በቄሳር ቤተሰቦች ዘንድ እንኳ እንደ ተሰበከና እንደ ታመነ ጽፎአል:: ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ተቃውሞ ይጽፍ የነበረውና አረማዊ የሆነን እምነት ይከተል የነበረው ሴልሱስ፣ ስለዚህ ነገርም ጽፎአል:: ሴልሱስ

[3] John Foster, *Church Histrovy: the First Advance, A.D. 29-500* (London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1972), 35.



በወቅቱ እየሆነ በነበረው ነገር እጅግ ተስፋ ቈርጦ ነበር፤ ምክንያቱም ወንጌል የባለ ሥልጣኖችን ሰፈር ሁሉ እያዳረሰ ስለነበረ ነው:: ሴልሱስ የክርስቲያኖቹን እንቅስቃሴ ሊገታ ባለመቻሉም መራር የሆነ ሐዘን ነበረነት:: ክርስቲያን የሆኑ የቤት አገልጋዮች/ሠራተኞች እንኳ የጌቶቻቸውን ልጆች በሚያሳድጉበት ጊዜ ለልጆቹ ስለ ወንጌል ይናገሩ ነበር:: ልጆቹም ለወላጆቻቸው ወንጌልን ይናገሩ ስለነበር ብዙም ሳይቆይ ባልተማሩና የገጠር ሰዎች በሆኑ የቤት ሠራተኞች አማካይነት፣ የብዙ ቤተ ሰብ አባላት ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ[4]::

ክርስቲያኖች የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ፣ "አዲስ ትውልድ"[5] አድርገው ይቈጥሩታል :—

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ:: እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ:: እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም፤ አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል (1ጴጥሮስ 2+9-10)::

አማኞች እግዚአብሔር ከዓለም ሕዝቦች፣ ከተለያዩ ቋንቋዎችና ጐሣዎች መካከል የጠራቸው የተለዩ እንዲሁም አዲስ ማኅበረሰቦች እንደ ሆኑ የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች:: ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት ሲጸልይ እንዲህ ብሎአል :— "እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም. . .ወደ ዓለም እንደላከኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላከኋቸው" (ዮሐንስ 17+16:18)::

ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ከዚያም ወደ ሌሎች ቦታዎች እንድትስፋፋ ጠንካራ አስተዳደርና ጥሩ አደረጃጀት መዘርጋቱ የግድ ነር:: ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ፣ ቤተ ክርስቲያን በጅማሬዋ ወቅት እንኳ ጠንካራ የሆነ አስተዳደራዊ መዋቅር ትጠቀም ነበር:: ከክርስቶስ ጋር አብረው የነበሩት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ:: ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የነበረው ይሁዳ፣ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ራሱን ስለገደለ፣ ሐዋርያት በእርሱ ፋንታ ማቲያስን መረጡ:: ቤተ ክርስቲያን በተተከለችባቸው አካባቢዎች ሁሉ፣ ጉባኤውን ሊመሩ የሚችሉ በሳልና መንፈሳዊ መሪዎች

[4] William G. Yong, *Handbook of Source Materials for Students of Church History up to 650 A.D* (Madras: The Diocesan Press, 1969), section 63.
[5] Foster, *Churah Histroy*, 35

በሕዝቡ ይመረጡ ነበር:: የድኾችን የገንዘብና የቍሳቍስ ችግሮች የሚፈ[...] ዲያቆናትም በተመሳሳይ መንገድ በሕዝቡ ተመረጡ::

ስለዚህ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በጥምረት የሚሠሩ ሦስት ክፍሎች ነበሩ፡ እነሱም ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎችና ሐዋርያት ናቸው:: በተለያዩ ዘመናት ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የአስተዳደር ዘዴዎችን ተጠቅማለች:: ነገር ግን የተለያዩ ዘዴዎች ቢኖሩም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተጠቀመችባቸው የአስተዳደር አካሄዶች እስከ ዛሬ ድረስ በሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ይሠራሉ:: የመሪነት ዘርፎች ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎች (መጋቢዎች ወይም ካህናት) እና እረኞች (ጳጳሳት) ናቸው:: መሪዎች ደግሞ የሕዝቡ አገልጋዮች እንጂ ገዥዎች አይደሉም (ዮሐንስ 13÷2-17)::

## የለውጥ ሐዋርያ የሆነች ቤተ ክርስቲያንና አዲስ የበቀለው ኡማ

በአራተኛው ክፍለ ዘመን የሮም መሪ የነበረው ቈስጠንጢኖስ፣ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የነበረውን ግንኙነት አዲስ አቅጣጫ እንዲይዝ አድርጉታል:: ቈንስጠንጢኖስ ቤተ ክርስቲያንን የሮማን ግዛት ወደ አንድነት ለማምጣትና ለማስፋፋት ተጠቅሞባታል:: ይህም የምዕራብ አገሮችን ጨምሮ የቤተ ክርስቲያንን የአስተዳደር ዘዴ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ሚና መሠረታዊ በሆነ ሁኔታ ለውጦታል:: ጳጳሳት በኅብረተሰብ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ ሰዎች ሆኑ፤ የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር አካሄድ የሮም መንግሥትን የአስተዳደር ዘይቤ መከተል ጀመረ:: ይህ የሆነበት ምክንያት ከቈንስጠንጢኖስ ዘመን ጀምሮ የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥትን ሥልጣን ተጠቃሚ በመሆንዋ ነው:: ይሁንና በአሁኑ ዘመን ያለው ዓለማዊ የሆነው ባህል በምዕራቡ መንግሥታት ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ ያላትን ሚና እየሸረሸረው ይገኛል::

በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው፣ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊም ኡማ ሲጀመር በቈንስጠንጢኖስ ዘመን በጠንካራ መሠረት ላይ የታነጸው የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ኅብረት በጥሩ ሁኔታ ላይ ነበር:: የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያንና አንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች፣ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መዋሐድ አለባቸው ብለው ያምኑ ነበር:: ነገር ግን በፐርሺያ፣ በሕንድና በዐረብያ የነበሩት ቤተ ክርስቲያናት ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ጕልሕ የሆነ የበላይነት አልነበራቸውም::



በመዲና የነበሩ ሙስሊሞች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ አንድ ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴና ፖለቲካዊ አስተዳደር የሶሪያና የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ከተከተሉት የአስተዳደር አካሄድ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው:: የሙስሊሙን ኡማ አደረጃጀት የሚነቅፉ ክርስቲያኖች፣ የሙስሊም ኡማ ከመጀመሩ ከብዙ ዓመታት በፊት፣ የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን የኡማ አደረጃጀትን ዐይነት መርሕ መከተልዋን ሊያስተውሉ ይገባቸዋል:: ቀጥለን በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊሙ ኡማ በመዲና እንዴት እንደ ተጀመረና እንደሰፋ እንመልከት::

## ኡማ በመዲና ተጀመረ

መሐመድ የዘጠኝ ቀን ጕዞ አድርገው ከመካ ወደ መዲና ሲገቡ፣ በመዲና ታላቅ ፈንጠዝያ ነበር:: በምዕራፍ እንደ ተገለጸው ይህ ጕዞ ለእስልምና አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት የሒጅራ ጕዞ ተብሎ ይጠራል::

### ሙስሊሞች ኡማን መሠረቱ

መዲና ከሚገኙ ሙስሊሞች በተጨማሪ፣ በመቶዎች የሚቈጠሩ ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱ ሙስሊሞች በመካ ይኖሩ ነበር:: እነዚህም ሙሐጂሩን ተብለው ይጠራሉ:: የመዲና ሙስሊሞች ደግሞ አንሳር በመባል ይጠራሉ:: መሐመድ እነዚህ ሁለቱ ክፍሎች ተዋሕደው የሙስሊሙን ኡማ እንዲፈጥሩ ሥልጣን ሰጧቸው:: በመዲና የነበሩት ሙስሊሞች ከመካ የመጡትን ስደተኞች ለማቋቋም ያላቸውን ሁሉ አካፍለዋል::

የሙስሊሙ ኡማ ከተቋቋመ በኋላ፣ መሐመድ በመዲና መስጊድ ለመሥራት ዕቅድ አወጡ:: ይህ መስጊድ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ የመጀመሪያው መስጊድ መሆኑ ነው:: በዚህ መስጊድ ውስጥ የተጀመረው አምልኮና የአምልኮ ሥርዐት በዓለም ሁሉና በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ሙስሊሞች እንደ አብነት የሚጠቀስ ነው::
በመስጊዱ ውስጥ ሚህራብ የሚባል ቦታ አለ:: ይህም ሙስሊሞች በጸሎት ሰዓት ወዴት አቅጣጫ መስገድ እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው:: በእስልምና የመጀመሪያዎቹ ዘመናት፣ ሙስሊሞች ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም አድርገው ይሰግዱ ነበር:: ወደ ኢየሩሳሌም መስገዳቸው ለአይሁድ ሕዝብና ነቢያት ክብሬታ ለመስጠት እንዲሁም እስልምና ከአይሁድ እምነት የቀጠለ መሆኑን ለማሳየት ሳይሆን አይቀርም:: እስልምና ከአይሁድ እምነት የቀጠለ ነው የሚለው አስተሳሰብ፣ በመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ዘንድ ዐቢይና ጕልሕ ቦታ ነበረው:: ነገር ግን በመዲና ይኖሩ የነበሩት ሙስሊሞች የጸሎት አቅጣጫውን ከኢየሩሳሌም፣ መካ ወደሚገኘው ካዕባ ቀየሩት::

በመዲና ለአሳህ የሚቀርበው አምልኮ ወደ መካ የሄዱትን ስደተኞች እንዲሁም የመዲናን ድኾች በአንድ ያጣመረ ነበር:: ይሁንና መፍትሔ የሚሹ ፖለቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮች ነበሩ:: ስለዚህ መሐመድ የአምልኮ ስፍራና የአምልኮ ሥርዐቱን ከመሠረቱ በኋላ፣ ሙስሊማዊ ለሆነ ፖለቲካዊ ሥርዐት መሠረት ጣሉ:: ለመዲና ነዋሪዎችም የመተዳደሪያ ደንቦችን አዘጋጁ::

## ሙስሊሞች መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጁ

ሙስሊሞች ያዘጋጁት መተዳደሪያ ደንብ ስለ ወንድማማችነት፣ ስለ ፍትሕ እንዲሁም በአንድ ጉዳይ ላይ ስለመስማማት መመሪያን የሚሰጥ ነበር:: የመተዳደሪያ ደንቡ ዋና ዐላማ የሙስሊሙን ኡማ አንድነት መጠበቅ ነው:: የግለሰቦች መብት ለኡማው መብት መገዛት አለበት:: በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ያሉት ሕጐች በዘመናችን ያለውን ዐይነት የዲሞክራሲ አካሄድ የሚከተሉ አይደሉም[6]:: ሙስሊሞች በሊበራል ዲሞክራሲ ውስጥ ያለውን የግለሰቦችን መብት ጉዳይ ሲሰሙ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤ ይሰማቸዋል::

እንዲያውም በቅርብ ዓመታት ውስጥ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ የሙስሊም አገሮች መማክርት እስላማዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አውጥቶአል:: ከዐሥራ ሦስት ምዕተ ዓመት በፊት በመዲና እንደ ነበረው ሕግ፣ የማኅበረሰቡ መብት ከግለሰብ መብት በላይ እንደ ሆነ ዛሬም ሙስሊሞች ያምናሉ[7]::

መሐመድ የሙስሊሞችን አገዛዝ በመዲና አካባቢ በሚገኙ ግዛቶች ሁሉ አስፋፉ፤ ሕጉም ተግባራዊ የሚሆነው እስልምናን በተቀበሉ ሰዎች ላይ ብቻ አልነበረም:: ሙስሊም ያልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙስሊማን አስተዳደርና በእስልምና ሕግ ሥር ሆነው መኖር ነበረባቸው:: በመዲና ሙስሊም ያልሆኑትን ክፍሎች በተለይም የአይሁዶች፣ የክርስቲያኖችንና የዞራአስተሪያንን መብቶች በተወሰነ መልኩም ቢሆን መጠበቅ ተችሎአል:: ይሁን እንጂ ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ቡድን የእስልምናውን የግዛት አንድነት በአደጋ ላይ መጣል አይፈቀድለትም:: ለምሳሌ በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ የነበሩ ሰዎች፣

---

[6] George W. Braswell Jr. *Islam: Its Prophet, Peoples, Politics and Power* (Nashville: Broadman & Holman Publishers, 1996), 127.

[7] Javid Iqbal, "Democracy and the Modern Islamic State," in *Voices of Resurgent Islam*, edited by John Esposito (New York: Oxford University Press, 1983), 252-60.



በእስልምና ላይ እያሤሩ እንደ ሆነ መሐመድም ሆኑ ሙስሊሞች ባረጋገጡ ጊዜ በሤራው የተጠረጠሩ ሰዎች ሁሉ እንዲገደሉ ተደርጉአል::

የዐረብ ማኅበረሰብ በተለያዩ ጐሣዎች የተከፋፈለ እንዲሁም አንዱ ጐሣ ከሌላው ጐሣ ጋር በጠላትነት የሚተያይ ነበር:: መሐመድ በመዲና ቆይታቸው በከተማው የነበሩትን ተጻራሪ ጐሣዎች ወደ አንድነት በማምጣት፣ የሙስሊሙን ኡማ መሠረቱ:: ይህም ኡማ የሙስሊም ግዛት ተብሎ ይጠራል:: እንዲህ ዐይነቱ ሥራ ንቁ የፖለቲካ ብቃትን ይጠይቃል:: በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩትን የመዲና ጐሣዎች ዕርቀ ሰላም እንዲያወርዱ የማድረጉ ጥረት በዐረብያ ያሉ ጐሣዎች ሁሉ ወደ አንድነት እንዲመጡ ምክንያት ሆኖአል::

የእስልምናው እንቅስቃሴ ከመዲና ዐልፎ ወደ ሌሎች ቦታዎች ሲዛመት፣ ዐረብ ክርስቲያኖች ለዚህ ዐይነቱ ሙስሊማዊ አካሄድ ትልቅ ፈተና ነበሩ:: ሙስሊሞች፣ ዐረብኛው ቁርአን የመጨረሻው የአምላክ መገለጥ ስለሆነ፣ የዐረብ ዝርያ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ወደ እስልምና መቀየር አለባቸው የሚል እምነት ነበራቸው:: በቀጣዮቹም ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ዐረቦች ሁሉ ወደ እስልምና ተቀየሩ:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ዐረብ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና የተለወጡት ሙስሊሞች ያካሂዱባቸው ከነበረው ከፍተኛ ጫና እንዲያውም ከፍተኛ የሆነ ማስፈራራት የተነሣ ነበር:: ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ያደርሱ ስለነበረው ጫና በናሙናነት ከሚያሳዩን ማስረጃዎች መካል አንዱ፣ ካሊፍ ዋሊድ የተባለው ሰው፣ ታግሀሊብ ለተባለው የክርስቲያኖች መሪ በተግሣጽ መልክ ያስተላለፈውን መልእክት እንመልከት:— "አንተ የዐረብ መሪ ስትሆን እንዴት መስቀልን ታመልካለህ? ይህ የአንተ ድርጊት ዐረቦችን የሚያሳፍር ድርጊት ነው[8]"::

## የዳር አል-ኢስላም (የሰላም/የሙስሊሞች ክልል) መጀመር

በመዲና አማኙ ኅብረተሰብና የፖለቲካው ሥርዐት ተቀላቅለው ነበር:: መሐመድ ነቢይም የአገር ገዢም ነበሩ:: በመሐመድ አስተዳደር ሥር የነበረው አካባቢ ዳር ሰላማዊ እንደ ነበር ይታመናል:: ይህ የሰላም ቀጣና በመዲና አካባቢ ዳር አል-አህድ (የስምምነት ቤት) ወይም ዳር አል-ኢስላም (የሙስሊሞች ቤት) በመባል ይጠራል:: ከሦስት ምዕተ ዓመታት በኋላ ዳር

---

[8] Jacqueline Hoover, "Pre-Islamic Arabia." Lecture from excerpts of Robert G. Hoyland, *Arabia and the Arabs* (New York: Routledge, 2001), 229-47.

አል-ሳላም (የሰላም ቀጣና) የሚለው አስተሳሰብ ሙስሊሞች ዓለምን ሁሉ መምራት አለባቸው የሚለውን አስተሳሰብ ወለደ።

ዳር አል-ኢስላም ማለት በሙስሊሞች አስተዳደር ሥር ያለ የሰላም ቀጣና ማለት ነው። ሙስሊሞችንና ሙስሊም ያልሆኑትን በተመለከተ ዳር አል-ኢስላማ የሚለው የአስተሳሰብ ዘር የተዘራው የእስልምናው ኡማ በመዲና በተጀመረ ጊዜ ነው። ቁርአን ራሱ ይህንን ዘር በኅብረተሰቡ ውስጥ ዘርቶአል። ቁርአን ዳር አል-ኢስላምን ውብ በሆነ ቋንቋ እንዲህ ሲል ገልጾታል :—

> አላህም ወደ ሰላም አገር ይጠራል፤ የሚሻውንም ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል። ለነዚያ መልካም ለሠሩት መልካም ነገርና ጭማሪም አላቸው፤ ፊቶቻቸውንም ጥቁረትና ውርደት አይሸፍናቸውም፤ እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው፤ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው (ሱራ 10+25-26)።
>
> ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ የሰላም አገር አላቸው፤ እርሱም ጌታህ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ረዳታቸው ነው (ሱራ 6+127)።

የሙስሊም ኡማ በመዲና የፖለቲካ የበላይነት ስለነበረው፣ ፈጣን ዕድገት አሳየ። በመዲና የነበረው የሙስሊሞች ስኬት በመካ ሥልጣንና የፖለቲካ የበላይነት ያልነበራቸው ሙስሊሞች ከደረሰባቸው መከራ ፍጹም ተቃራኒ ነበር።
ሙስሊሞች በመካና በመዲና የነበራቸው ተሞክሮ እስልምናን ለማስፋፋት የፖለቲካውንና የሥልጣንን የበላይነት መያዝ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው እንዲሉ አድርጓቸዋል። ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት በሌላቸው ጊዜ የሙስሊም ተልእኮና ስኬት መሰናክሎች እንደሚገጥሙት በአንጻሩ ደግሞ የሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት መረጋገጥ እውነት እንዲያሸንፍና የሙስሊሙን ማኀበረሰብ መብቶች ለማስከበር ይረዳል የሚል እምነት አላቸው።

## <u>ሙስሊሞችና መንግሥት</u>

ኬኔት ክራግ፣ "የእስልምናን ታሪክ እንዲሁም የእስልምናን ነገረ መለኮት ማጥናት ማለት፣ ከየትኛውም እምነት ይልቅ ህልውናውንና ትምክታቸውን ለማረጋገጥ የፖለቲካን ሥልጣን መሠረት የሚያደርግ ከፍተኛ የሆነ ቊርጠኝነት ያለውን የሃይማኖት ክፍል ማጥናት ማለት ነው"[9] ይላሉ።

[9] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 32.



በኘሪንስተን ዩኒቨርስቲ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር የሆኑት በርናርድ ልዊስ ስለዚሁ ጉዳይ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተዋል:—

> ሙስሊም የሆነ ማንኛውም መንግሥት ቀዳማይ ዐላማው፣ እያንዳንዱ ሙስሊም መልካም የሆነ ሙስሊማዊ ሕይወት እንዲኖር ማስቻል ነው። ይህ የመልካም ሙስሊማዊ መንግሥት ዐላማ የመጨረሻው መመዘኛ ሲሆን እግዚአብሔር መንግሥትን የመሠረተበት እንዲሁም ባለሥልጣናትን የሚሾምበት ዋነኛ ዐላማም ይኸው ነው የሚል እምነት አላቸው። የመንግሥት ብቃት፣ የባለሥልጣናት መልካምነትና ክፋት የሚመዘንበት መስፈርትም ይኸው ነው[10]።

ሙስሊም ያልሆነ አንድ መንግሥት ይህ ዐይነቱን ሙስሊማዊ ጥቅም ማስከበር ይችላልን? ላይፈጽም ይችላል። ይህ ርእስ ጉዳይ በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩ ኡላማዎች (የእስልምና ሕግ ምሁራን) መካከል ይደረግ የነበረ ክርክር ነው። ክርክሩ ሙስሊሞች የሙስሊም ግዛት ወዳልሆኑት የምዕራባውያን አገሮች እንዳይሄዱ እንዲሁም ኑሮአቸውን በዚያ እንዳያደርጉ ወደ መከልከሉ ያዘነበለ ነው[11]። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያለው ከፍተኛ ፍልሰት በዚህ ረገድ ያለው ሕግ እውን እንዳይሆን አድርጎአል። እንዲያውም በአሁን ጊዜ የተወሰኑ ሙስሊሞች ለሃይማኖት ጉዳይ ለዘብተኛ የሆነው የምዕራባውያኑ ባህል ለሙስሊሙ ኡማና ለእያንዳንዱ ሙስሊም ከፍተኛ የሆነ ከለላ ሊሰጥ እንደሚችል ተረድተዋል።

የእስልምና ሃይማኖት ፕሮፌሰር እንዲሁም የኢራን ሺአ እስልምና ተከታይ የሆኑት ሐሚዳህ ሞሐገገ የሚባሉት ወይዘሮ በጀርመን አገር ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ የኖሩ ሲሆን፣ በጀርመን አገር ለተሰበሰቡት አናባፕቲስቶች ከላይ ያለውን ሐሳብ በመደገፍ እንዲህ ሲሉ ንግግር አድርገዋል:—

> ሙስሊሞች በሰላም የሚኖሩበት ሥፍራ ሁሉ የእስልምና ቤት ነው። ያም ዳር አል-ኢስላም ነው። ጀርመን ሙስሊሞች በሰላም የሚኖሩባት አገር እስከ ሆነች ድረስ ጀርመን ዳር አል-ኢስላም ናት[12]።

[10] Bernard Lewis, *The Political Language of Islam* (Chicago: Chicago University Press, 1969), 29

[11] Bernard Lewis, *What Went Wrong? Western Impact and Middle Eastern Response* (New York: Oxford University Press, 2002), 36-37.

[12] Hamideh Mohagheghi, "The House of Islam." Lecture at the *Theologische Studientage der* AMG, Heiligenstadt, October 6-10, 2002

## ዛሬም መዲና ሞዴል ናት

ሙስሊሞች የጥንቷን መዲና የፍጽምና ተምሳሌት አድርገው ስለሚመለከቱ፣ አብዛኛው ሙስሊም ዳር አል-ኢስላምን መመሥረት ቀዳማይ ግቡ ነው:: ፕሮፌሰር ሐሚዳህ ይህንን ዐላማ አስመልክተው በ2002 ዓ.ም ላይ በጀርመን አናባፕቲስት መማክርት ላይ በመገኘት እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተዋል:—

> የእስልምና አስተዳደር በመዲና ከተማ ከተመሠረተ በኋላ እንስሳት እንኳ በሰላም መኖር ጀምረው ነበር:: በነቢዩ አስተዳደር መዲናና አካባቢው ፍጹም የሆነ ሰላም ሰፍኖበት ነበር[13]::

ይህ የመዲና ተሞክሮ የሙስሊሞች ኡማ ይረጋገጥ ዘንድ የፖለቲካ የበላይነት ማግኘት ዋነኛ ነገር እንደ ሆነ፣ ይህም የፖለቲካ የበላይነት ሰላምን እንደሚያሰፍን ትምህርት እንደ ሆናቸው ይናገራሉ:: በእስልምና ቍጥጥር ሥር ያልዋለ አካባቢ (ዳር አል-ኢስላም) የጦርነት ምድር (ዳር አል-ሐርብ) ተብሎ ይጠራል:: ሙስሊሞች ዓለማችንን በሁለት ዐቢይ ወገን ከፍለው ይመለከቷታል:: ይኸውም በእስልምና ቍጥጥር ሥር የዋለው አካባቢ የሰላም ምድርና ተብሎ ሲጠራ፣ በእስልምና ቍጥጥር ሥር ያልዋለው አካባቢ ደግሞ የጦርነት ምድር ይባላል::

## ድል አድራጊ ሙስሊሞች

መሐመድ ከሒጅራ ጉዞ በኋላ ለዐሥር ዓመት በሕይወት ኖረዋል:: በእነዚህ ዐሥር ዓመታት የነበረው የመሐመድ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መስፋፋት (ዳር አል-ኢስላም) እጅግ አስገራሚ ነበር:: ሙስሊሞች፣ ስኬታማ የሆነው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እስላማዊውን አስተዳደር በምድረ ዐረቢያ ሁሉ ማስፋፋት ሲጀምር (ዳር አል-ኢስላም)፣ የጦር ምድር (ዳር አል-ዐረብ) የሚባለው ክልል መሸሽና ማፈግፈግ ግድ ሆኖበታል ይላሉ::

በሰላም ምድርና በጦርነት ምድር መኻል የተካሄደው በጦር ኀይል የታገዘ ነው:: የእስልምና ኀይሎች በመሐመድ መሪነት ከእስልምና ጠላቶች ጋር ባደረጉዋቸው ውጊያዎች ሁሉ አመርቂ ድሎችን አግኝተዋል:: የጠላት ጦር ቍጥር በበዛባቸው ዐውደ ግንባሮች ሳይቀር ሙስሊሞች ጠላቶቻቸውን ድል ነሥተዋል:: የሙስሊሞች ድል የመሐመድን ነቢይነትና የእስልምናን እውነት የሚያረጋግጥ እንደ ሆነ በሱራ 8፥5-19 ላይ ተገልጾአል:: ሙስሊሞች ይህን ይበሉ እንጂ፣ ቢያንስ በአንድ የጦር ውሎ መሐመድና ተከታዮቻቸው ድል

---

13 ዝኒ ከማሁ::



እንደ ተመቱ ይታወቃል:: በኡሑድ ዐውደ ግንባር የመካ ጦር በመሐመድ የሚመራውን የሙስሊም ጦር ያሸነፈ ሲሆን፣ መሐመድ በጦርነቱ ክፉኛ ቈስለው ሁለት ጥርሶቻቸውን ያጡ ሲሆን፣ ሰባ ሙስሊሞችም በዐውደ ግምባሩ ተገድለዋል::

ቁርአን በሱራ 3፥134-200 ይህ ሽንፈት ለምን ሊከሠት እንደ ቻለ ሰፊ የሆነ ነገረ መለኮታዊ ማብራሪያ ይሰጣል:: ይኸውም እስልምናን ለመከላከል የሚሞቱ ሰዎች ሰማዕት ሲሆኑ፣ መንግሥተ ሰማይም በቀጥታ የመግባት ዕድል ያገኛሉ:: እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው የሚሞትበትን ቀን ስለወሰነ፣ አንድ ሰው ጦር ሜዳ ቢሄድ ወይም ደግሞ በሰላም ቤቱ ቢቀመጥ ቀኑ ከደረሰ ከሞት ማምለጥ አይችልም:: በመሞቻው ቀን ላይ አንዳችም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም:: ጣዖት አምላኪዎች በእስልምና ላይ ምን ጊዜም የበላይነት ሊኖራቸው እንደማይገባ እንዲሁም ሙስሊሞች ለነቢዩ መሐመድ እስከ ታዘዙ ድረስ ድል በደጃቸው እንደ ሆነች የኡሑዱም ጦርነት ሙስሊሞች እምነታቸው የሚፈተንበት ዐውደ ግንባር እንደ ሆነ ነው:: በርቱ የማታ ማታ ድሉ የእኛ ነው:: እግዚአብሔር ይቅር ባይና መሓሪ ነው[14]::

ሙስሊሞች ከኡሑድ ጦርነት ሽንፈት በማገገም፣ ከሒጅራ ጉዞ ዐሥር ዓመት በኋላ መላው ዐረብያን በእስልምና አስተዳደር ሥር እንዲገባ አደረጉ:: ከሒጅራ ጉዞ ስምንት ዓመት በኋላ፣ መሐመድ የሙስሊምን ጦር በመምራት መካን ያዙ:: የመሐመድ ጦር ተከታታይ መሆን ጥቃት በማካሄዱ የመካ ነዋሪዎች ወታደራዊ ጕልበት ተፈታ:: መሐመድ ዐሥር ሺህ የሚሆን ጦር እየመሩ ወደ መካ የገቡት፣ "እውነት መጣ፤ ውሸትም ተወገደ፤ እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና" (ሱራ 17፥81) የሚለውን በማወጅ ነበር::

# እውነትና የፖለቲካው ሥርዐት

መሐመድ በመዲና ቆይታቸው የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እምነትና የፖለቲካው ሥርዐት እንዲጋባ አድርገዋል:: በዚህ ስኬት መሐመድ ዓለም ዐቀፋዊ ራእይ እንዲኖራቸው እንዲሁም ይህ ራእይ በዓለም ሙስሊሞች ዘንድ ቀጣይነት እንዲኖረው አድርገዋል:: ዳር አል-ኢስላም የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከፖለቲካው ሥርዐት ጋር በቍርኝት እንዲሠራ የሚያደርግ ምልክታ ነው::

ሙስሊሞች ኢየሱስ የፖለቲካውን ሥርዐት ለመቈጣጠር አንዳችም ፍላጎት እንዳልነበረው ይረዳሉ:: በእርግጥም ሥልጣን ሊያስጡት የሚችሉትን

---

14 Alfred Guillaume, *Islam* (New York: Penguin, 1979), 46.

አጋጣሚዎች አልተጠቀመባቸውም—አይፈልገውምና። በሙስሊሞች ዕይታ ግን ይህ ዐይነቱ የኢየሱስ አካሄድ፣ ተግባራዊነት የጐደለውና ምሉዕ ያልሆነ ነው። እንደ ሙስሊሞቹ ትምህርት፣ ተግባራዊ እምነት በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍንና የበላይነት መያዝን ይጠይቃል። አብዛኛውን ጊዜ ሙስሊሞች፣ "እናንተ ኢየሱስ ባስተማረው የፍቅር ሕግ አገርን እንዴት መምራት ትችላላችሁ?" ሲሉ ይጠይቃሉ። ይህ የፍቅር ሕግ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ላስገዙ መነኩሳት እንጂ፣ ይህንን ክፉ ዓለም ለማስተዳደር አይሠራምና። ስለዚህ የክርስቶስ አገልግሎት በተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። ሙስሊሞች የፖለቲካ ሥርዐቱም ሆነ የመንግሥት ሹማምንት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊመጡ የሚችሉት በኢየሱስ ሳይሆን በመሐመድ አገልግሎት እንደ ሆነ ይናገራሉ።

የመሐመድ የፖለቲካ አካሄድ ከኢየሱስ ጋር ተመሳሳይ እንዳይደለ ሙስሊሞች መረዳታቸው/መናገራቸው ትክክል ነው። ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በፖለቲካና በጦር ኀይል የታገዘውን መንግሥት አልቀበልም በማለት ለቀረበለት ጥሪ ጀርባውን ሰጠ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ላይ "ጨው"፣ "ብርሃን" እንዲሁም "እርሾ" በመሆን ዓለምን እንደሚያጣፍጡና እንደሚያደምቁ አስተምሮአል። ይህ የጽድቅን መንገድ የሚከተሉ ሰዎች በእያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍልና በፖለቲካው ውስጥ መልካምን ነገር ለማምጣት ኀያልና ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ተጽእኖ ማድረግ እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ተከታዮቹ ፖለቲካውን የመቈጣጠር አጀንዳ እንዲኖራቸው የማነሣሣት ዕቅድም ሆነ ትምህርት አልነበረውም። ነገር ግን ማናቸውም ዐይነት የፖለቲካ ሥርዐት የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስክርነት ማዳመጥ እንዲሁም ለፍትሕና ለጽድቅ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት አለበት—ይጠበቅበትማል። ነገር ግን ኢየሱስ በሕይወቱም ሆነ በትምህርቱ ግልጽ ያደረገው ቍም ነገር የትኛውም የፖለቲካ ሥርዐት የእግዚአብሔር መንግሥት ያለመሆኑን ነው።

እንደዚህ ሲባል ግን በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል መደጋገፍ አይኑር ወይም ለጌታ ታማኝ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ መሰደድ አለባት ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት የምታስተምረው ነገር የለም ማለት በፍጹም አይደለም። ሆኖም የተለያዩ የክርስቲያን ማኅበረሰብ ክፍሎች የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ምን መምሰል አለበት በሚለው ጒዳይ ላይ የተለያየ ዐይነት አመለካከት አላቸው። ከዚህም ምልከታ የተነሣ፣ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል በአንዳንድ አካባቢዎች የቀረበ ግንኙነት ሲኖር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ምንም ዐይነት ግንኙነት



አይታይም። ለምሳሌ በሶቭየት ሶሻሊስት ሥርዐት ዘመን የሶሻሊስቱን ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ አገሮች፣ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ሆነው ነበር።

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የዳግም መጥምቃውያን (የአናባፕቲስት) እንቅስቃሴ፣ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት የተለያዩ ተቋማት ናቸው የሚል አስተምህሮ ነበረው። እስካሁን ድረስ የአናባፕቲስት አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን መልክ የሚበላሸው ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለማስፈጸም ስትል ከመንግሥት ጋር መተባበር ስትጀምር ወይም መንግሥት አገራዊ አጀንዳውን ለማስፈጸም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሲሠራ ነው ይላሉ። ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ሰላም ሠርቶአል፤ ጸልዮላታልም። ነገር ግን የእርሱ መንግሥት ኢየሩሳሌምን የፖለቲካ ሥርዐት ማዕከል ያደረገ አልነበረም። አናባፕቲስት ክርስቲያኖች፣ የመጀመሪያዪቱ የሆነችው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንና በወቅቱ የነበረው መንግሥት የተለያዩ ተቋማት ሆነው የመኖራቸው እውነት በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ምሳሌ ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያንነቷ፣ መንግሥትም መንግሥትነቱ ይቀጥል፣ አንዱ ከሌላው ጋር ሊጋባ አይገባውም ይላሉ።

በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በመጀመሪያ በመዲና የነበረው የሙስሊሙ ኡማ አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ለሙስሊሙ ኡማ መሠረትን ጥለዋል። በሙስሊም ኡማ የኡማውና የፖለቲካ ሥርዐቱ መዋሐዳቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ እንዲሁም የሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሠረት ነው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የፖለቲካውንና የጦር ኀይሉን የበላይነት እስካልተቈጣጠረ ድረስ፣ እስልምና ወደ ፍጽምና ደረጃ እንደ ተሸጋገረ አይቈጠርም። እንደ ሙስሊሞቹ ትምህርት የፖለቲካው ኀይል ለእውነት (ለእስልምና) ጥበቃ ያደርጋል፤ እውነት ደግሞ በፖለቲካ ኀይል ሲደገፍ ያሸንፋል።

## እውነትና ኀይል

የእምነትና የፖለቲካ ሥርዐት ይለያዩ ወይስ ይጣመሩ የሚለው ጒዳይ፣ እውነት የፖለቲካን ኀይል ድጋፍ ትፈልጋለችን? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። በጦር ኀይል ተገዶ አንድን እምነት የሚቀበል ሰው ሕይወት/ነፍስ ዕጣ ፈንታዋ ምንድን ነው? የሃይማኖት ትምህርት ይህ ዐይነቱን የአስገድዶ ማሳመን አካሄድ እንዴት ይመለከተዋል?

እነዚህ ርእሰ ጉዳዮች የእስልምናን ሃይማኖት ስለሚያሳስቡት ቁርአን፣ "በሃይማኖት ማስገደድ የለም" (ሱራ 2+256) ሲል የተማሣጸ ምክር ይመክራል። ሙስሊሞች ለዚህ ቁርአናዊ ምክር ምን ያህል ታማኞች ሆነዋል? ቤተ ክርስቲያንስ ብትሆን ሰዎች የማመን ወይም ያለማመን መብታቸውን እንዲጠቀሙ ምን ያህል ነጻነት ትሰጣለች?

ኢየሱስ እውነትን በመግለጥ፤ ሰላምን ሰበከ እንጂ፣ እውነቱን ተቀበሉ በሚል ማንንም አላስገደደም። ይሁዳ ለሞት አሳልፎ እንደሚሰጠው እያወቀ እንኳ፣ አቋሙን እንዲለውጥ ግዳጅ ሲያደርግበት አንመለከትም። ሰዎች አንድን እምነትን ለመከተልም ሆነ ለመቃወም ሙሉ ነጻነት አላቸው።

ይህ ሰዎች በነጻነት በሙሉ ፈቃደኝነታቸው እምነታቸውን ይወስኑ የሚለው አስተሳሰብ፣ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት ዳግም መጥምቃውያን የሕፃናትን ጥምቀት እንዲቃወሙ እንዲሁም ለማመንና ክርስቶስን ለመከተል የወሰኑ ዐዋቂዎች ብቻ የውሃ ጥምቀት እንዲወስዱ ካደረጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ወላጆች እንኳ ለልጆቻቸው እምነትን መምረጥ አይችሉም። በርግጥ በሕፃናት ጥምቀት የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያናት እንኳ፣ ሕፃኑ ካደገ በኋላ የእምነት ማጽኛ ትምህርት በመከታተል እምነቱን በጉባኤ ፊት እንዲያሳውቅ ያደርጋሉ። ሰዎች የማመንም ሆነ ያለማመን መብታቸውን በነጻነት እንዲያደርጉት ቤተ ክርስቲያን ብታደፋፍርም አንዳንድ ጊዜ ግን ይህ የነጻነት ውሳኔ ጉዳይ በጉልሕ ሲከወን አይታይም።

ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ስትመሠረት የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? የሙስሊም ኡማ በመዲና በሚጀመርበት ወቅትስ? እነዚህ ክሥተቶች በቤተ ክርስቲያንና በሙስሊም ኡማ መካከል ስላለው እውነትና የፖለቲካ ኀይል ምን ያስተምሩናል? ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ቨርጂኒያ በሚገኘው በብሔራዊ የሕዝብ ሬዲዮ ጣቢያ ፕሮግራም ቃለ መጠይቅ ተደርጐልኝ ነበር። በቃለ ምልልሱ ወቅት አስተያየት የሰጠሁት መሐመድና ኢየሱስ ከፖለቲካ ኀይልና ከእውነት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነበር።

ቃለ መጠይቁን ያደረገልኝ ሰው፣ "በኢየሩሳሌም በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖችና ሰባኪዎች ምናልባት በኢየሩሳሌም ከኢየሱስ ጋር ከመሆን ይልቅ በመዲና ከመሐመድ ጋር መሆንን የሚመርጡ ይመስለኛል" ሲል ተናገረ። እኔም፣ "ምናልባት ይህ አንተ የምትለው ነገር እውነት ሊሆን እንደሚችል



እኔም ግምት አለኝ" አልሁት። ይህ ጉዳይ ከሙስሊሞች ጋር በምንወያይባቸው ጊዜዎች ሁሉ ወደሚነሣው መሠረታዊ ጥያቄ የሚወስደን ነው።

መሲሑ ኢየሱስ በአህያይቱ ውርጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የተገለጠው እውነት ምንም ዐይነት የኀይል ተገን አያስፈልገውም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተቸነከሩትንና የቈሰሉትን እጆቹን በመዘርጋት በመስቀል ላይ ለሰቀሉት ሰዎች የይቅርታ እንባ በማንባቱ የተገለጠ እውነት ነው። በተጨማሪም ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርት በሰጣቸው ሰላምና በላከላቸው መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ እውነት ተረጋግጦአል። በአንጻሩ ግን መሐመድ ወደ መካ ሲገቡ የሰበኩት እውነት የጦር ድጋፍ የጠየቀ ነበር። እንግዲያው እውነት ምን ዐይነት ባሕርይ አለው? የእውነተኛ ሰላም ባሕርይስ ምንድን ነው?

ወንጌልና እስልምና በልባችን እንዲሁም በታሪክ ለተጻፉት እውነታዎች የተለያየ ምላሽ አላቸው። እነዚህም የተለያዩ ምላሾች የተገለጡት ወደ ሁለት ከተሞች በተደረጉ የተለያዩ ጒዞዎች ውስጥ ነው። የናዝሬቱ ኢየሱስ በሕፃናት መዝሙር ታጅቦ ለመስቀል ሞት ፈቃደኝነቱን ያረጋገጠበት ጒዞ አንዱ ሲሆን፣ የቁሬይሹ መሐመድ ደግሞ የፖለቲካውንና የወታደራዊውን ኀይል ለመቈጣጠር ወደ መዲና የተሰደዱበት ጒዞ ደግሞ ሌላው ነው።

ሙስሊሞች ስለእስልምናው ሰላም ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። ቤተ ክርስቲያን የተጠራችው ግን የመሲሑን ሰላም ለማወጅ ነው። በዚህ የቤተ ክርስቲያን ጥሪ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ጥቃት ሊያደርስበት ለሚችለው ለዚህ የወንጌል እውነት ሕያው ምስክር የመሆን ታላቅ ኀላፊነት አለባት። ይህንን የእውነት ስጦታም ሰዎች በሙሉ ነጻነትና ፈቃድ ሊቀበሉትም ሆነ ሊቃወሙት ሙሉ መብት አላቸው። እንዲህ ዐይነቱም እውነት ታማኝነትና ድፍረት የተሞላበትን ምስክርነት ይፈልጋል። ይህን እውነት ለማወጅ አንዳችም የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይል ተገን አያስፈልገውምና።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ሉቃስ 10+28-48

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 8+5-19

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ያሳየው የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ዐይነት ባሕርይ አለው (ዘካርያስ 9፥9-10፤ ሉቃስ 19፥28-44)?
2. መሐመድ በመዲና የመሠረቱት መንግሥት ባሕርዩ ምንድን ነው (ሱራ 8፥37-41)?
3. የቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት ቀን የነበረውን ሁኔታ ይግለጹ (ሐዋርያት ሥራ 2፥1-47)። በቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን እንደ ነበር ያብራሩ።
4. በመዲና የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ይግለጹ። ለኡማው መመሥረት የመሐመድ ሚና ምን እንደ ነበር ይዘርዝሩ (ሱራ 8፥20-21)።
5. እውነት የሚያሸንፈው እንዴት ነው? በበዓለ ኀምሳ ቀን ቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት መልኩ ነው ወይስ የሙስሊም ኡማ በመዲና በተመሠረተበት መንገድ ነው?
6. "ወንጌልን የተቀበሉ ሰዎች እውነትን ከጥቃት ለመከላከል አንዳችም ኀይል ወይም ዐመጽ አይጠቀሙም" በሚለው ዐረፍተ ነገር ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ።
7. አሁን ቤተ ክርስቲያን ከኢየሱስ ጋር ኢየሩሳሌም ጉዞ የምታደርገው እንዴት ነው?



ምዕራፍ ዐሥር

# አሐዱ አምላክ
# ቶውሂድ—ሥላሴ

በፍጥነት ይጓዝ በነበረው ማርቸዲስ አውቶቡስ ውስጥ እንደ እኔው በጉዞ ላይ የነበረ አንድ ሰው፣ በአውቶቡሱ ውስጥ ከሚሰማው ከፍተኛ የሆነ የሙዚቃ ድምፅ በላይ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "ሙስሊም ነህ እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የለም እኔ ክርስቲያን ነኝ" ብዬ መለስሁለት። ሰው ሁሉ ይሰማው ዘንድ ይበልጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "እንግዲያው የመድበለ አማልክት አምላኪ ነኻ! ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምናለህ። ለእግዚአብሔር ልጅ የወለደችለት ሴት የእግዚአብሔር ሚስት ነበረች ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ።

በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ግንኙነት ውስጥ፣ "ኢየሱስን በተመለከተ የክርስቲያኖች እምነት ምንድን ነው?" የሚለው ጥያቄ ሙስሊሞች ሊያውቁት የሚፈልጉት ጥያቄ ነው። ይህ ዐይነቱም ጥያቄ በአውቶቡሱ ውስጥ እንደ ነበረው ዐይነት፣ ሰዎች ተጨናንቀው በሚገኙባቸው ቦታዎችም ሆነ ረጭ ባሉ ስፍራዎች ዘወትር የሚጠየቅ ጥያቄ ነው።

ይህ የአውቶቡስ ክሥተት ከተካሄደ ከብዙ ዓመት በኋላ በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ቢሮ በሚገኝበት አካባቢ፣ በርካታ ክርስቲያኖች ከሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ጋር የአንድ ቀን ውይይት አካሂደን ነበር። በስፍራው የሚካሄደው ውይይት፣ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በኅብረት የሚሳተፉበት የማኅበራዊ ዕድገትና የሰላም አፈላላጊ ጥምረት መመሥረት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የሚመክር ነበር። ከሙስሊሙ ወገን የተገኙት ሰዎች ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ባለ ሙያዎች ሲሆኑ፣ ሙስሊም ወርልድ ሊግ በተባለው እስላማዊ ድርጅት ውስጥ የመሪነት ድርሻ የነበራቸውም ሰዎች የጉባኤው ታዳሚ ነበሩ።

ርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ በመወያየት ላይ እያለን፣ የሊጉ መሪ ከምንወያይበት ርእስ ጋር በፍጹም ባልተዛመደ መልኩ ድንገት እመር ብለው፣ "የክርስቲያኖችንና የሙስሊሞችን ልዩነት በተመለከተ ማወቅ ያለብን መሠረታዊ ቊም ነገር አለ፤

ይኸውም ክርስቲያኖች በሦስት አማልክት ሲያምኑ እኛ ሙስሊሞች ግን በአንድ አምላክ ብቻ ነው የምናምነው" በማለት ተናገሩ::

## በሥላሴ ላይ የሚነሡ ተቃውሞዎች

ሁሉም ሙስሊሞች በእግዚአብሔር አሐድነት/አንድነት (ቶውሂድ) ያምናሉ:: በተጨማሪም እግዚአብሔርን ሦስት አካል እንዳለው ማሰብ አንድነቱን (ቶውሂድነቱን) እንደ መጣስ አድርገው ይመለከቱታል:: ይህ አስተምህሮ በሙስሊም ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፤ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ በቁርአን ውስጥ ሰፊ ትኩረት ስላገኘ ነው:: ርእሰ ጉዳዩን በቀጥታ እንዲሁም በማያወላዳ መንገድ መልስ ካልሰጠነው፣ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል እውነተኛ የሆነ መተማመንም ሆነ ፍሬያማ ውይይት ማካሄድ አይቻልም[1]::

አሕመድ እኛ በምንኖርበት ናይሮቢ በኢስትሌይ በሚገኘው ቤታችን አቅራቢያ የሚኖር ሱማሌያዊ መድረሳ (የእስልምና ትምህርት ተማሪ) ነው:: ከመስጊድ ወደ እኛ ቤት በመምጣት ላይ በነበረበት ወቅት፣ ስለ እግዚአብሔር አሐድነት (ቶውሂድነት) እያሰበ ነበር:: "ሆዲ" ብሎ ተጣራ:: ኬንያውያን ከደጅ ወደ ቤት መግባት ሲፈልጉ በቤት ያለው ሰው በር እንዲከፍትላቸው የሚጠሩት "ሆዲ" በማለት ነው:: እንዲገባ የበራችንን በር ስከፍትለት፣ "ለመሆኑ ሦስት አማልክት አሉ ብላችሁ ለማስተማር እንዴት ደፈራችሁ?" ሲል በቍጣ ጠየቀኝ::

"ግባ ግባ" ስል ጋበዝሁት፤ "ያሳሰበህን ነገር ሻያችንን ፉት እያልን ብንወያይበት ምን ይመስልሃል?" አልሁት:: አሕመድ ወደ ሳሎኑ እየገባ፤ "አይሆንም ዛሬ ከአንተ ጋር ለመቀመጥም ሆነ ሻይ ለመጠጣት በፍጹም ፈቃደኛ አይደለሁም:: በማኅበረሰባችን ውስጥ የምትዘሩት ሐሰትና ማታለል መቆም አለበት:: እግዚአብሔር አንድ (ቶውሂድ) እንጂ ሦስት አይደለም" አለ:: እኔም፣ "እኔ ራሴ የማምነው በአንድ አምላክ ብቻ ነው" ስል ከእርሱ ጋር ተሟገትሁ:: "ሥላሴ!" አለ በጩኸት፣ "ሥላሴ እያልህ በአንድ አምላክ አምናለሁ ማለት

---

[1] በትምህርተ ሥላሴ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን እንዲሁም አግሬ መስፍንና ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ቅድስት ሥላሴ የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ ትንታኔ* በሚል ርእስ የጻፉትን መጽሐፍ ይመለከቷል:: የመጀመሪያው መጽሐፍ የትምህርተ ሥላሴን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለጀማሪ አንባብያን የሚያስተዋውቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ አስተምህሮውን ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክና ከሥነ አመክንዮ አንጻር ይተነትናል::



አትችልም፤ የሥላሴ እምነት የመድበለ አማልክት እምነት ነው:: ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር አንድነት (ቶውሂድ) ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው:: ይህ አምሳያና አኩያ ለሌለው እግዚአብሔር፣ አምሳያና አኩያ (ሽርክ) ማበጀት ነው:: ይህ ዐይነቱ ኀጢአት የሰው ልጆች ሊሠሩ ከሚችሉት ኀጢአት ሁሉ እጅግ የከፋው ኀጢአት ነው:: ለበደሉም ይቅርታ የለውም"::

## የሥላሴ ትርጕም

"ሥላሴ ማለት የእኔና የአንተ መዋደድና መከባበር ማለት ነው" አልሁ:: አሕመድም እጅግ በመደነቅ፣ "ምን እያልህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ:: :

"ሥላሴ ማለት የእኔና የአንተ መዋደድ ማለት ነው" በመቀጠልም "በርግጥ ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም:: በነገረ መለኮት ትምህርት ውስጥ ክርስቲያኖች ቃሉን መጠቀም የጀመሩት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከዐረገ ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ ነው:: ተርቱሊያን የተባለ የሰሜን አፍሪካ የነገረ መለኮት ምሁር፣ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን መረዳት ሊወክል ከቻለ በሚል፣ 'ሥላሴ' የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ አውሉአል:: እግዚአብሔርን ከዚህ በተሻለ መንገድ የሚገልጽ ቃል ካለ፣ ያንን ቃል ልንጠቀምበት እንችላለን" አልሁት::

በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሰሜን አፍሪካ ይኖር የነገረው የነገረ መለኮት ምሁር ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ላይ ያለውን ነገር በመዋስ ገለጻዬን እንደሚከተለው አቀረብሁ፣ "እኛ ክርስቲያኖች ሥላሴ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው የእግዚአብሔርን ፍቅር ደካማ በሆነው በሰዎች ቋንቋ ለመግለጽ በምናደርገው ሙከራ ነው:: ሥላሴ ማለት በራሱ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለውን መስተጋብር፣ ኅብረት፣ የፍቅር ግንኙነት እንዲሁም አንድነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው:: ሥላሴ ማለት እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ነው:: ከእኛም ጋር ኅብረትን ያፈጠረው በራሱ አማካይነት የፍቅር አገልግሎት በመስጠት ለዚያም ደግሞ እኛን በመጋበዝ ነው::

እግዚአብሔር ራሱን እንዲሁም ፍቅሩን የገለጠልን፣ በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ነው:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረን የጋበዘን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በሰጠበት ፍቅርና ኅብረት ነው:: በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካይነትም ኢየሱስ እኛን በወደደበት ፍቅር እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ኀይል ተሰጥቶናል::

በአጠቃላይ ሥላሴ ማለት፣ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለ የፍቅር ግንኙነት ማለት ነው። እግዚአብሔር እርሱ ያለው ዐይነት ፍቅር እኛም እንዲኖረን ግብዣ ያቀርብልናል።

አሕመድ በተመስጦ ያደምጠኝ ነበር፤ ነገሩም እጅግ ሳያስደንቀው የቀረ አይመስልም። ጥቂት ካሰበ በኋላ፣ "የእግዚአብሔር በሆነው ፍቅር እኛም እርስ በርስ መዋደዳችን ጥሩ ነው" የሚል አስተያየት ሰጠ።

ከዚያ በኋላ ግን አሕመድ የቅርብ ወዳጄ እንዲሁም በኢስሊ በሚገኘው ሙስሊም ማኅበረሰብ ስለእኔ የሚሟገት ሰው ሆነ። ይህ ውይይት ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር የሚያወዛግባቸው ርእሰ ጉዳይ ምን እንደሚመስል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አመላካች ነው።

## ተዘውትረው የሚሰሙ ስሑት/የተሳሳቱ አስተሳሰቦች

ስለ ሥላሴና የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ሙስሊሞች ያላቸው ግራ መጋባት ወይም ተቃውሞ ትክክለኛ የሆነ የነገረ መለኮት መሠረት ያለው ነው። እነዚህ የነገረ መለኮት ተቃውሞዎች በአክብሮት፣ በውይይትና በምስክርነት መልስ ማግኘት አለባቸው።

ሁሉም ዐይነት ተቃውሞዎች የነገረ መለኮት መሠረት አላቸው ማለት እንዳልሆነ ግን ልብ ሊባል ይገባዋል። አብዛኛው ሙስሊም በክርስቲያኖች መሠረተ እምነት ላይ ያለው ተቃውሞ፣ ክርስቲያኖች ከሚያምኑት እምነት ጋር የተቃረነ እንዲሁም በተዛባ መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው። ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የሚያስተምረውን ትምህርት በጠለለ ሁኔታ ይረዱ ዘንድ፣ አሁን ያለውን ግራ መጋባት በሰከነ ሁኔታ ማረም ያስፈልጋል። በክርስትና መሠረተ እምነት ላይ ያላቸው መረዳት የተሳሳተ እስከ ሆነ ድረስ፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ከሙስሊሞች ጋር የነገረ መለኮት ውይይት ማድረግ አዳጋች ነው።

እነዚህ የተምታቱ መረዳቶች የበቀሉት የእስልምና እንቅስቃሴ ከተነሣበት ዐረባዊ ዐውድ (ሁኔታ) ነው። በምዕራፍ 2 ላይ እንደ ተመለከተው፣ መሐመድ ስብከታቸውን የጀመሩት የዐረብ አማልክቶች እርስ በርስ ተጋብተው ልጅ እንደሚወልዱ በሚታመንበት ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ስለዚህም በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የዐረብ ክርስቲያኖች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለው አነጋገራቸው መሐመድን ከፉኛ አወካቸው። ይህ ሐሳብ



አማልክት እርስ በርሳቸው ተጋብተው ልጅ ይወልዳሉ፣ ከሚለው የመድብለ አማልክት አምላክያን ሐሳብ ጋር ተመሳስለባቸው።

አስደናቂው ቀ‑ም ነገር፣ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ እነዚህ የዐረብ ክርስቲያኖች ሥላሴ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያለመረዳታቸው ነው። ስለዚህም ማርያም የእግዚአብሔር እናት ስለሆነች የሥላሴ አካል ነች ይሉ ነበር። ስለዚህ ሥላሴ ማለት አብ፣ ማርያምና ኢየሱስ ሲሆኑ፣ እነርሱም ሦስት አማልክት ናቸው የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበራቸው። በወቅቱ የነበሩት አብዛኞቹ ክርስቲያኖች አሁን ባለው መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ልብ በእጃቸው ያለመኖሩ፣ ለዚህ ችግር ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል። ቁርአን የሥላሴን አስተምህሮ የሚቃወመው ከዚህ ዐይነቱ የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ አንጻር ቆሞ ነው። ቁርአን የሥላሴ አስተምህሮ እጅግጸያፍና ውጉዝ ነው ሲል፣ እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ በወሲባዊ ግንኙነት ልጅ አይወልድም የሚለውን የአረማውያንን አስተሳሰብ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው (ሱራ 5፥75፤ 6፥100-101)። በየዘመናቱ ያለው የሙስሊም ኡማ ስለ ሥላሴ ያለው ግንዛቤ፣ ይህ ዐይነት አመለካከት ባለው የቁርአን አስተምህሮ የተቃኘ ስለሆነ፣ በየዘመናቱ ያሉ ሙስሊሞች ሥላሴን ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር አስተምህሮውን እንዲቃወሙ አድርጎአቸዋል።

ቁርአን ክርስቲያኖች ስለ ሥላሴ ያላቸውን የአብ፣ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ትምህርት በተመለከተ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። የኢየሱስን ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከል የተቃወመው የቁርአን ጥቅስ፣ ኢየሱስ መሲሕ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሆነ ይናገራል (ሱራ 4፥171)። እነዚህ የተሳሳቱ ሐሳቦች ሙስሊሞች ስለ ሥላሴ ያላቸውን ግንዛቤ በትክክለኛው ትምህርት ለማረቅ/ለማስተካከል የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ ቢያደርጉትም፣ የልብ ስፋቱ እስካለ ድረስ፣ ለውይይት ያለው ተስፋ ተሟጠአል ማለት አይደለም።

የሆነ ሆኖ እስላማዊ ነገረ መለኮት የዳበረው፣ የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት ባላገናዘበ ሁኔታ ነው። ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች ቁርአንን ሲተረጉሙ ቁርአንንና ሐዲስን መሠረት በማድረግ ብቻ እንጂ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ወይም ስለ መሲሑ የእግዚአብሔር ቃልነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት ባገናዘበ መልኩ አይደለም።

ስለዚህ ሙስሊሞች፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ መልአኩ ገብርኤል ነው" እንዲሁም "ኢየሱስ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል የተፈጠረ ፍጥረት እንጂ፣ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም" ባይ ናቸው።

ለሙስሊሞች የማሰናከያ ዐለት የሚሆንባቸው የእግዚአብሔር ሥላሴነት፣ ወይም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑ ጉዳይ ብቻ አይደለም። የተሳሳቱ ሌሎች ግንዛቤዎችም አሉ። ለምሳሌ ክርስቲያኖች መሲሕ የሚሉት እግዚአብሔር አብን እንደ ሆነ ቁርአን ያስተምራል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፣ "እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ" (ሱራ 5፥17)።

ክርስቲያናዊው ነገረ መለኮት መሲሑ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል እንዳችም ትምህርት የለውም። ይህ ማለት ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የጽንፈ ዓለሙ ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ነበር እንደ ማለት ነው። ይህ ትክክል አይደለም። ኢየሱስ አዘውትሮ አፍቃሪው ወደ ሆነው ሰማያዊ አባት ይጸልይ የነበረ መሲሕ ነው። በእግዚአብሔርም ላይ ይደገፍ ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት ኢየሱስ በእግዚአብሔር ላይ የማይደገፍ አልነበረም። መሲሑ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን የሚታዘዝና ከእርሱም ጋር ጠንካራ የሆነ ኅብረት ነበረው። ከኢየሱስ ጋር ኅብረት ማድረግ ማለት ከአብ ጋር መተዋወቅ ማለት ነው (ዮሐንስ 14፥6-11)። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሲሑ ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ ቢያስተምሩም፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትምህርት ግን የላቸውም። አብና ወልድ የተለያዩ አካላት ናቸውና[2]።

ቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚነት የሚስተዋለው ሌላው ችግር፣ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር አቻ/እኩያ (አጋሮች) ነን ይላሉ የሚለው ትምህርቱ ነው። እግዚአብሔር አቻና እኩያ የለውም፤ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው። ቁርአንም ቢሆን ከዚህ እውነት ጋር ይስማማል (ሱራ 6፥22-23፡ 136-37፡ 163)። አንድ የቁርአን ምንባብ፣ በሁለት አማልክት የሚያምኑ ሰዎችን ይኰንናል (ሱራ 16፥51)። ከእነዚህ የቁርአን ምንባባት ውስጥ አንዳንዶቹ የአረማውያንን መድብለ አማልክት እምነት የሚቃወሙ ናቸው። ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ምንባባት በግልጥም ሆነ በስውር (በውስጠ ወይራ) ክርስቲያኖችን የሚመለከቱ ናቸው።

---

[2] በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *ሰባልዮሳውያን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።



በተሳሳተ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተው ስሑት/ስሕተት የሆነው ይህ የቁርአን አተያይ፣ በየትኛውም አካባቢ በሚገኙ ሙስሊሞች ዘንድ በግልጽ ይስተዋላል። ለምሳሌ ከክርስቲያን ባልንጀሮቼ ጋር በመሆን፣ በአራት የተለያዩ ከተሞች ውስጥ በሚገኙ መስጊዶች ያካሄድኋቸው ጉብኝቶች ይህንኑ ጉዳይ የሚያጸኑ ናቸው። በአራቱም መስጊዶች የሚገኙት ኢማሞች በተመሳሳይ መንገድ እንዲህ አሉ፣ "እግዚአብሔር ልጅ ይወልዳል ማለት ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው እንደ ማለት ስለሆነ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሽርክ ኀጢአት መፈጸም ነው። ይህ ደግሞ ከኀጢአቶች ሁሉ የከፋው ኀጢአት ነው። የሽርክ ኀጢአት ንስሓ የለውም። እግዚአብሔር ልጅ ይወልዳል የሚል ማንኛውም ሰው ወደ ሲኦል ይሄዳል"።

እነዚህ ኢማሞች ይህን ነገር ደጋግመው የነገሩን ለእኛ ግድ ስላላቸው ነው። ይህን መሰሉን የማስጠንቀቂያ መልእክት በቀጥታ የሚነግሩንም ለዚሁ ነው። በእነዚህ አጋጣሚዎች ሁሉ ኢማሞቹ ምናልባት በተግሣጻችን አስቀይመናቸው ይሆናል ብለው ስለፈሩ፣ ከተግሣጻቸው በኋላ ይቅርታ ይጠይቁን ነበር። ይሁን እንጂ ልናስቀይማቸው እንችላለን በሚል ይህን ጉዳይ ከመናገር ቸል አላሉም።

እርግጥ ነው ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው ሊሉ አይገባም። በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን በመሲሑ በኩል በሙላት ገለጠ የሚለው ነገረ መለኮት፣ እግዚአብሔር ሁለት ወይም ሦስት ነው ወይም ደግሞ እግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው ማለት በፍጹም አይደለም። ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው እምነት እጅግ የራቀና ፍጹም የተዛባ ስለሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ጋር ውይይት በምታደርግበት በማናቸውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ፣ ይህን የተውገረገረና የተምታታ ሐሳብ የማስተካከል ትልቅ ኀላፊነት አለባት።

ትክክለኛ የሆነ መረጃን መሠረት ያላደረገው ይህ የተዛባ አስተሳሰብ፣ ሁነኛ ማስተካከያ እስካልተበጀለት ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን ራሱን በመሲሑ በኢየሱስ አማካይነት እንደ አዳኝና እንደ ቤዛ የገለጠውን አምላክ ለሙስሊሞች መግለጥ አትችልም። ይህ የተምታታ መረጃ፣ እግዚአብሔር በመሲሑ ሆኖ እኛን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር የሚለውን የወንጌል ትምህርት እንዳይቀበሉ መሰናክል ይሆንባቸዋል (2ቆሮ 5፥18)።

## ስለ እግዚአብሔር ልጅ ማብራራት

ከላይ እንደ ተገለጸው፣ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ልጅነት ላይ የተፈጠረውን ይህ ዐይነቱን ግራ መጋባት ለማስተካከል፣ በክርስቲያኖችና

በሙስሊሞች ባልንጀርነት ውስጥ ጠንካራ የመተማመን ግንኙነት እስኪፈጠር ድረስ መቆየት ያስፈልጋል ማለት የለባትም። ርእሰ ጉዳዩ የሙስሊሞችን አእምሮ ክፉኛ የሚረብሽ ጉዳይ ቢሆንም፣ ቤተ ክርስቲያን በቈራጥነት ልትናገረው የሚገባ እውነት ነው። በዚህ ረገድ የሐዋርያው የጴጥሮስ ምክር ማለፊያ ነው:—

> ማስፈራሪታቸውንም አትፍሩ አትናወጡም፤ ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቆአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን። በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት ነገር እንዲያፍሩ፣ በጐ ኅሊና ይኑራችሁ። የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ቢሆን ክፉ ስለማድረግ ሳይሆን በጐ ስለማድረግ መከራን ብትቀበሉ ይሻላችኋል (1ጴጥ 3፥15-17)።

አንድ ምሽት የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆኑት ዶክተር ዓሊና እኔ፣ በአንድ የፊላደልፊያ ጉዳና ላይ በሚገኝ መስጊድ ውስጥ ውይይቶችን እንመራ ነበር። በስብሰባው ሃምሳ የሚሆኑ ሰዎች የሚገኙ ሲሆን፣ የሙስሊሞቹና የክርስቲያኖቹ ቍጥር እኩል ነበር።

ዶክተር ዓሊ፣ "እኛ መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ አጥብቀን እንቃወማለን፤ ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ ማበጀት እግዚአብሔርን መሳደብ ነው" አሉ በአጽንኦት።

"ለዚህ ንግግርዎ መልስ እንድሰጥዎ ይፈቅዱልኛል?" ስል ፈቃድ ጠየቅሁ። ጥሩ ወዳጄ የሆኑት ዶክተር ዓሊም፣ "እንዴታ! ትችላለህ" አሉኝ።

ትልቅ አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ለአምስት ደቂቃ ያህል ስለ ክርስትና እምነት ለማብራራት ሙከራ አደረግሁ:— "ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ወሲባዊ ግንኙነት አድርጐ/ሚስት አግብቶ የልጅ አባት ሆነ የሚል አንዳችም እምነት የላቸውም። ይህ በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ነገር ስለሆነ ልናስወግደው ይገባል! ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ ማበጀትም በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ጉዳይ ነው። እኛም በሁለት ወይም በሦስት አማልክት በጭራሽ አናምንም"።

ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ መሲሑን "ልጄ" ሲል ጠርቶታል። በመሲሑ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ከሰማይ "የምወደው ልጄ ይህ ነው" ሲል ተደምጦአል። እግዚአብሔር መሲሑን የምወደው ልጄ



እርሱ ነው ሲል ምን ማለት ፈልጎ ነው የሚለውን ጉዳይ መመርመር ያለብን እኛ ነን። በራሱ በቁርአን እንኳ እግዚአብሔር መሲሑን "የምወደው ልጄ" ያለበት ሁኔታ አለ። እንዲሁም መሲሑ ካሊማቱኢላሂ (የእግዚአብሔር ቃል) ተብሎአል (ሱራ 4፥171)።

ዶክተር ዓሊም ለዚህ ንግግሬ እንዲህ ሲሉ ተቃውሞአቸውን አቀረቡ። "በእርግጥ መሲሑ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ማለት ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት አይደለም። በእግዚአብሔር ኪነ ጥበባዊ አሠራር እግዚአብሔር ቃል በሚናገርበት ጊዜ መሲሑ በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ተፀነሰ። የእግዚአብሔር ቃል አዳምን እንደ ፈጠረው፣ በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔር ቃል መሲሑን በድንግል ማሕፀን ውስጥ እንዲፀነስ አደረገ"።

እኔም በመቀጠል፣ "'ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው' ለሚለው ቁርአናዊ ሐረግ ለተሰጠኝ ሙስሊማዊ ትንተና አመሰግናለሁ። ኢንጂልም (ወንጌልም) መሲሑ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ መሲሑን 'የእግዚአብሔር ቃል' ሲለው፣ ምን ማለት ፈልጎ ነው የሚለውን ጉዳይ በዚህ ምሽት ሳብራራ በጥሙና እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ" አልሁ።

"ሙስሊማን እንደ መሆናችሁ መጠን፣ በሰማያት ስለሚገኘው የመጻሕፍት ሁሉ እናት ዐልፎ ዐልፎ ትናገራላችሁ (ሱራ 3፥7፤ 13፥39፤ 43፥4)። ይህ መጽሐፍ የማይለወጥና ያልተፈጠረ እንዲሁም በወርቅ ጽላት ላይ የተጻፈ መጽሐፍ ነው የሚል እምነት አላችሁ። በእርግጥ የወርቅ ጽላት የሚለው ገለጻ ተምሳሌታዊ ዘይቤ መሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ራሱን የሚገልጽ አምላክ ስለሆነ፣ ቃሉ ሕያው ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ ውሸት ስለሌለ ቃሉ ዘወትር ስለ እግዚአብሔር ማንነት ትክክለኛ የሆነ መረጃ ይሰጣል። በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መካከል አንዳችም ልዩነት የለም"።

"የክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት እንደሚያስረዳው፣ መሲሑ ሰው ሆኖ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሕያው የሆነው፣ ፈጣሪ ዐቅም ያለው እንዲሁም የሚቤዠው የእግዚአብሔር ቃል፣ በጽላት ላይ ብቻ ሊወሰን በፍጹም አይችልም። ይልቁንም ሕይወት ሰጪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ሰው በመሆን በመካከላችን ተመላለሰ። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከፈለግን፣ ከመሲሑ ጋር መገናኘት የግድ ይሆናል። እግዚአብሔር ራሱን በመካከላችን በሙላት የገለጠው በመሲሑ አማካይነት ነው። ስለዚህም በቃሉና በእግዚአብሔር መካከል አንዳችም ልዩነት የለም።

"የእግዚአብሔር ልጅ ማለት በሰው አምሳል የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውም ስያሜ ግንኙነትን አመላካች ቃል መሆኑ ብቻ ሳይሆን መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም የሆነ የፍቅር ግንኙነት እንዳለው የሚያሳይ ነው። ለዚህም ነው መሲሑ ኢየሱስ 'እኔና አብ አንድ ነን። እኔንም ያየ አብን አይቶአል' (ዮሐንስ 14+8-10) ሲል የተናገረው"።

"በመሲሑ አገልግሎት እኛም እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችን መሆኑን እንድናውቅ ተጋብዘናል። መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ከሰማይ አባቱ ጋር የነበረውም ግንኙነት ፍጹም ነበር። እኛም በመሲሑ በኩል የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች እንዲሁም ወንድና ሴት ልጆች ለመሆን ተጠርተናል/ተጋብዘናል (ኤፌሶን 1+5)"።

ከረዥም ዝምታ በኋላ ዶክተር ዓሊ፣ "ነገሩ እንዲህ ከሆነ ማመን እችላለሁ" አሉ።

## በርካታ ወንጌላት

ይህ ዐይነቱ ውይይት ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ላላቸው ተቃውሞ ሁሉ መፍትሔ እንደማይሰጥ እሙን ነው። ሙስሊሞች አዲስ ኪዳንን በተለይም ወንጌልን ሲያነቡ፣ ከዚህ የተለዩ በርካታ የሆኑ መሰናክሎች ይጋረጡባቸዋል። የናይሮቢን መስጊድ ከበርካታ ሰዎች ጋር ሆነን በመጐብኘት ላይ ሳለን፣ አንድ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር እንዲህ ሲሉ ጥያቄ ጠየቁ፣ "የመሲሑ የኢየሱስ ወንጌል የት ነው ያለው? አዲስ ኪዳን የአራት ሰዎችን ወንጌል ይዟል እንጂ የመሲሑን ወንጌል አልያዘም። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ወንጌሉን ይዞ መሄዱ ግልጽ ነው"።

ይህ ዐይነቱ ግራ የተጋባ ጥያቄ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የተወሰነ ትውውቅ ባላቸው በበርካታ የሙስሊም ሃይማኖት ምሁራን ዘንድ በስፋት የተሠራጨ ትምህርት ነው። ሙስሊሞች ቁርአን አንድ ነው ነገር ግን ወንጌል በአራት የተለያዩ ሰዎች የተጻፈ እንዲሁም የመሲሑን ወንጌል ያላካተተ መጽሐፍ እንደ ሆነ ያስባሉ። ከአራቱ ወንጌላት መካል የመሲሑ ወንጌል የለም የሚለው አስተሳሰብ፣ ሙስሊሞችን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ወስዷቸዋል።

በዚያን ወቅት በናይሮቢው መስጊድ ውስጥ አብረውን ከነበሩ ሰዎች መካል አንዱ፣ "በዐረብኛው ቁርአን መሲሑ ኢየሱስ 'ኢንጅል' (መልካሙ ዜና/የምሥራች) ተብሉ ተጠርቶአል (ሱራ 3+45)። ኢንጅል ማለት መልካም



የምሥራች ወይም ወንጌል ማለት ነው። መሲሑ ኢንጅል የተባለበት ምክንያት እርሱ ራሱ ወንጌል ስለሆነ ነው። ክርስቲያኖችም ኢየሱስ ወንጌልን ከሰማይ ይዞ መጥቶአል ብለው ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ ከሰማይ የመጣ ወንጌል ነው የሚል እምነት ነው ያላቸው። እርሱ ሰው ሆኖ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ ወንጌል መጽሐፍ ሳይሆን ሰው ነው፤ ይኸውም ሰው ሆኖ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል መሲሑ ኢየሱስ ነው"።

"ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌል ስለሆነው ስለ ኢየሱስ የራሳቸውን ምስክርነት ሰጥተዋል። እነዚህ አራት ሰዎች ስለኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት አንድ ዐይነት ምስክርነት ባይሰጡን እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት የዘገበልን አንድ ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ግለሰቡ የዘገበውን ዘገባ ተአማኒነት ማረጋገጥ አይቻልም ነበር። ነገር ግን እነዚህ አራት ምስክሮች በተለያየ መንገድ አንድ ዐይነት ምስክርነት መስጠታቸው የዘገባቸውን ትክክለኛነት የሚያስረግጥ ነው። በሕግ ችሎት ላይ የአራት ሰዎች ምስክርነት ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት አለው"።

"ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ስለ መሲሑ የራሳቸውን ምስክርነት በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ መርቶአቸዋል። ስለዚህም ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርትና አገልግሎት የሰጡት ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ እናምናለን"።

ይህ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፣ እውነተኛ ለሆነ ውይይትና መደማመጥ ራሳቸውን በአዘጋጁበት ስፍራ ሁሉ ሊገኝ የሚችል ተምሳሌታዊ ውይይት ነው። ሙስሊሞች መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ ለመቀበል የሚቸገሩበትን ምክንያት ክርስቲያኖች በውል ማወቅ ይፈልጋሉ። በተለይ ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት፣ ስለ ትምህርተ ሥላሴ ወዘተ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ከየት የመጣ እንደ ሆነ እንዲሁም እነዚህን ትምህርቶች ላለመቀበል ምክንያት የሆናቸውን የነገረ መለኮት መሠረት ማወቅ ይፈልጋሉ። የተዛባው ምልከታ በትክክል ከተመለሰ በኋላ ነው የነገረ መለኮት ውይይቱ መካሄድ የሚኖርበት። ሙስሊሞች አዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው፣ የሚለውን ጉዳይ በትክክል መረዳት አለባቸው። ክርስቲያኖች ትልቅ ዋጋ የሚሰጡትን እውነት ማለትም እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል እኛን የማስታረቁን እውነት ሙስሊሞች ሊገነዘቡ የሚችሉት፣ በቤተ ክርስቲያንና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አማካይነት ብቻ ነው።

# ወንጌልና ቁርአን

መሲሑ ኢየሱስን ከመሐመድ ጋር በማነጻጸር ማቅረብ፣ መሲሑ በክርስትና መሠረተ እምነት ውስጥ ያለውን ሁነኛ ስፍራ እንዲሁም መሐመድ በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ያላቸውን ዐቢይ ቦታ ክፉኛ የሚያበላሽ ነው:: ለዚህም አንዱ ምክንያት ሙስሊሞች ቁርአን በመሐመድ በኩል መጣ ብለው ሲያምኑ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ወንጌል አምጪ ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ ወንጌል ነው የሚለው እምነታቸው ነው::

"ሙስሊሞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ እግዚአብሔር ቁርአንን የገለጠው በመሐመድ በኩል ነው የሚል እምነት አላችሁ፤ አይደለም እንዴ?" ስል በፊላደልፊያ መስጊድ ለተሰበሰቡት ሙስሊሞች ጥያቄ አቀረብሁ:: የመስጊዱም ኢማም፣ "አዎን ትክክል ነው" አሉኝ::

በመቀጠልም የሚከተለውን ነጥብ ተናገርሁ፣ "ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም የመወለዱን እውነት ይቀበላሉ:: ራሱ ወንጌል የሆነው መሲሕ ወደ ዓለም የመጣው በድንግል በኩል ነው:: ሙስሊሞች ቁርአን በነቢዩ መሐመድ በኩል መምጣቱን ይቀበላሉ:: ድንግሊቱ መሲሑ ወደ ምድር የመጣበት ሰብአዊ መሣሪያ (ምክንያት) ስትሆን፣ መሐመድ ደግሞ ቁርአን የተገለጠባቸው ሰብአዊ መሣሪያ ናቸው"::

## <u>እውነታው ምንድን ነው?</u>

መሲሑም ሆነ ቁርአን በየራሳቸው ለቤተ ክርስቲያንና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) የእውነት ማዕከል ናቸው:: ሁለቱም ወገኖች፣ ኢየሱስም ሆነ ቁርአን መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎችን እንደ ገለጹ ያምናሉ:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐንስ 14፥6):: በሌላ ስፍራ፣ "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ተመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው:: ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም" (ዮሐንስ 5፥39):: ኢየሱስ በማመንና ባለማመን መካከል ልዩነት እንዳለም ተናግሮአል (ዮሐንስ 12፥35-50)::

በቁርአንም "ያም ከመጽሐፍ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲኾን እርሱ እውነት ነው" (ሱራ 35፥31):: ቁርአን የእውነት ሁሉ መለኪያ



እንደ ሆነ ይታመናል:: ይህም ጉዳይ እውነተኛ አማኞችንና እውነተኛ አማኞች ያልሆኑትን ሰዎች የሚለይ ጉዳይ እንደ ሆነ ይታሰባል (ሱራ 84፥20-25)::

በመሐመድ የተነገረው ቁርአንና ከድንግል ማርያም የተወለደው መሲሑ ኢየሱስ፣ የፍጹማዊ እውነት መስፈርትን በተመለከተ የሚያስተላልፉት መልእክት እርስ በርሱ ሊወዳደር/ሊነጻጸር የሚችል ነው:: መሲሑ በሰው አምሳል የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፣ ቁርአን ደግሞ በመጽሐፍ መልክ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የእውነት ማዕከል የሆነው ቁርአን ነው ወይስ መሲሑ የሚለው ጥያቄ ምን ለውጥ ሊያስከትል ይችላል? አንዳንድ የነገረ መለኮት ሰዎች ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፣ ኢየሱስንም ሆነ ቁርአንን በመያዝ የሚፈጥሩትን ክርክር ዕርግፍ አድርገው በመተው፣ ውይይታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ያድርጉ ሲሉ ይመክራሉ:: ምክንያቱም እርስ በርስ የሚያግባባቸውን መሠረት የሚያገኙት በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው የሚል ግምት ስላላቸው ነው::

ነገር ግን ያግባባል የተባለው እግዚአብሔር ራሱ ማነው? በርግጥ እርሱ አምባገነን ነውን? በርግጥ እርሱ ሰዎችን ያፈቅራል ወይስ ይጠላል? እርሱ ለሰው ልጆች የገለጠው ፈቃዱን ብቻ ነው ወይስ ራሱን/ማንነቱን ጨምሮ ነው? የሕይወት ትርጉሙና የሰው ልጆች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምንድን ነው? እነዚህንና እነዚህን መሰል ጥያቄዎች የምንመልሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ተገልጦልናል ከምንለው መገለጥ አንጻር እስከ ሆነ ድረስ የትኛውን መገለጥ ተከትለን እንሂድ የሚለው ጉዳይ እጅግ መሠረታዊ ነጥብ ይሆናል::

በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መሠረታዊ አስተምህሮ ላይ ስምምነቶች አሉ:: ይሁን እንጂ፣ ጳጳስ ኬኔት ክራግ ጥሩ አድርገው እንደ ገለጹት በእያንዳንዱ ስምምነት ላይ ልዩነት አለ:: ለዚህም ምክንያቱ መሲሓዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና የሙስሊሙ ቁርአን ወደ ተለያየ አቅጣጫ ስለሚወስዱን ነው::
መጽሐፍ ቅዱሳዊው መሠረተ እምነት፣ እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት እርሱ ራሱ በኀጢአት በተበላሸው ሕይወታችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት፣ ከኀጢአታችንና ኀጢአታችን ካስከተለው ሞት ዐርነት እንዳወጣን ያስተምራል:: እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት ከራሱ ጋር እንዲሁም እርስ በርሳችን እንዲሁም ደግሞ ከፍጥረት ጋር እንድንታረቅ እርሱ ራሱ በፍቅር ጠራን:: ቁርአን ደግሞ በአንጻሩ ርኅሩኅና አዛኝ የሆነው አምላክ ፈቃዱን ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ላከልን እንዲሁም ለፈቃዱ በመገዛት መልካምን ነገር

እንደምናገኝ ያስረዳል። ኢየሱስ የመቤዥትን ሥራ ሲሠራ ቁርአን ግን ምሬትን ይሰጣል።

## አንድነት-ተስእኮ-ልዩነት

እግዚአብሔር አንድ (ተውሂድ) ነው። እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (ሥላሴ) አንድ አምላክ ነው። ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ይህ ምልከታ የመነጨው መጻሕፍቶቻቸውን፣ ምስክርነታቸውንና ተልእኮአቸውን በታማኝነት ለመግለጽ ካላቸው ብርቱ ፍላጐት ነው።

ይህ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔርና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያላቸው የተለያየ መረዳት ሊመጣ የቻለው፣ ረጅም በሆነ የእምነት ጉዞ ነው። ይህ ዐይነቱ እምነት በምንኖርባት ምድር ስለ አንድነትና በአንድነት ላይ መሠረት ስላደረገ ልዩነት ትልቅ የሆነ ተሞክሮአዊ እንድምታ ያስከትላል። እነዚህ የተለያዩ መረዳቶች የሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን ስለ ሚስዮናዊነት ባላቸው ግንዛቤ ላይ ጕልሕ ሚና አላቸው።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) እግዚአብሔር አንድ ነው (ተውሂድ) የሚለውን ያህል ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር አንድ ነው የሚለውን ጕዳይ ከሙሉ ልብ ይቀበላሉ።

አንድ ክርስቲያን ሥርዐተ ጥምቀትን በሚወስድበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐቱን የምትፈጽመው በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም ነው። በአጠቃላይ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ሥርዐተ አምልኮ፣ አንቀጸ ሃይማኖትና የሃይማኖት መግለጫዎች ሁሉ መሠረት ያደረጉት አብን እንደ ፈጣሪ፣ ወልድን እንደ አዳኝ/መሲሕ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን በክርስቲያኖች ውስጥ እንደሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ራሱን በአንድነትም ሆነ በሦስትነት ለገለጠልን አምላክ በምንሰጠው የእምነት ምላሽ ላይ ነው። ይህ እንግዲህ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለ አንድነትና ብዙኀነት ነው።

እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ በማድረሱ ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው። እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን ላከ፤ እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስን ላከ፤ ይህ ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር በድነት ሥራ ውስጥ



ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳለው አመላካች ነው። እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ፈቃዱን ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም ጭምር ነው ይፋ ያደረገው። ኀጢአተኞችን በመውደዱ ኀጢአተኞችን ሊያድን ፈቀደ። ይህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ያላት ትልቅ የምሥራች እንዲሁም ጥሪ ነው። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም እንደ ላከ፣ ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ዓለም ልኳታል። ለምን? መሲሑ ኀጢአተኞችን ሁሉ ወዶ በፍቅር ሊያገለግላቸውና ሊያድናቸው በጐ ፈቃዱ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም የጠፉትን ልትፈልግ፣ ልትወድና ልታገለግል ኀላፊነት ስላለባት ነው።

በእግዚአብሔር ራስን የመስጠት ፍቅር ውስጥ አንድነት እንዲሁም አንድነትን መሠረት ያደረገ ልዩነት አለ የሚለው የእምነት አንቀጽ፣ ዐበይት በሆኑ አስተምህሮዎች ላይ መሠረት ላደረገው የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲሁም ንዑሳን/ደቂቃን ለሆኑ ትምህርታዊ ልዩነቶች መሠረት ጥሉአል። የቤተ ክርስቲያን አንድነት የተመሠረተው በፍቅር ራስን በመስጠት መሠረት ላይ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር ለእኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠበት ፍቅር እንዲሁም እኛ ለእግዚአብሔር ራሳችንን አሳልፈን የሰጠንበት ፍቅር በተጨማሪም አንዳችን ለሌላችን ራሳችንን የሰጠንበት ፍቅርና ለኀጢአተኞች ራሳችንን የምንሰጥበት ፍቅር ነው። ይህን ጕዳይ በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ የሚል አቋም አላት:—

> በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ፣ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን ከሁሉ በላይ የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉ አባት አለ (ኤፌሶን 4+4-6)።

ይህ በአንድነት ውስጥ ያለውን ልዩነት የሚያቅፍ ነው። የሥላሴ አስተምህሮ ራስን በመስጠት ላይ በተመሠረተው ፍቅርና ኅብረት ላይ የተመሠረተ ነገረ መለኮት ነው። ይህም ዓለም ዐቀፏን ቤተ ክርስቲያን በሁለት መንገድ ያሳድጋታል፤ ይኸውም በልዩነትና በአንድነት።

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ፣ "ቤተ ክርስቲያን ትልቅና አስገራሚ ልዩነት አላት። በዓለም ላይ ያለው የሙስሊም ማኅበረሰብ ግን በተመሳሳይ ሰዓትና በአንድ ዐይነት መልክ ይጸልያል። የአምልኮ ቋንቋው እንኳ ሳይቀር አንድ ነው። እኛ በዓለም ዐቀፍ ደረጃም ቢሆን ጠንካራ አንድነት አለን" ሲሉ ሐሳብ ይሰጣሉ።

ይህ በተመሳሳይ መንገድ ጸሎት የማድረሱ ሂደት የእግዚአብሔርን አንድነት ከሚገልጸው የሙስሊም ነገረ መለኮት (ተውሂድ) ጋር የሚጣጣም ነው።

ሙስሊሞች በእግዚአብሔር መካከል ልዩነት እንደ ሌለ ሁሉ፣ በፈቃዱም ውስጥ ልዩነት የለም፤ ይህ አንድነት መንጸባረቅ ያለበት ደግሞ በአምልኮ ውስጥ ነው የሚል አቋም አላቸው:: ለምሳሌ ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የእግዚአብሔር ፈቃድ በዐረብኛው ቁርአን ውስጥ ተገልጾአል:: ይህ እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠበት የዐረብኛ ቁርአን፣ በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐሙ፣ በሙስሊሙ ማኅበረሰብና በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ልዩነት ስለሚያስከትል የዐረብኛው ቁርአን በተለያዩ ቋንቋዎች በፍጹም መተርጐም የለበትም::

የእስልምና ተሐድሶ እንቅስቃሴ አራማጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ እንመሠርታለን ለሚለው ጥረታቸው መነሻ ሐሳብ የሚያደርጉት፣ የእግዚአብሔርን አንድነትና የእግዚአብሔርን አንድያ ፈቃድ ነው:: በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይገለጽ በሚለው ርእስ ጒዳይ ላይ የተለያዩ አተረጓጐሞች አሉ:: በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ አራት ዐይነት የትንታኔ አቅጣጫ የሚከተሉ የእስላማዊ የሕግ ትምህርት ቤቶች አሉ (ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ስለ እስላማዊ ሕግ በስፋት ይተነትናል):: ይህ ቢሆንም ግን ሁሉም እስላማዊ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች፣ የእግዚአብሔርን ብቸኛ ፈቃድ በምድር ላይ መመሥረት ቀዳማይ ዐላማቸው ነው::

ኢራናዊው የኅብረተሰብ ጥናት ምሁር ዓሊ ሻሪአቲ፣ የኢራንን እስላማዊ አብዮት ለማብራራት በሞከሩበት ወቅት፣ የዚህን አመለካከት ነገረ መለኮታዊ መሠረት ለመተንተን ሙከራ አድርገዋል:: የዚህ አብዮት ዋነኛ ዐላማ የአንዱን እግዚአብሔር አሐዳዊ ፈቃድ፣ በምድር ላይ በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ በአንድ ጊዜ እንዲሰፍን ማድረግ ነው:: ሻሪአቲ፣ አንድ ከሆነው ከዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማፈንገጥ ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ (ሽርክ) ማበጀት ነው ባይ ናቸው:: ሁሉም የሕይወት ክልል መንፈሳዊ ይዘት አለው (የተቀደሰ ነው)፤ ፖለቲካው፣ ምጣኔ ሀብቱ፣ ባህሉ፣ የአደባባይና የግጀት ሕይወት ሁሉ፣ አሐዳዊውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ማንጸባረቅ አለባቸው[3]::

ሸሪአቲ በሚተነትኑት በዚህ አሐዳዊ ማዕቀፍ ውስጥ አንዳችም አንድነትን መሠረት ያደረገ ኅብረ ልዩነት የለም:: ስለዚህ አሐዳዊ የሆነው ይህ እስላማዊ እንቅስቃሴ በግድም/በኀይልም እንኳ ቢሆን፣ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ግድ ነው:: አሐዳዊው የእግዚአብሔር ሕግ በሕዝቡ ላይ በኀይልም እንኳ ቢሆን

[3] Ali Shari'ati, On *the Sociology of Islam,* translated by Hamid Algar (Berkeley, Calif.: Mizan Press, 1979).



እንዳይጫን የሚከለክል ማንኛውንም ነገር ማስተናገድ፣ ልንታገሣቸው የማንችላቸው ልዩነቶች እንደ አሸን እንዲፈሉ በር ይከፍታል:: ይህም የቶውሂድን መሠረታዊ አስተምህሮ የሚቃረን ነው:: ይህ ዐይነቱን አመለካከት በሠለጠነው ዓለም ላይ ልጓን ብሉ መነሣት ደግሞ ቀላል የሆነ ትግል የሚጠይቅ አይደለም:: ይህም የኢራናውያን አብዮት ፍትጊያ የበዛበት እንዲሆን ማድረጉ የግድ ነው::

## ሙስሊሞች ለቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች

ሙስሊሞች ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱት፣ አሐዳዊውን የእግዚአብሔር ፈቃድ (ቶውሂድ) በምድር ላይ ለማስፈን ችላ እንደለ አካል አድርገው ነው:: ይህ ወቀሳ ጣምራ ገጽ አለው:: ይኸውም ግራ መጋባትን አመላካች ነው:: ይህ ትችት በሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች ሊገለጽ ያችላል::

### በክርስትና እምነት ይህን ያህል ልዩነት ስምን ሲከሠት ቻለ?

በመጀመሪያ ሙስሊሞች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህን ያህል ሰፊ የባህል እንዲሁም የአሠራር ልዩነት የመኖሩ ጒዳይ ያስገርማቸዋል:: የሃይማኖት ሥርዐት ወይም ክህነታዊ ተቋማት የሌላቸው ክዌከሮች (Quakers)፣ ክህነታዊ ሥርዐትካላቸው እንዲሁም በአምልኮተ ሥርዐት ወቅት ዕጣን ከሚታጠንባት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት፣ ክርስቲያኖች እንዲሁም በአንድ መሠረተ እምነት ውስጥ ያሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሊባሉ እንዴት ይችላሉ? ክርስቲያኖች በክርስትና እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ልዩነት በኅብረ ቀለማት ባሸበረቀ በኅብር-ልዩነትና ኀይል ቢመለከቱትም፣ ሙስሊሞች ግን ይህን በይዘት አንድ ሆኖ በቅርጽ የሚለያየውን ልዩነት መልካም ነው የሚል እምነት የላቸውም::

### ክርስቲያኖች ሺዩሱን የማይከተሉት ስምንድን ነው?

ከሙስሊሞች ወገን የሚሰነዘረው ሁለተኛው ሒስ፣ አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች ምድራዊውን ሕይወት መንፈሳዊና ዓለማዊ በማለት በሁለት ወገን የመወገን አባዜ ተጠናውቶአቸዋል የሚለው ጒዳይ ነው:: ለምሳሌ 1979-1981 ዓ.ም ተከሥቶ በነበረው የኢራን የዕገታ ቀውስ ወቅት ቻርልስ ኪምባል የተባለው የቅርብ ባልንጀራዬ፣ የአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን ወኪል ሆነው ከተጓዙት የልዑካን ቡድን አባላት ጋር ወደ ኢራን በመጓዝ፣ የኢራን እስልምና አብዮት መንፈሳዊ መሪ ከሆኑት ከአያቶላ ኾሚኒ ጋር ተገናኝቶ ነበር::

ወቅቱ የአሜሪካና የኢራቅ ግንኙነት አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀበት ጊዜ ነበር። ሆኖም አያቶላው ለአሜሪካውያኑ የልዑካን ቡድን የሰጡት ምክር፣ "ለአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን መልእክት አለኝ፤ ይኸውም እናንተ አሜሪካውያን ኢየሱስን ተከተሉ! በአሜሪካ የሚገኙ ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስን ቢከተሉ ኖሮ፣ በኢራንና በአሜሪካ መካከል ያለው ይህ ችግር በፍጥነት ይፈታ ነበር" የሚል ነበር።

እኔ እንደምገምተው እኚህ መንፈሳዊ መሪ፣ የአሜሪካ ክርስቲያኖች በዓለም ዐቀፍ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚል የተጋነነ ግምት ያደረባቸው ይመስለኛል። አያቶላው የአሜሪካኑን የኢራን መልእክተኛ ልዑካን እንደ መከሩት ብዙ ሙስሊሞች፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ ካመናችሁ፣ ከዚህ እምነት ጋር በተጣጣመ መንገድ ሕይወታችሁን ምሩ" ብለው ይነግሩኛል።

ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች፣ "እንደ እስልምናው ትምህርት የኢየሱስ አስተምህሮ ዘወትር በምድራዊ ሕይወት ተግባራዊ መሆን የሚችል አይደለም። ቁርአን ግን በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ዘወትር ተግባራዊ መሆን የሚችል እንደ ሆነ እናምናለን። ለምሳሌ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጦር እንዳይሰብቁ ወይም ፍቺ እንዳይፈጽሙ አስተምሮአል። እኛ ሙስሊሞች ይህ አሳብ በፍጹም ተግባራዊ መሆን እንደማይችል ጠንቅቀን እናውቃለን። ከዚህ ተቃራኒ በሆነው መልኩ ደግሞ፣ ቁርአንም ሆነ እስላማዊው ሕግ ከጠላቶቻችን ጋር እንዴት መዋጋት እንዳለብን፣ ለጠላታችን ምን ዐይነት አመለካከት ሊኖረን እንደሚገባ፣ ሥርዐቱን በጠበቀ መንገድ እንዴት ፍቺ መፈጸም እንዳለብን ይነግሩናል። እስልምና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ትምህርት ስላለው፣ ዓለም ዐቀፋዊ ለሆነው እስላማዊ ሕግ መገዛት ይቻላል"።

በክርስትና ያለው ትልቁ ተቃርኖ፣ "እናንተ ክርስቲያኖች በአንደበታችሁ ኢየሱስ ጌታ ነው ብትሉም እንኳ፣ የኢየሱስን መርሕ በሕይወታችሁ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ እንደ ሆነባችሁ ሕይወታችሁ ራሱ ይመሰክርባችኋል። በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ የእስልምናን አስተምህሮ ተግባራዊ በማድረግ፣ የኢየሱስን አስተምህሮ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ጕዳይ መሆኑን ማሳየታችሁ አልቀረም። ስለዚህም ሕይወታችሁን በተለያየ መደብ በመከፋፈል ሲመቻችሁ ለኢየሱስ በመታዘዝ፣ ሳይመቻችሁ ደግሞ ኢየሱስን በመቃረን በተቃርኖ የተሞላ ሕይወት መኖር ግድ ሆኖባችኋል። የተቃረነ ሕይወት በመኖር የክርስትናን አንድነት (ቶውሂድ) ጥሳችኋል።



ይህ ከአሕመድ ጋር ከረጅም ዓመታት በፊት በናይሮቢ ስለ ሥላሴ በተነጋገርንበት ወቅት አሕመድን ካሳሰበው ጕዳይ ጋር ይመሳሰላል። በአሁኑ ጊዜ አሕመድ በአሜሪካን አገር፣ በዋሽንግተን ዲሲ የታክሲ ሹፌር ሲሆን፣ የኢትዮጵያውያኑ እንጀራና ወጥ ወደሚገኝበት ምግብ ቤት በመውሰድ እንጀራ በወጥ እየጋበዘኝ፣ "ክርስቲያኖች ኢየሱስ ጌታ ነው ይላሉ። ሆኖም የኢየሱስን አስተምህሮ የሚከተል አንድም ክርስቲያን አላገኘሁም። መሲሑ ኢየሱስን የሚታዘዙት ሲመቻቸው ብቻ ነው። ሆኖም በአብዛኛው ክርስቲያኖች ኢየሱስን ቢከተሉት ኖሮ ይህቺ አገር በአስደናቂ መንገድ ትለወጥ ነበር። ዐልፎ ተርፎ የአሜሪካን ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ስፍራ ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች ታላቅ በረከት ትሆን ነበር" አለ።

እዚህ አሜሪካ ከመገናኘታችን ከረጅም ዓመታት በፊት አሕመድ በናይሮቢ ኢስትሌይ ወደሚገኘው ቤቴ ለመግባት የውጪውን በር አንኳክቶ ሲገባ፣ ያሳሰበውና ያስጨነቀው የነበረው የቶውሂድ አስተምህሮ ነበር። ይኸውም የቶውሂድ አስተምህሮ ከሥላሴ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጣረስ ስለመሰለው ነበር። ዛሬ ግን አሕመድ እኛ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ለመከተል ቍርጠኛና ጽኑ ውሳኔ ማድረግ እንደሚገባን አበክሮ እየጠየቀኝ ነው፣ "የመሲሑ ሕግ ፍቅር ከሆነ በዚያ መንገድ ኑሩ! መሲሑ ሰዎችን ሁሉ እንደሚያፈቅር ሰዎችን ሁሉ የሚወድ ክርስቲያን በእርግጥ ዓለምን ማሸነፍ እንዲሁም የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ መማረክ ይችላል"።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*

ማቴዎስ 28፥18-20፤

*የቁርአን ምንባብ*

ሱራ 30፥30-32፤ 42፥13-15

## የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በትምህርተ ሥላሴ እንዲሁም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው በሚለው አስተምህሮ ላይ ያለው የተሳሳተ ግንዛቤ የመጣው፣ የክርስትናን መሠረተ እምነት በተሳሳተ መንገድ መረዳት እንዲሁም በክርስትና አስተምህሮ ላይ በተፈጠረ የተዛባ ምልከታ ምክንያት ነው በሚለው ጕዳይ ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ (ሱራ 5፥75 ፤ 6፥100-101)።

2. ክርስቲያኖች መሲሑ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ ለሙስሊም ጓደኞቻቸው እንዴት ማስረዳት ይችላሉ (ዮሐንስ 1+1:14፤ ሱራ 4+171)?
3. ተውሂድ (የእግዚአብሔር አሐድነት) የኢራንን አብዮት በመሳሰሉ የሙስሊም የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽእኖ ማሳደር የቻለው በምን ዐይነት መንገዶች ነው?
4. አብዛኛውን ጊዜ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ፣ "የኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት በምንኖርባት በዚህች ዓለም ውስጥ በፍጹም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም በሚለው ሐሳብ ላይ፣ ክርስቲያኖች ራሳቸው ከሙስሊሞች አስተሳሰብ ጋር ይስማማሉ" የሚል አስተያየት ይሰጣል:: በዚህ ጉዳይ ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ::
5. ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደ ሆነ ሁሉ በምድርም እንዲሆን ይጸልያሉ:: ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ የተለያየ አስተያየት አላት:: በአንጻሩ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ግን ይህ ዐይነቱ ልዩነት አይስተዋልም:: ለምሳሌ የሙስሊሞች ጸሎት ሁሉ አንድ ዐይነት ነው:: ይህን ጉዳይ ያብራሩ::
6. "እግዚአብሔር በሥላሴነቱ ሚስዮናዊ አምላክ ነው" በሚለው ሐሳብ ላይ አስተያየት ይስጡ::



ምዕራፍ ዐሥር አንድ

# ሃይማኖታዊ ጉዞ

## ሃጅ—የጌታ ራት

ዩሱፍ የግልፍተኛነት ጠባይ አለበት:: በሚኖርበት ከተማ የሠራተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ነው:: እኔ ዳይሬክተር በነበርሁበት ትምህርት ቤት፣ ከሚገኙ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን ወደ እርሱ ቢሮ መሄድ ባሰብን ቍጥር ሁሉ፣ ጭንቀት ይሰማናል:: ምክንያቱም የዩሱፍ ምላሽ እንደ አለብላቢት ይፋጃል::

በከተማው ወሬ አቀባዮች አማካይነት ዩሱፍ ለሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ መካ የመሄድ ዕቅድ እንዳለው የሚገልጽ መልካም ዜና፣ በከተማው በአንዴ ተናፈሰ::

የሙያተኞች ተቈጣጣሪ/አለቃ የሆነው ፋራህ እንደ ነገረኝ፣ "ዩሱፍ ከሃይማኖታዊው ጉዞ ሲመለስ አዲስ ስም ይኖረዋል—ሃጂ ዩሱፍ ይባላል:: አዲስ ጠባይ ይኖረዋል:: ዩሱፍ የተለወጠ ጠባይና አዲስ ስም ስለሚኖረው የከተማዋ ሕዝብ በሙሉ በትልቅ ደስታ ውስጥ ነው ያለው"::

ዩሱፍ ከሃይማኖታዊ ጉዞ የተመለሰው፣ አዲሱን የሃጂነት ማዕረግ ከተገቢው ክብር ጋር ተጐናጽፎ ነው:: ግልፍተኝነቱን አስመልክቶ ቅጽበታዊ ለውጥ ማምጣቱ ባይረጋገጥም፣ በሂደትም እንኳ ቢሆን የጠባይ ለውጥ እንደሚያመጣ የከተማዋ ነዋሪዎች ትልቅ ተስፋ አላቸው::

### የእምነትና የምግባር አዕማድ

ዩሱፍ ያደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ (ሐጅ) በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ከሚገኙት አምስት የእምነትና የምግባር አዕማድ ውስጥ አንዱ ነው:: እነዚህ አምስት የእስልምና ሃይማኖት አዕማድ የሚከተሉት ናቸው:— (1) የእምነት ማረጋገጫ (*ሻሃዳ*—" ይኸውም ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፣ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው":: (2) በአምልኮና በሃይማኖታዊ ጸሎት (*ሰላት*) ለእግዚአብሔር መገዛት (3) ለድኾች መመጽወት (*ዘካት*) (4) በረመዳን ወር መጾም (*ሳውም*) (5) ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ (*ሃጂ*) ናቸው::

አንዳንድ የሙስሊም ማኅበረሰብ እንዲሁም አንዳንድ የሙስሊም ነገረ መለኮት ሰዎች፣ ሃይማኖቱን ከጥቃት ለመከላከል በሃይማኖት ጦርነት ውስጥ መሳተፍን (ጂሃድን) የሃይማኖቱ ስድስተኛ ዐምድ ያደርጉታል[1]:: እነዚህ የሃይማኖቱ አዕማድ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ:: እነዚህ ምግባራት በቁርአን ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ ሲባል ግን፣ በእያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ ላይ ቁርአን ትምህርት አለው ማለት ሳይሆን፣ መሐመድ ለእነዚህ ተግባራት ምሳሌ ሆነው ስላለፉ እርሳቸው ያደረጉትን ነገር ማድረግ በሃይማኖቱ ትልቅ ስፍራ እስከ ተሰጠው ድረስ፣ እነዚህ ጉዳዮች ቁርአናዊ መሠረት አላቸው ማለት ይቻላል:: እነዚህ የሃይማኖቱ ምግባራትና ኀላፊነቶች፣ በሙስሊማኑ የሃይማኖት እንቅስቃሴ የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የራሳቸው የሆነ ዕድገት አሳይተዋል[2]:: ይህ ምዕራፍ አምስተኛውን ዐምድ ማለትም ሃይማኖታዊውን ጉዞ (*ሃጂን*) በስፋት ለመመልከት ይሞክራል::

## ወደ መካ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጉዞ

በየዓመቱ መካ ወደሚገኘው ወደ ካዕባ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዞ ያደርጋሉ:: ይህን ጉዞ ያደረጉ ሰዎችም የአዲስ ስም ባለቤት ይሆናሉ:: በምሥራቅ አፍሪካ ይህ አዲስ ስም ለወንዶች ሃጂ ሲሆን ለሴቶች ደግሞ ሃጂያ ነው:: በ1930ዎቹ በየዓመቱ አንድ መቶ ሺህ የሚጠጉ የእስልምና የሃይማኖት ተጓዦች ወደ መካ ይሄዱ ነበር:: ዛሬ ግን ከአምስት እስከ ዘጠኝ ቀን ለሚፈጀው ለዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞ፣ ሦስት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጉዞ ያደርጋሉ:: በደሁ-አል-ሂጃህ ወር፣ በዘጠነኛው ቀን የሚጀምረው ሃይማኖታዊ ጉዞ፣ በተለያየ ምክንያት በምድር ላይ ከሚደረጉ ስብሰባዎች በላይ እጅግ ብዙ ሕዝብ የሚሰበሰብበት ክብረ በዓል ሆኖአል::

አዳዲሶቹ ሃጂዎችና ሃጂያዎች (የሃይማኖት ተጓዦቹ) ወደ ቀዬአቸው ሲመለሱ፣ በሚናገሩባቸው በብዙ መቶዎች በሚቈጠሩ ቋንቋዎቻቸው፣ በመካ ያዩትንና ያጋጠማቸውን ነገር ሁሉ ይተርካሉ:: የሃጂዎቹንና ሃጂያዎቹን ትረካ በንቃት ሲከተተሉ የነበሩ ትናንሽ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ አንድ ቀን እኔም ሃይማኖታዊውን ጉዞ አደርጋለሁ የሚል ትልቅ ፍላጎት ያድርባቸዋል::

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 97-98.

[2] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 66-67.



ሃይማኖታዊውን ጉዞ እንዲያካሂዱ የሚጠበቅባቸው ወጪያቸውን መሸፈን የሚችሉ ሰዎች ብቻ ናቸው:: ይሁን እንጂ የእስልምና ሃይማኖት የነገረ መለኮት ምሁር የሆኑት ሙሐመድ ሃሚዱላህ እንዲህ ይላሉ:—

> ሆኖም የትኛው ሙስሊም ነው የሃይማኖቱ መሠረት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቤት ለረጅም ጊዜ እንኳ ቢሆን ገንዘብ አጠራቅሞ አንድ ቀን ካዕባን እጎበኛለሁ የማይል? ቁርአን (ሱራ 3+96) ይህን ስፍራ፣ የሰው ልጆች ለእግዚአብሔር ያበረከቱት ጥንታዊ የአምላክ ቤት እንዲሁም አሐዳዊው አምልኮ የሚካሄድበት ስፍራ ማለቱ አንዳችም ግነት የለበትም:: እስላማዊውን ትውፊት ተከትለን አብርሃምን ብቻ እንኳ ብናስብ፣ አብርሃም አዳም በመጀመሪያ ያቆመውን ሕንፃ መልሶ ያደሰና የጠገነ ሰው መሆኑን እንረዳለን:: ይህም ሕንፃ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ከገነባው ቤተ መቅደስ እንኳ ይልቅ ቀዳሚ ነው[3]::

ዘጠኝ ቀን በሚፈጀው በዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞ ላይ ለአፍታም እንኳ ቢሆን፣ ትኵረት እናድርግ:: ይህ ጉዞ የእስልምናን መሠረተ እምነት ፍንትው አድርጎ ያሳያልና::

## መካ መድረስ

ወንድ የሆኑ የሃይማኖት ተጓዦች ሁሉ፣ *ኢህራም* (ሁለት ክፍል ያለው ነጭ የሥርዐተ አምልኮ ልብስ) ይለብሳሉ:: ሁሉም ሙስሊም ይህን ልብስ በወጥነት መልበሱ፣ ሙስሊሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆናቸውን ያመላክት ዘንድ ነው:: ኢህራም ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥቻለሁ የሚለውንም ሐሳብ ይወክላል:: የሃይማኖት ተጓዦቹ መካ ከመድረሳቸው በፊት፣ በኢህራም መንፈስ ውስጥ ገብቶ መገኘት ይጠበቅባቸዋል:: እነዚህ የሃይማኖት ተጓዦች በሚሄዱባቸው መንገዶች ላይ፣ ሙስሊም ያልሆነ ሰው በእነዚህ መንገዶች ዐልፎ ወደ መካ እንዳይቀርብ የሚከለክሉ ምልክቶች በየመንገድ ዳሩ ተለጥፈዋል:: ይህም የሙስሊሙ ኡማ በምድር ላይ ከሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ይልቅ፣ እጅግ የተለየ መሆኑን አመላካች እንደ ሆነ ይታመናል::

የሃይማኖት ተጓዦቹ ሁሉ፣ ጂዳ ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ከጂዳ በ45 ማይል ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ መካ ጉዞ ይጀምራሉ:: ወደ መካም እየተጓዙ ሳለ፣ *ታልቢያ* በመባል የሚታወቀውን ጸሎት ደጋግመው ይጸልያሉ:—

[3] Muhammad Hamidullah, *Introduction to Islam* (Paris: Centre Culturel Islamique, 1969), 64.

አምላኬ አንተ እንዳዘዝኸው እዚህ ተገኝቻለሁ፤ እነሆ በፊትህ ነኝ፤
አንተ አቻና እኩያ የለህም፤
አንተ ጸጋና ምስጋና ግዛትም ይገባሃል፤
አንተ አቻና እኩያ የለህም፤
እነሆኝ በፊትህ ነኝ![4]

## ካዕባ (የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት)

የሃይማኖት ተጓዧች ሁሉ መካ ሲደርሱ ወደ መስጂድ-አል-ሃራም ይገባሉ። ይህ መስጊድ አምስት መቶ ሺህ ሰዎችን የማስተናገድ ዐቅም አለው። ካዕባም በተቀደሰው በዚህ መስጊድ መኻል ቆሞአል። ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ስፍራው አዳም በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር አምልኮ ያቀረበበት ስፍራ ነው። ካዕባ የእግዚአብሔር ቤት ይሆን ዘንድ በመጀመሪያ አዳም ያነጸው ቤት ሲሆን፣ ኋላም አብርሃምና እስማኤል ደጋግመው ያደሱት ቤት ነው። መሐመድ ነቢያዊ ስብከታቸውን ሲጀምሩ 360 አማልክትን ደምስሰው ካዕባን ከጣዖታት አጽድተዋል። መሐመድ የጣዖት አምላኪዎችን ጣዖት ብቻ አይደለም ያወደሙት፣ ነገር ግን ከእነዚህ አምልኮተ ጣዖታት ጋር ተያይዞ ይካሄዱ የነበሩ ሥርዐተ አምልኮዎችን፣ ለምሳሌ የሴት ሕፃናት ግድያ ኢፍትሓዊ መሆኑን ተቃውመው ሰብከዋል[5]።

በካዕባ ግድግዳ ውስጥ የተቀደሰ ጥቁር ድንጋይ አለ። ይህ ድንጋይ አዳምና ሔዋን ከገነት ወደ ምድር ሲወርዱ፣ ከሰማይ የወረደ እንደ ሆነ በሙስሊሞች ይታመናል። በአንድ ወቅት ጠፍቶና ተዘንግቶ የነበረው ይህ ድንጋይ፣ አብርሃምና እስማኤል በተአምር አግኝተውት፣ የእግዚአብሔርን ቤት ሲያድሱ በካዕባ ግድግዳ ላይ እንዳስቀመጡት ይታመናል።

መሐመድ ከመሞታቸው በፊት ባካሄዱትና ስንብታዊ በሆነው ሃይማኖታዊ ጉዞአቸው፣ ይህንን ድንጋይ እንደ ሳሙ ይነገራል። የሃይማኖት ተጓዦች ሁሉ የእርሳቸውን ፈለግ በመከተል፣ ካዕባን የሚዞሩት ይህን ድንጋይ በመሳለም ወይም እርሱን በመመልከት ነው። ካዕባን የሚዞሩት ሰዓት በሚዞርበት ተቃራኒ አቅጣጫ ስለሆነ፣ ድንጋዩና ካዕባ በዧሪዎቹ በስተግራ በኩል ይሆናል። ሥርዐተ

[4] Mohamed Amin, *Pilgrimage to Mecca* (Nairobi, Kenya: Camerapix, 1978), 20.
[5] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Hearald Press, 1997), 69.



ሃይማኖቱና አምልኮው ቅንጣት ታህል ዝንፍ የማይሉና በዝርዝር የተቀመጡ ናቸው። የሃይማኖት ተጓዧቹ ካዕባን የሚዞሩት ሰባት ጊዜ ነው።

ሙሐመድ ሃሚዱላህ በእስልምና የጥቁሩን ድንጋይና የካዕባን አገልግሎት እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ:—

> በሐዲስ (በትውፊት) ነቢዩ ጥቁሩን ድንጋይ፣ "የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ" (ያሚን አላህ) ብለው ሰይመውታል፤ ይህም ምክንያት አለው። አንድ ሰው ጉዞውን ማጠናቀቁን እንዲሁም በታማኝነትና በትሕትና መገዛቱን ለማሳየት እጁን በድንጋዩ ላይ ያኖራል፤ በዚህ መንገድ እግዚአብሔር የእኛን መገዛትና ለእርሱ ያለንን ታማኝነት ይቀበላል። በቁርአን አገላለጽ እግዚአብሔር ንጉሥ ነው፤ በእርሱ ግዛትም ውስጥ ትልቅ ከተማ (እማል ቁራ) አለ፤ በዚህም እማል ቁራ ቤተ መንግሥት አለ፤ በዚህም ቤተ መንግሥት ውስጥ እግዚአብሔር ይኖራል (ቤት-አላህ)። ታማኝነቱ እንዲመሰከርለት የተፈለገ ሰው ወደ ንጉሡ መኖሪያ ቀርቦ ታማኝነቱንና መገዛቱን መግለጽ አለበት። በዚህም ጊዜ የማይታየው የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ይታያል። ይህም (አል ሃጃር አል-አስዋድ) በካዕባ ላይ ያለው ጥቁር ድንጋይ ነው[6]።

በእስልምና ይህ ሃይማኖታዊ ጉዞ እጅግ ወደ ተቀደሰ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ ነው። ሙስሊሞች እንደሚያምኑት የመጀመሪያዎቹ፣ መካከለኞቹና የመጨረሻዎቹ የእስላም ነቢያት አዳም፣ አብርሃምና መሐመድ በካዕባ ልዩ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን መገለጥ አግኝተዋል። ለሙስሊሞች ወደዚህ ወደ ተቀደሰ ስፍራ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ ሙሉ ምልክት ነው። ካዕባ ጥቁር ድንጋይ ያለበት ሕንፃ ብቻ አይደለም። የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች ለአላህ በመገዛት የሰገዱበትና አላህን ያመለኩበት የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት እንዲሁም የምድር ዕምብርት ነው።

## የአጋር፣ ኡስማኤልና የአብርሃም ፋና

ሙስሊሞች የሃጂን ጉዞ የአብርሃምን ጉዞ እንደ መድገም ይቈጥሩታል። ሃይማኖታዊ ተጓዦቹ በአብርሃም ክልል ውስጥ ጸሎት ያደርሳሉ። ከዚያም ወደ ዘምዘም ምንጭ ይጓዛሉ። ይህ መልአኩ ገብርኤል ለአጋርና ለእስማኤል ተኣምራዊ በሆነ መንገድ ውሃን ያቀረበበት ስፍራ ነው። ይህም ውሃ በምድር ላይ ካሉት ውሆች ሁሉ ይልቅ ንጹሕ እንደ ሆነ ይታመናል። የሃይማኖት

[6] Hamidullah, *Introduction to Islam*, 66.

ተጓዦቹ ጥማቸውን ለመቁረጥ ብቻ ሳይሆን፣ ሃይማኖታዊ መንጻት ይሆናቸው ዘንድ ይታጠቡበታል።

ከምንጩ በቅርብ ርቀት ላይ ወደሚገኙት መንትያ ዳገቶች ወደ አል-ሳፋና አል-መረዋ ይጓዛሉ። በእነዚህ ዳገቶች መካከል አጋር በውሃ ጥም ወደ ሞት ለተቃረበው ልጇ እየጸለየች የተጓዘችበትን መከራዋን በማሰብ በአካባቢው ይዘዋወራሉ።

## የመሐመድ የመጨረሻው ሃይማኖታዊ ጉዞ

የሃይማኖት ተጓዦች ከመካ ዐሥር ማይል ርቆ ወደሚገኘው ወደ አረፋት ሜዳ ይጓዛሉ። በሜዳው መኻል መሐመድ ለመጨረሻ ጊዜ ለአንድ መቶ ሺህ አማኞች የሰበኩበት የምሕረት ተራራ አለ። በዚህ መልእክትም የሃይማኖታዊ ጉዞን ሕግ ደነገጉ።

ሙስሊሞች በተራራው ላይ ሲሰባሰቡ መሐመድ በመጨረሻ የሃይማኖት ጉዞቸው ወቅት የሰበኩትን ዐይነት ስብከት ይሰማሉ። ይህ ተራራ አዳም ከእግዚአብሔር ምሕረትንና ምሪትን የጠየቀበት ስፍራ ነው።

ይህ ከዓለም ዙሪያ ከሁለት እስከ ሦስት ሚሊዮን ሕዝብ የተሰበሰበበት ስፍራ፣ ለሃይማኖታዊ ጉዞው እጅግ የከበረው ስፍራ ነው። አንድ ወቅት ላይ አዳምና መሐመድ ቆመውበት በነበረው በምሕረት ተራራ ሰባኪው ይቆማል። ሕዝቡ በአንድነት እንደ አንድ ሕዝብ እጅብ ብሎ በመቆም የእግዚአብሔር ቃል ሲታወጅ ያዳምጣል፤ ይህም ዐዋጅ፦ "እግዚአብሔር አቻና እኩያ የሌለው ብቸኛ አምላክ ነው፤ አንዱ ሙስሊም ከሌላው ሙስሊም ጋር እኩል ነው" የሚል ነው።

## የእስማኤል መታሰቢያ

የሃይማኖት ተጓዦቹ ጥቂት ዕረፍት ወስደው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሚና ወደ ተባሉ አጋንንትን የሚወክሉ ሦስት የድንጋይ አዕማድ ወደ ቆሙበት ስፍራ ይጓዛሉ። እነዚህ የድንጋይ አዕማድ የቆሙት ሰይጣን፣ አብርሃም ልጁ እስማኤልን እንዳይሠዋ ለማሳመን የሞከረውን ሙከራ ለማሰብ ነው። የሃይማኖት ተጓዦቹ በሰይጣንና በሽንገላ ዘዴው ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለጽ በሚና በሚገኙት ሃውልቶች ላይ ጠጠር ይወረውራሉ።



በሚና ከሚደረገው የጠጠር ውርወራ በኋላ የሃይማኖት ተጓዦቹ የኢህራም ልብሳቸውን አውልቀው እንደ ባህላቸው ያሻቸውን ልብስ ይለብሳሉ። ከዚህ በኋላ የክብረ በዓል ጊዜ ይሆናል። ሌሊት ለመሥዋዕትና ለድግስ የሚሆኑ በጎችና ግመሎች እንዲሁም ሌሎች እንስሳት ይገዛሉ። እነዚህ እንስሳት የመሠዋታቸው ዐቢይ ዐላማ፣ እግዚአብሔር በምትኩ በግን አዘጋጅቶ የእስማኤልን ሕይወት ከመሥዋዕትነት ማትረፉን ለማሰብ ነው።

በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች በዚህች ምሽት በሚካሄደው በመሥዋዕቱና በድግሱ ክብረ በዓል ላይ ይሳተፋሉ። በሙስሊሙ ግዛት የታቀፉ ሕዝቦች በዚህ መሥዋዕት የማቅረብ ክብረ በዓል ላይ (ኢድ አል-አድሃ) ይሳተፋሉ። ይህ አራት ቀን የሚፈጀው ክብረ በዓል በሐጂ መዝጊያ ወር (ዱሀል-ሂዳ) በዐሥረኛው ቀን ላይ ይጀምራል። ሁሉም ሙስሊሞች አብርሃምንና እስማኤልን፣ በችግሮች ሁሉ ውስጥ ጸንተው እምነታቸውን ለመሐመድና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ በማስተላለፍ እንዲሁም እምነትና ምግባርን መመሥረት ያስቻሉ ነቢያት እንደ ሆኑ በመቁጠር በአክብሮት ያስቡአቸዋል። ምትክ ሆኖ በቀረበው መሥዋዕት የእስማኤል ሕይወት ብቻ አይደለም የተረፈው ነገር ግን የእስልምና እምነት መሠረትም ተጠብቋል፤ ለሚቀጥለው ትውልድም ተላልፏል። ስጦታዎች ይሰጣሉ፤ ለድኾችም ምግብ ይዘጋጃል።

የሃይማኖት ተጓዦቹ የጉዞ ፍጻሜ ወደ መካ ተመልሶ ካዕባን ለመጨረሻ ጊዜ መጎብኘት ነው። ብዙ ተጓዦች ቆይታቸውን በማራዘም መዲናን ይጎበኛሉ። ይህ ተጨማሪ ጉዞ ለእምነት መታነጽ የሚረዳ ቢሆንም፣ ሃይማኖታዊ ተጓዥ ማሟላት ያለበት ግዴታ አይደለም።

## የሃይማኖታዊው ጉዞ ነገረ መለኮት

ትልልቅ የሆኑ የነገረ መለኮት ሐሳቦች በሃይማኖታዊ ጉዞው ላይ ተሳስረዋል። ሃይማኖታዊ የሥነ ሰብ ጥናት ተመራማሪዎች በብዙ እምነቶች፣ "የምድርን እንብርት" የሚወክል ስፍራ አለ የሚል እምነት እንዳላቸው ያስረዳሉ። ይህ የምድር ማዕከል/እንብርት መለኮትንና ሰውን እንዲሁም ሰማይንና ምድርን የሚያገናኝ ስፍራ እንደ ሆነ ይታመናል። በእስልምና ይህ ስፍራ ካዕባ ነው።

በካዕባ የሚገኘው ጥቁር ድንጋይ ለአዳምና ለሰው ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው። በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ግንኙነትንና የሰዎችን አንድነት የሚወክል ነው። እግዚአብሔር እስልምናን ለሁሉም ሕዝቦች ምሕረት አድርጉ እንደ ላከው የሚያሳይ ተምሳሌትም ነው።

ድንጋዩ ነቢያትን፣ አዳምን፣ አብርሃምንና መሐመድን እንዲሁም ይህን ድንጋይ በትልቅ አክብሮት የሚያዩት ሰዎች ሁሉ አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ድንጋዩ ተአምራዊ መገለጥን የሚያመላክትና ለአዳም የተላከለት ድንጋይም ነው። ይህ ድንጋይ በአሸዋ ውስጥ ተቀብሮ ጠፍቶ ነበር። ተአምራዊ በሆነ መንገድ አብርሃምና እስማኤል ድንጋዩን እንዳገኙትና ለዘላለም በእግዚአብሔር ቀደምት ቤት በካዕባ እንደ ተቀመጠ ሙስሊሞች ሁሉ ያምናሉ።

የአብርሃም፣ የአጋርና የእስማኤል ታሪክ በሃይማኖት ጉዞው ውስጥ ሁሉን የሚያስርና ለሁሉ ቅርጽ የሚሰጥ ርእስ ጉዳይ ነው። መሐመድ ለመጨረሻ ጊዜ ያካሄዱት ሃይማኖታዊ ጉዞና ለመጨረሻ ጊዜ በአረፋት ሜዳ፣ በምሕረት ተራራ የሰበኩትም ስብከት በዚህ መልክ የሚታሰብ ነው። የአዳምም ድርሻ በዚህ ሥዕል ውስጥ ትልቅ ሚና አለው። ሃይማኖታዊው ጉዞ ሙስሊሞች ከሁሉም የእግዚአብሔር ነቢያትና ሕዝቦች ጋር በዘመናት መካከል ያለውን አንድነት በግልጽ ቋንቋ የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም ሙስሊሞች ለእስልምና ሃይማኖት ከማይገዙ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ያላቸውን ልዩነት አመልካች ነው።

የመሥዋዕቱ ክብረ በዓል ትልቅ ትኩረት የሚፈልግ ነው። ሃይማኖታዊው ጉዞ በሙስሊሙ ሕዝብ ሕይወት ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለእስማኤልና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ምትክ ይሆን ዘንድ የበግ መሥዋዕት አቅርቦ የታደገበት የደስታ መታሰቢያ በዓል ነው። ይህ በሙስሊም ልቦና የተሰወረ ምሥጢር ነው። በአብርሃም ልጅ ምትክ የተሠዋው በግ ምን ትርጉም የሚወክል ነው?

## ስአብርሃም ልጅ ትኪ ሆኖ የቀረበው በግ ምን ትርጉም ይወክሳል?

ከኢየሩሳሌም ቅጥር ውጪ ጐልጐታ በተባለው ኩረብታ የተሠዋውን ሌላውን መሥዋዕት፣ ሙስሊሞች እንዲያስተውሉት ክርስቲያኖች ጥሪ ያቀርባሉ። ክርስቲያኖች ይህ ስፍራ ኢየሱስ ተሠውቶበት የነበረው ስፋራ ነው የሚል እምነት አላቸው። የእግዚአብሔር በግ ተብሎ የሚጠራው መሲሑ፣ አብርሃም በልጁ ምትክ የሠዋው በግ ምስጢራዊ ፍጻሜ አይደለምን?



በረመዳን የጾም ወር ወቅት በፊላደልፊያ መስጊድ ውስጥ ከክርስቲያኖች ጋር ይወያዩ ለነበሩ ሙስሊሞች ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ጸሎቱ ለሁለት ሰዓት ተካሂዶ ስለነበር ለውይይት የተሰበሰብነው ከምሽቱ አራት ሰዓት ገደማ ላይ ነበር።

ኢማሙ፣ "በዛሬ ምሽት ተጨማሪ ጸሎት እንዳሳረግን (እንዳቀረብን) አስተውላችኋልን? በረመዳን የጾም ወር በየምሽቱ ሁለት ተጨማሪ ሰዓት እንጸልያለን። እነዚህ ተጨማሪ የጸሎት ሰዓቶች ለኀጢአታችን ማካካሻ ሊሆኑን እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን" አለ። አንዱ ክርስቲያን እንዲህ ብሎ ጠየቀ፣ "ኀጢአታችሁን ሙሉ ለሙሉ ሊያካክስ የሚችል በቂ ጸሎት ጸለያችሁን?"

"ስለዚያ የምናውቀው አንዳች ነገር የለም" ሲል ኢማሙ መልስ ሰጠ። እኛም እንዲህ አልን፣ "በሙሴ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለኀጢአት መሥዋዕት የእንስሳት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ታዞአል። እነዚህ መሥዋዕቶች ምንድን ናቸው? ለአብርሃም ልጅ ትኪ ሆኖ የተሠዋው በግ በስተጀርባ ያለው ምሳሌ ትርጉሙ ምንድን ነው? ከመሲሑ ኢየሱስ ስሞች መካከል አንዱ የእግዚአብሔር በግ ነው። ይህ ማለት ደግሞ መሲሑ በእኛ ምትክ በመስቀል ላይ የመሥዋዕትነት ሞት ሞቶአል። በሙሴ ሕግ ይደረግ የነበረው መሥዋዕት በመጨረሻ ወደ መሲሑ መሥዋዕታዊ ሞት አመልካች እንደ ሆነ አዲስ ኪዳን ይገልጻል። እርሱ የእኛን መከራ ወሰደ። እኛም ምሕረትን (ይቅርታን) አገኘን"።

"ይህ ሊሆን አይችልም። እያንዳንዱ ሰው የራሱን የኀጢአት ውጤት መሸከም አለበት። ፈራጁ ፍርድን ሲያሰማ በደለኛ ሰው የኀጢአቱን ዋጋ መክፈል አለበት" በማለት ተቃወመ።

እኛም "እውነት ነው" ብለን ተስማማን። "ሆኖም ፈራጁ ራሱ ከፍርድ ዙፋኑ ላይ ወርዶ በአንተ ስፍራ እኔ እሆናለሁ፤ አንተ ነጻ ነህ ብሎ ቢልስ። ኢየሱስ ቤዛ ሆነን ማለት ይህ ነው። እግዚአብሔር መሲሑን ልኮ ችሎት በመሰየም የእኛን ስፍራ በመውሰድ ተቤዠን"። ውድ ስለሆነው የይቅርታ ስጦታና እግዚአብሔር በመሲሑ የሰጠውን መቤዠት በማሰብ በዚያች ምሽት በመስጊድ ውስጥ ለአጭር ደቂቃ የአክብሮት ዝምታ ሰፈነ።

## እግዚአብሔር መሐሪው አማላጅ

መቤዠት (መዋጀት) የወንጌል ዋናው ክፍል ሲሆን፣ ለሙስሊም ነገረ መለኮት ግን መቤዠት ማዕከላዊ አስተምህሮ አይደለም:: ይሁንና በእስልምናም ቢሆን እግዚአብሔር የሚዋጅ አምላክ መሆኑን የሚጠቁሙ ፍንጮች አሉ:: የሚያስገርመው ነገር እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ምትክ ይሆን ዘንድ ያዘጋጀው በግን ነው:: እግዚአብሔር ራሱ አማላጅ እንደ ሆነ በቁርአን ውስጥ ማረጋገጫ እናገኛለን :—

> "አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ በዚያም በዐርሹ ላይ (ሥልጣኑ) የተደላደለ ነው፤ ከእርሱ ሌላ በእናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም አትገሠጹምን?" (ሱራ 32+4)

በሌላ ስፍራ ደግሞ:—

> "እነዚያም በተአምራታችን የሚያምኑት በመጡብህ ጊዜ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፤ ጌታችሁ በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ፤ እነሆ ከእናንተ ውስጥ በስሕተት ክፉን ሥራ የሠራ ሰው ከዚያም ከእርሱ በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ እርሱ (አላህ) መሐሪ አዛኝ ነው በላቸው" (ሱራ 6+54)::

ይህ የመጨረሻው የቁርአን ክፍል በእጅጉ ከወንጌል ጋር ይመሳሰላል:: በቁርአን ውስጥ የምሕረትን ሕግ እግዚአብሔር በራሱ ላይ ደንግጓል:: በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር ጓደኛችንና መሐሪ አማላጃችን እንደ ሆነ ተገልጸአል:: በእስልምና እግዚአብሔር ወደ እርሱ በንስሓ ለሚቀርቡ ምሕረትን ያደርጋል:: ንስሓ ለሚገቡና ለእስልምና ለሚገዙ ኀጢአተኞች ምሕረት አለ፤ እግዚአብሔር በራሱ ምሕረትን ደንግጓል::

እንደነዚህ ያሉት የቁርአን ማስረጃዎች ከወንጌል ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው ጠቀሜታቸው ታላቅ ነው:: ሆኖም በወንጌል ውስጥ መሲሑ ኀጢአተኞችን ሲፈልግና አብሯቸው ሲበላ እናያለን:: ሕይወቱንም ለኀጢአተኞች ሰጥቶአል:: የሃይማኖት መሪዎች ደቀ መዛሙርቱን፣ "መምህራችሁ ከቀራጮችና ከኀጢአተኞች ጋር አብሮ ስለ ምን ይበላል? አሉአቸው" (ማቴዎስ 9+11):: ኢየሱስም ሰምቶ፣ "ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኀኒት አያስፈልጋቸውም" ብሎ መለሰላቸው (ማቴዎስ 9+11)::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ አንድ አባትና ስለ ሁለት ልጆቹ ታሪክ የሚናገር ክፍል አለ:: በምሳሌው ውስጥ አባትየው ዐመፀኛውንና የጠፋውን ልጅ በሩቅ



ሲያየው ክብሩን ጥሎ ልጁን ለማቀፍ ሮጠ:: ለጠፋው ልጅ ግብዣን አዘጋጀ:: ይህ አባት ከእርሱ ጋር አብሮ ይኖር የነበረው ልጅ ስለጠፋው ነገር ግን አሁን ስለተገኘው ወንድሙ ፍሥሓ እንዲያደርግ ይለምነዋል (ሉቃስ 15+11-32):: ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ የሚገለጸውን ራሱን አሳልፎ የሰጠበትን ፍቅር ይበልጡኑ ግን በመሲሑ ራሱን የሠዋበትን ፍቅር ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው (ሉቃስ 15+1-7):: እግዚአብሔር በመሲሑ ኀጢአተኞችን ይፈልጋል፤ ወደ እርሱ እንዲመጡም ይጠራል:: ከኀጢአተኞችም ጋር ይበላል:: መሲሑ ኀጢአተኞችን ለመቤዠት ሕይወቱን ሰጥቶአል:: ይህም የመሥዋዕት ግብዣ ወደሚባለው የሙስሊሙ ሐሳብ የሚወስደን ነው::

የዚህ ምሥጢር ትርጒም ምንድን ነው? እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል የገለጠው መሥዋዕታዊና ራስን የመስጠት ፍቅር የተፈጸመበት ምልክት ይሆንን? እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ምትክ የሚሆን በግ በማዘጋጀት በጉ ለልጁ ሞት ምትክ ሆኖአል:: ወንጌል እንደሚያስተምረን መሲሑ በመስቀል ላይ የፈጸመው መሥዋዕታዊ ሞት ለእኛ ምትክ ሆኖአል::

## ሃይማኖታዊ ጉዞ ከመሲሑ ጋር

ሙስሊሞች በዱሉ ሐል ሂጃ እንደሚያደርጉት ክርስቲያኖች አብርሃማዊ የሆነ የሃይማኖት ጉዞን ለመታሰቢያነት በማድረግ ቅዱስ ወደሚባሉ ስፍራዎች አይጓዙም:: ሆኖም እግዚአብሔር ሁሉም የእምነት ክፍሎች እርሱን እንዲከተሉት ጥሪ አቅርቦአል:: ይህም ጥሪ ልክ እንደ አብርሃም የምቾት ስፍራችንንና ቤተሰባችንን ጥለን እግዚአብሔርን በእምነት እንድንከተለው ነው:: ምንም እንኳ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን ሸንጣቸውን ጠቅልለው እርሱን እንዲከተሉት ወይም እርሱ ወደሚመራቸው ስፍራ እንዲሄዱ ጥሪ ቢያቀርብም፣ የሃይማኖታዊ ጉዞ ቀዳማይ ዐላማው እርሱን በፍጹም ልብ መከተል ነው:: ይህም የእግዚአብሔር ጥሪ ፍጹም ታማኝነትን የሚጠይቅ ከሌሎች መሰጠቶች ሁሉ የሚልቅ ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው::

የክርስቲያኖች ዘመን አቈጣጠር ከሙስሊሙ ሃይማኖታዊ ጉዞ ጋር የሚመሳሰሉም ሆነ የሚለያዩ መታሰቢያዎች አሉት:— ክርስቲያኖች ከፋሲካ በፊት ያለውን እሑድ፣ የስቅለትን ቀንና የፋሲካን በዓል በትልቅ ተመስጦ ያስቡታል፤ ነገር ግን ቍም ነገሩን ለማሰብ፣ ሙስሊሞች ወደ መካ እንደሚያደርጉት ዐይነት ጉዞ መጓዝ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት የላቸውም::

## ቤተ መቅደስ (የእግዚአብሔር ቤት)

መሲሑ ኢየሱስ አዘውትሮ ወደ ቤተ መቅደስ ይሄድ ነበር። ዐሥራ ሁለት ዓመት በነበረበት ጊዜ ቤተሰቦቹ በቤተ መቅደስ ባገኙት ጊዜ የተናገረው ቃል፣ በቤተ መቅደስ በመገኘት የተናገረው የመጀመሪያው ቃሉ ነው፣ "እርሱም ስለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው" (ሉቃስ 2፥49)። ኢየሱስ የአይሁድን ሃይማኖት፣ የቤተ መቅደስን ባህል እንዲሁም ልምምድ በማክበር የሚኖር ሰው ነበር[7]።

ይሁን እንጂ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረውን የፍትሕ መጓደልን፣ ግብዝነትንና ሰውን ማዋረድ ክፉኛ ተቃውሞአል። በተጨማሪም የእርሱ መምጣት ቤተ መቅደሱ የሚወክለው እምነት ፍጻሜ ማግኘቱን በተግባር እንደሚያሳይ አስተምሮአል። ይህም እምነቱ ከቤተ መቅደስ ባለሥልጣናት ጋር አጋጭቶታል። ምዕራፍ 8 ከፋሲካ በፊት ስላለው እሑድና ቤተ መቅደሱን ስለ ማጽዳት ማብራሪያ ይሰጣል። ምዕራፍ 9 ደግሞ በኢየሱስና በመቅደስ ልግድ መካከል የፈጠረው ልዩነት ያስከተለውን ጠንካራ ግጭት ይተርካል።

በአይሁዶች ነገረ መለኮት መሠረት ቤተ መቅደሱ እንደ እግዚአብሔር መኖሪያ ተደርጐ ይቈጠር ነበር። ንጉሥ ሰሎሞን የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ሞላው (2ዜና 6፥17:10)። ይህ ቤተ መቅደስ 586 ዓ.ቅ.ክ በባቢሎናውያን ወራሪዎች ተደምስሶአል። ዳግመኛም ቤተ መቅደሱ በዘሩባቤል መሪነት በ515 ዓ.ቅ.ክ ታንጾ ተመርቋል። ከመሲሑ በፊትና በመሲሑ ጊዜ ቤተ መቅደሱ ዋና የሚባል ዕድሳት ተደርጐለታል። በየክፍለ ዘመናቱም እስራኤላውያን የአይሁድ በዓላትን ለመዘከር መደበኛ የሆነ የሃይማኖት ጉዞ ያደርጉ ነበር። በኢየሱስ ዘመን ቤተ መቅደስን አለቅጥ ትልቅ ዋጋ የመስጠትና የማምለክ አባዜ ተስፋፍቶ ነበር። ለብዙ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ቤት ጉዳይ ወጥመድ እንዲሁም ከፍ ያለ ዋጋ በማስከፈል ወደ ስሕተት የሚመራ ጉዳይ ነበር[8]። ኢየሱስም ወደ መቅደሱ ገብቶ ብልሹ የሆኑ ነጋዴዎችን እንዲህ ሲል ገሥጾአቸዋል:— "ይህን ከዚህ ውሰዱ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት"

[7] E. P. Sanders, *The Historical Figure of Jesus* (London: The Penguin Press, 1995), 33-48.

[8] Donald B. Kraybill, *The Upside-Down Kingdom* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1978), 65-94.



(ዮሐንስ 2፥16)። ከስድስት ምዕተ ዓመት በኋላ፣ መሐመድ በመካ የሚገኘውን የካዕባውን የእግዚአብሔር ቤት ከጣዖት አምልኮ አጸዱ። ይህ በኢየሱስና በመሐመድ የተካሄደው ቤተ መቅደስን የማጽዳት ሥራ በዚህ ረገድ ኢየሱስና መሐመድ ተመሳሳይ የሆነ ሥራ እንደ ነበራቸው የሚያሳይ ነው። ነገር ግን የኢየሱስ ተልእኮ የተበላሸውን መቅደስ በማጽዳት ብቻ ያበቃ አልነበረም። እውነተኛ አምልኮን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ረገድ ቤተ መቅደሱ የማይጠቅም መሆኑን በመግለጽ፣ ባለሥልጣናቱን ክፉኛ አስደንግጦአል (ምዕራፍ 9 ይመለከቷል)።

## መሲሑ ራሱ ቤተ መቅደስ ነው

ቤተ መቅደሱን ሲያጸዳ በተፈጠረው ኹከት መካከል፣ "ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስተኛው ቀንም አስነሣዋለሁ" (ዮሐንስ 2፥19) ብሎ በመናገር የቤተ መቅደስ ባለሥልጣናትን የበለጠ አስቈጣቸው። በሌላ ጊዜ ደግሞ ለደቀ መዛሙርቱ ስለቤተ መቅደሱ መፍረስ ትንቢት በሚናገርበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በሁኔታው ተደናግጠዋል:— "ይህ የምታዩት ሁሉ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ" (ሉቃስ 21፥6)።

መሐመድ የእግዚአብሔርን ቤት ወይም ካዕባን የሚተኩ መሆናቸውን አልገለጹም፤ በዚህ መልክም ራሳቸውን አላቀረቡም። እንዲያውም በየዓመቱ ወደ ካዕባ የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ፣ ለሙስሊሞች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤት አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን የሚያስተምር ነው[9]።

ኢየሱስ ግን በሰው እጅ የተሠራ ቤተ መቅደስ አስፈላጊ እንዳልሆነ አስተምሮአል። እንዲያውም ኢየሱስ እርሱ ራሱ የቤተ መቅደስ ምትክ እንደ ሆነ ይፋ አድርጎአል። ስለዚህ እርሱ አሁን ወደ ምድር መጥቶአል። ከዚህ የተነሣ ቤተ መቅደስ ከዚህ በኋላ አያስፈልግም። እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነውና[10]። ኢየሱስ ሕግን ተላላፊ ተደርጐ እንዲቈጠር እንዲሁም እንዲሰቀል የሃይማኖት ባለሥልጣናት የጠየቁት በዚሁ ምክንያት ነበር።

[9] ካዕባ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ መልክዐ ምድራዊ ማዕከል ነው። ክርስቲያኖችም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህ ዐይነቱ መልክዐ ምድራዊ ማዕከል የላቸውም።

[10] N. T. Wright, *The Challenge of Jesus* (Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1999), 110.

በክርስቲያኖች የነገረ መለኮት አስተምህሮ የመሲሑ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነች። መሲሑ ኢየሱስ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስን ተክተዋል። ብቸኛው የእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር ሙላት ያለበት መሲሑና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መሲሑ በመካከላቸው የሚያድርባቸው (የሚኖርባቸው) የእግዚአብሔር ሕዝቦች ናቸው (ኤፌሶን 2፥19-22)። ኢየሱስ በግልጽ ያለማወላወል፣ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" (ማቴዎስ 18፥20) ብሎአል።

## የቤተ መቅደስ ተራራ

በሙስሊሞች መረዳት ካዕባ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት ቢሆንም ሌሎች ሙስሊሞች ግን ተጨማሪ የተቀደሱ ስፍራዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ተጠቃሹ የዐለት መስጊድ የታነጸበት የመቅደስ ተራራ ነው። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው፣ በወቅቱ ለእስራኤልና ፍልስጥኤማውያን በኢየሩሳሌም ጉዳይ ላይ ያለመስማማት ዋናው ምክንያቱ ሙስሊሞችም ሆኑ እስራኤላውያን ቤተ መቅደስ መጀመሪያ የተሠራበትን ስፍራ የራሳቸው ቅዱስ ስፍራ አድርገው ስለሚቈጥሩት ነው። ይህንን ስፍራ ኢየሱስ አስፈላጊ እንዳይደለ ገልጾአል።

በ2002 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ኢየሱስ የተወለደበትንና ቤተ ልሔም የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን የእስራኤል ጦር በወረረበት (በከበበበት) ጊዜ፣ በምድር ላይ የሚኖሩና ወደ ሁለት ቢሊዮን የሚጠጉ ክርስቲያኖች በሰላማዊ ሰልፍ በዓለም ዙሪያ ያለመውጣታቸው ሙስሊሞችን እጅግ እንዳስደነቃቸው ሙስሊማን የሆኑ ጓደኞቼ ነግረውኛል። ክርስቲያኖች ፍጹም የተለዩና የተቀደሰ ስፍራቸው ሲዋረድ እንዴት ዝም ብለው ማየት ቻሉ? የሚለው ጥያቄ እንቈቅልሽ ሆኖባቸዋል። መስከረም 27 ቀን 2000 ዓ.ም ላይ ሙስሊሞች በመስጊድ በተሰበሰቡበት ሰዓት ኤሪያል ሻሮን ጦራቸውን ወደ መቅደሱ በመሩበት ጊዜ ታማኝ ሙስሊሞች ለቅዱስ ስፍራቸው ያሳዩትን ታማኝነትና የዐመፅ ቅስቀሳ (ኢንቲፋዳን) ከዚህ ጋር በማወዳደር ይጠይቃሉ። የተቀደሰው የመታሰቢያ ስፍራ ሲናቅ በእርግጥ ክርስቲያኖች ደንግጠዋል አዝነውማል፤ ይህ ዐይነቱ ስሜት ተሰምቶአቸዋል። ሆኖም የእግዚአብሔር ቤት በሰው እጅ እንደማይሠራ ክርስቲያኖች ያምናሉ። እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ፣ "እናንተ ደግሞ በእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ" (ኤፌሶን 2፥22) የሚል ተስፋ ቃል ተሰጥቶአልና።



## የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጉዞ

የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ወደ ተቀደሰ ስፍራ ሃይማኖታዊ ጉዞዎች ማድረግ አያስፈልገውም። በሰው እጅ የተሠራ ክርስቲያኖች የግድ የሚጐበኙት ስፍራ የለም። ይህም የሆነበት ምክንያት አዲሱ የእግዚአብሔር ቤት ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠራ ባለመሆኑ ነው። ሆኖም አዲሱ የእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው። ስለዚህ የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ ተቀደሱ ስፍራዎች ሳይሆን እግዚአብሔርን በእምነት መከተልና እሱ ወደሚሻውም የሕይወት ዘይቤ መሄድ ነው። ሃይማኖታዊ ጉዞ የእግዚአብሔርን ጸጋ መካፈል፣ መቀበልና በዚህም ሐሴት ማድረግ ነው።

የጌታ ራት (ቅዱስ ቁርባን) የክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጉዞ ተምሳሌት ነው። የጌታ ራት ማለት "ጸጋ፣ ደስታና ምስጋና" ማለት ነው። በቅዱስ ቁርባን በሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ ውስጥ ለሚገኙት ጸጋ፣ ደስታና ምስጋና ምንጫቸው ምንድን ነው?

## ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ፋሲካን አብረው በሉ

ኢየሱስ ታልፎ ከመሰጠቱ፣ ከመታሰሩና ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን ለማክበር አብሮአቸው ሆኖአል። ፋሲካ በፈርዖን ባርነት ሥር የነበሩትን የእስራኤላውያንን የበኵር ልጆች እግዚአብሔር በተሠዋው በግ ደም አማካይነት ከሞት ያዳነበትና ከፈርዖን ባርነት ነጻ ያወጣበት መታሰቢያ ነው። በዚያች ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት በበላበት ጊዜ የፋሲካን ትርጒም ከሚጠብቀው መሥዋዕታዊ የመስቀል ሞትና ከሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ጋር አያይዞታል።

## የተቈረሰው ዳቦና የተጨመቀው የወይን ፍሬዎች

ኢየሱስ ዳቦውንና ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፣ "መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን ፋሲካ አብሬያችሁ ለመብላት በጣም ስመኝ ነበር፤ እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት የዚህ ትርጒም እስኪፈጸም ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም" (ሉቃስ 22፥15-16) ዳቦውንም ቈርሶ ሰጣቸውና "ስለእናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው" አላቸው በመቀጠልም ጽዋውን "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴዎስ 27፥27-28)። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ክርስቲያኖች

በየጊዜው ተሰብስበው ዳቦውንና ወይኑን አብረው ይካፋላሉ። ይህም የክርስቶስን መከራና ስቅለት ለማሰብ ነው።

ኢራን ውስጥ ቆም በሚባለው ሰፍራ በሚገኘው በኢማም ሆሚኒ የትምህርት ምርምር ተቋም አስተማሪ የነበሩት ሮይ ሃንግ ከወንጌል እጅግ የሚያስደንቀው ነገር፣ ከተቈረሰው ዳቦና ከተጨመቀው የወይን ምልክት በስተኋላ ያለው ትርጉም ነው በማለት ተናገረዋል። ይህ የመከራና የአገልግሎት ምልክት ነው። የወይን ፍሬዎች ተቈርጠው ይጨመቃሉ፤ ከዚያ የሚጠጣ ወይን ይሆናሉ። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የጠራብት ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው። ይህ ሃይማኖታዊ ጉዞ ዓለም ልትረዳው የማትችለው ከኢየሱስ ጋር በዓለም የሚደረግ የመከራ፣ የአገልግሎትና ራስን አሳልፎ የመስጠት የአምላክ ፍቅር ነው። ሆኖም በዚህ ማዳንን የተላበሰ የመከራ ጉዞ፣ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብን የሚፈውስ አካል ትሆናለች። የክርስትና ሕይወት ይህን በመሰለው ሃይማኖታዊ ጉዞ የተሞላ ነው።

## ግብዣ

ይህ ዐይነቱ ክርስቲያናዊ የሃይማኖት ጉዞ ኀጢአተኞች በመሲሑ በኢየሱስ ስም ለመሰብሰብ የተደረገ ግብዣ እንዲሁም ውድ የሆነውን የኀጢአት ይቅርታ፣ የጸጋን ስጦታ መቀበያ እንዲሁም ወደ ዓለም ሁሉ ይህንን ግብዣ ማድረሻ ጥሪ ነው። የተቈረሰው ዳቦና የተጨመቀው ወይን ለተቀበሉት ሁሉ ሕይወትን እንደሚሰጠው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም በመሲሑ በኩል የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሚቀበሉ ሁሉ ሕይወትንና ፈውስን ትሰጣለች።

ሃይማኖታዊ ጉዞ ስሜትን ያካተተ ነው ይኸውም ዕይታንና ሐሴትን። ሙስሊሞች ከሃጂ (ከሃይማኖታዊው) ጉዞ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ በዚያ ጉዞ የተሰማቸውን እየተናገሩና እያሰቡ ነው የሚጓዙት። ለክርስቲያኖች በቅዱስ ቊርባን የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ በእግዚአብሔር ታላቅ የጸጋ መዳሰስ የተሞላ ነው። ይኸም አምላኪዎቹ የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክት የሆነውን የተቈረሰ ዳቦና የተጨመቀ ወይን ሲወስዱ የመሲሑ መሥዋዕት ኀጢአተኞችን ለመቤዠት መሆኑን ስለሚያስተውሉ በደስታና በምስጋና እንዲሞሉ ያደርጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖታዊው ጉዞ ላይ ነች። ኢየሱስ በመጨረሻው የፋሲካ ራት ላይ ጽዋውን አንሥቶ ሲሰጣቸው እንዲህ አለ፣ "ነገር ግን እላችኋለሁ፣ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ



አዲሱን እንከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ፣ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም" (ማቴዎስ 26+29) ይህ አባባል የታሪክ ፍጻሜን ይጠቁማል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ*
ዮሐንስ 2+12-22፤
*የቁርአን ምንባብ*
ሱራ 2+196-203፤ 22+26-33

## የአስተውሉትና የውይይት ጥያቄዎች

1. አብርሃምና እስማኤል በሙስሊም ሃይማኖታዊ ተጓዦች መታሰባቸው ያለውን አስፈላጊነት አገናዝብ። በዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞ የሚደረጉ ነገረ መለኮታዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው (ሱራ 2+124-27፤ 37+99-111)?
2. መሐመድ በመካ ከሚገኘው ካዕባ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል (ሱራ 2+124-128)? ኢየሱስ ከኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር (ሉቃስ 2+41-50፤ ዮሐንስ 2+19-22፤ ሉቃስ 21+5-6፤ ኤፌሶን 2+19-22)? ቤተ መቅደሱን አስመልክቶ ኢየሱስ ከተናገራቸው ንግግሮች መካል እጅግ የሚያስደንቀው ንግግር የቱ ነው?
3. ሙስሊሞች የእግዚአብሔር ቤት ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? (ሱራ 5+100፤ 2+26)? የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በተመለከተ የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ምን ይመስላል (ዮሐንስ 2+19-22)?
4. በእስልምና ሃይማኖት የመሥዋዕት በዓል ምን ትርጉም ነው ያለው (ሱራ 22+28)? በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የቅዱስ ቊርባን ትርጉም ምንድን ነው (1ቆሮንቶስ 11+23-28)?
5. የመሥዋዕት በዓል ትርጉም የእግዚአብሔር በግ ሆኖ መሥዋዕት የሆነውን መሲሑን አመላካች እንደ ሆነና በመሲሑ እንደ ተፈጸመ ሙስሊሞች እንዲረዱት ማሳሰብ ትክክል ነውን? ለመልስዎ ምክንያት ይስጡ።